# ሐመር


## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

መጀመርያ ዓመት ቁጥር 7

ጥር 1986 ዓ.ም.



የጥምቀት አከባበር በላሊበላ



**የልደት በዓል አከባበር በላሊበላ ቤተ ክርስቲያን**
**«ቤዛ ኵሉ ዓለም»**


- ✣ ስለክርስቶስ የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው
- ✣ እውነት ጾም አይጠቅምም?
- ✣ ቬነስያ .....
- ✣ ማዳኑን ያዩ ይናገሩ
- ✣ ከቦረን ዋሻ–እቲየማርያም
- ✣ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል
- ✣ የምንፈልገው ኦርቶዶክሳዊ ወጣት
- ✣ መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው
- ✣ ክርስቲያናዊ ቤት


©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org


① በምድር፡ላይ፡ ለዘላለም፡መኖር ትፈልጊያለሽ? ሚሚዬ
② በወንጌሉስ፡ እንኳን፡ምድር፡ ሰማይም፡ ያልፋሉ ተብሏል፡
③ በመጽሐፍ፡እኮ፡ ሰማይ፡ዙፋኔ፡ምድር መረገጫዬ፡ ነው፡ ተብሏል፡ ካለፉ፡ እግዚአብሔር፡ የት፡ ሊቆም፡ የት፡ ሊቀመጥ፡ ነው?
④ ሰማይና፡ምድር ከመፈጠራቸው፡ በፊት፡ እግዚአብሔር የት፡ ነበር፡ ልትለኝ፡ ነው?

# ሐመር

መጀመርያ ዓመት ቁጥር 7
ጥር 1986 ዓ.ም.

## ይዘት

ከአዘጋጁ............................ 1
የማኅበሩ መልእክት ................ 2
ደብዳቤዎቻችሁ ..................... 3
ትምህርተ ሃይማኖት
✤ ስለክርስቶስ የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው .............. 4
✤ እመአምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ .... 7
✤ መዝሙርና ምሥጢራዊ ሥርዓቱ ........ 8
የጥያቄዎቻችሁ መልስ
✤ እውነት ጾም አይጠቅምም? ....... 11
✤ አምላኩ የቀረበው ማነው? (ስብከት).... 14
ኪነጥበብ
✤ ቬነስያ .......................... 16
✤ ማዳኑን ያዩ ይናገሩ ................ 20
እናስተዋውቃችሁ
✤ ከቦረን ዋሻ–እቴየማርያም ......... 21
✤ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል........................ 23
ዓምደ ወራዙት
✤ የምንፈልገው ኦርቶዶክሳዊ ወጣት........ 25
✤ መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው ....... 27
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
✤ ክርስቲያናዊ ቤት .................. 29
በረከተ ወንጌል
✤ ይህ ሕፃን ምን ይሆን? ........... 31

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክንን ትምህርተ ሃይማኖት፥ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ

# ከአዘጋጁ

### «እንኳን ለብርሃን ጥምቀቱ አደረሳችሁ»

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

«እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎቹ አናንቀላፋ»

1ኛ ተሰሎ.5፥6።

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንደተናገረው ዛሬም እኛ እንደ ሌሎቹ ተስፋ እንደሌላቸው የክርስቶስ ብርሃን እንዳልበራላቸው ለኃጢአት ሥራ የምንነቃና ለጽድቅ ሥራ የምናንቀላፋ መሆን የለብንም። የጨለማ ልጆች ሥራቸውን ሁሉ ጨለማ ለብሰው በሌሊት ይሠራሉ ዝሙቱ፥ ስካሩ፥ መግደሉ፥ መዝረፉ፥ መስረቁ...የመሳሰሉት የኃጢአት ሥራ በጨለማ ነው የሚሠሩት «እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ» 1ኛ ተሰሎ.5፥8።

የብርሃን ልጆች የብርሃን ሥራ ልንሠራ እንደሚገባን ተነግሮን ሳለ እኛ ግን የጨለማ ሥራ ከላይ የተዘረዘሩትን የምንሠራ ከሆንን ብርሃናችን እንኳን ለሌላ ሰው ሊበራ ቀርቶ ለራሳችንም ጨልመናል ማለት ነው። ስለዚህ የብርሃን ልጆች እውነተኛው ብርሃን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ሕይወት በርቶ እኛም የጽድቅ ብርሃናችን ለሌላው ሰው እንዲበራ ማድረግ ይኖርብናል። «ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ ተብለናልና» የጠራን እርሱ ለመቅሰፍት ሳይሆን ለዘላለማዊ ሕይወት ነው። ስለሆነም መጠራታችንን ተመልክተን ከሚመረጡት ወገኖች ለመሆን በሃይማኖት ልንነቃ በምግባር ልንጐለብት ይገባል ያለበለዚያ ተጠርተን ነበር የሚለውን ዘይቤ ይዘን እንቀራለን።

ከተመረጡት ወገኖች እንድንሆን የእርሱ ቅዱስ ፈቃድ ይሁን።

ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ
ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.እሸቱ ታደሰ ወ/አገኘሁ
✉ 80078
☎ 110754
አዲስ አበባ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

ለዛሬው የማኅበሩ መልእክት እንዲሆን የመረጥነው በአንድ ወቅት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ስለ ጥምቀት ያስተማሩትን ትምህርት ይሆናል።

## ጥምቀት

ማቴዎስ 3 ቁጥር 17

ቤተ ክርስቲያናችን በሚዳና በውሀ ዳር የምታከብረው ትልቅ በዓል የጥምቀት በዓል ነው። በዚህ ምዕራፍና ቁጥር እንደ ተገለጠው ጌታ እስከ ሠላሳ ዓመት ድረስ ከእናቱ ጋር ቆይቶ በሠላሳ ዓመቱ ከገሊላ ምድር ወደ ይሁዳ ምድር ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ያን ጊዜ በዮርዳኖስ ዮሐንስ መጥምቅ በትምህርቱ ያመኑትን ሰዎች ያጠምቅ ነበር። ሰዎቹም ኃጢአታቸውን እተናዘዙ ይጠመቁ ነበርና። መድኃኒታችን ወደ ዮርዳኖስ እንደ መጣ ዮሐንስ ልዕልናውን አይቶ ለመጠመቅ ትመጣለህን? የሚል ጥያቄ አቀረበለት። ጌታም ይህ ሊፈፀም የሚገባው ጉዳይ ነውና እምቢ አትበል አለው። ዮሐንስም ለቃሉ ታዞ አጠመቀው በዚህ ጊዜ:-

ሀ. ሰማይ ተከፈተ፥

ለ. አብ በደመና ሁኖ ስለ ወልድ መሠከረ፥

ሐ. መንፈስ ቅዱስም በጥንተ ተፈጥሮ በውሀ ላይ እንደ ታየ፥ አሁን በሐዲስ ተፈጥሮ ታየ።

ይህም አስተርእዮ (ኤጲፋንያ) ይባላል።

አሁን ቤተ ክርስቲያናችን በያመቱ የጥምቀትን በዓል ጥር 11 ቀን የምታከብረው ታቦቶቻችንን ከየቤተ ክርስቲያኖቻችን በማውጣት በውሀ በወንዝ ዳር ድንኳን ተክለን ዳስ ሠርተን እዚያው በማደር ሌሊት በጸሎተ ማኅሌትና በቅዳሴ እግዚአብሔርን ስናመሰግን እናድራለን። ይህም የቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት፥ በወንጌሉ እንደ ተገለጠው ኹሉ ጌታ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ተጉዞ እዚያው በዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ተራውን ሲጠብቅ አድሮ የመጠመቁ ምሳሌ ነው። ሲነጋም ወንዙ ተባርኮ ሕዝቡም ፀበል ተረጭቶ የባህል ጨዋታዎችን እየተጫወተ ይቆያል። ታቦታቱ ካደሩበት ድንኳን ወጥተው በምዕመናኑ ተከብረው ወደየቤተክርስቲያናቸው ይሔዳሉ። ይህ ነው በሀገራችን የጥምቀት በዓል።

ይህን በዓል ለማክበር የተሰበሰባችሁ ምዕመናን ጥምቀት ለክርስቲያኖች የሕይወት በዓል ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ሰውን ለመፈለግ ሰውን ለማዳን የመጣ እንደመኾኑ ኹሉ የወደቅንበትን ቦታ ኹሉ አስሶታል። አኹን ዛሬ የምናየው የምናከብረው እገዚአብሔር የሰውን ልጅ በውሀ ውስጥ ሲፈልገው ነው። ፈልጎም አላጣው አግኝቶታል። ተዘግቶ የነበረው ሰማይ ተከፈተ። የአምላኩን ገጽታ አጥቶ ጣኦታትን ያመልክ የነበረው የሰው ልጅ የአምላኩን ፊት አየ። አምላኩን አወቀ። በጥፋቱ ያጣትን ገነት እንደገና ተከፍታ አያት፥ አገሩ መኾኑን አወቀ ወደ እሷም ገባ። እንግዲህ የዚህ በዓል ቁም ነገሩ ይህ ነው። ትናንት በበረት በእንስሳት መካከል የተገኘው መሢሕ ዛሬ በዮርዳኖስ ውስጥ ከኀጢአተኞች ጋር ተሰልፎ ጥምቀትን ሲጠባበቅ ያየነው እኛን ከወደቅንበት ለማንሳት ስለኾነ ልንረሳው አይገባም። የዩርዳኖስ ውሀ ንዕማንን ከለምጹ የፈወሰ ነው። እሥራኤል ከግብጽ ከወጡ በኋላ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ነው ወደ ምድረ ርስት ወደ ኢየሩሳሌም የገቡት። እኛንም መሢሐችን ከነባር ደዌያችን ያዳነን ወደ መንግሥቱም መርቶ ያስገባን በጥምቀት ነው።

ምዕመናን የጥምቀት ልጆች እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ። እኛ እንግዲህ በክርስቶስ ጥምቀት የተጠራን ኹሉ በዚህ ጥምቀት የተከፈተልንን የእግዚአብሔር ቤት መልሰን እንዳናዘጋው። ወደ ምድረ ርስት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከገባን በኋላ እንደገና ወደ ኋላ እንዳንመለስ ዮርዳኖስ የሕይወት ውሀ ነው፥ የሕይወት ወንዝ ነው፥ የበረከት በር ነው። ይህንን ረስተንና ዘንግተን ወደ ሙት ባሕር እንዳንገባ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ብዙ ሰዎች ዛሬ ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከገቡ በኋላ እንደገና ወደ ሙት ባሕር እየዘለሉ እየገቡ ነው። ታዲያ በሙት ባሕር ሕይወት ስለሌለ እዚያው ቀልጠው ይቀራሉ። ይህም ያሳዝናል የዘለዓለም ሞት ነውና። እዚህ አኹን ላላችሁት ምዕመናን አደራ የምንለው ሕይወታችሁ እንዳይጋለጥ ነው። ተመለሱ፥ በንስሐ ወደ ምድረ ርስት መሻገሪያ ወደ ፈለገ ንስሐ ተመልከቱ። የመድኃኒታችንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀበሉ። ለዘለዓለም ሕይወት ይሆንላችኋል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ከአባ ጎርጎርዮስ
የሸዋ ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
በጽሑፍ ካዘጋጁት ስብከት የተወሰደ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

በዚህ ዓምድ ከአንባብያን የተላኩ ገንቢ አስተያየቶችንና መንፈሳዊ ምክሮችን እናቀርባለን።

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል
አዲስ አበባ

እኔ ያለሁት እዚህ አሜሪካ ሎስአንጀለስ ነው በቅድስት ማርያም ስም ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ነገር ግን ራቅ ስለሚሉ እንደ ኢትዮጵያው ሁሉ መማር አልቻልኩም። እንዲሁም እዚህ ያሉት የሰ/ት/ቤት ተማሪዎችም መጽሔታችሁን አሳይቻቸው በጣም ተደስተዋልና በተቻለ መጠን ሳታቋርጡ ላኩልን።

ራሔል ገበየሁ
ሎስአንጀለስ አሜሪካ

● ራሔል መጽሔታችንን በተቻለን መጠን እያሰብን እንልክላችኋለን ክፍያ ለአንድ መጽሔት ሁለት ዶላር ነው ከነመላኪያው። አብረውሽ ያሉትን የሰ/ት/ቤት ወጣቶችም ሰላም በይልን በሃይማኖት ጸንታችሁ ኑሩ።

እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል
አዲስ አበባ

በቁጥር 5 ሐመር መጽሔት «ሃይማኖት ይታደስ ይሆን?» የሚለውን ሳነብ ሐመር የልቤን ተናገረችው አልኩ ቃለ ሕይወት ያሰማችሁ ዛሬም ነገም የእምነታችን መሠረት ፈሩን እንዳይለቅ የ«ምን አለበት» መንፈስ መጥፋት አለበት።

ደጉ ማሞ እና ስለሺ ፈይሳ – ከጅጅጋ

● አሜን። የሁላችን ጥረት ሊሆን ይገባል። ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔር ይጠብቀን።

✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል
አዲስ አበባ

በቅድሚያ በእግዚአብሔር ስም ስላምታዬን እያቀረብኩ ሐመርን እዚህ ሳገኛት የተሰማኝን ደስታ እገልጻለሁ እንደ ጅምራችሁ መጨረሻችሁን ያሳምርላችሁ።

አሸናፊ ቢሻው
ከመካነ ኢየሱስ ቅ/ማርያም ሰ/ት/ቤት
ደ. ጐንደር እስቴ

● አሜን!

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል
አዲስ አበባ

በቁጥር 5 በገጽ 13 የቀረበውን «ኃጢአቴን ለካህን ባልናገርስ? የሚለው በኀሊናዬ የነበረ ጥያቄ በመሆኑ ለመልሱ አመሰግናለሁ።

ጸጋዬ በርሄ
የደብረ ቅዱሳን አቡነ አረጋዊ ሰ/ት/ቤት
መቀሌ. ዓዲ.ሐቂ

● አሜን ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን።

✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች በሙሉ

በቅድሚያ በጌታ ስም ሰላም እያልኩኝ የእኔ ብቻ ሳይሆን የመሰል ወንድሞችና እኅቶችም ጭምር የሆነውን ሃሳቤን አቀርባለሁ። ሃሳቤንም ተግባራዊ እንደምታደርጉት ተስፋ አደርጋለሁ፤ ይኸውም ቤተ ክርስቲያናችን እንደሌሎች ለምን አንድ የሬድዮ ክፍለ ጊዜ አይኖራትም? ትምህርቶችንና መዝሙራትን በሚገባ ለማስተላለፍ ይረዳልና ቢታሰብበት እንዲሁም ውጭ ሀገር ለሚገኙ የቤተክርስቲያኒቱ ልጆች አስታውቃችሁ እንዲተባበሩ ቢደረግ መልካም ይመስለኛል የእመቤታችን አማላጅነት ሁላችንንም አይለየን።

ወርቅነሽ አበበ ከወለጋ ነቀምቴ

● ሃሳብሽ አስፈላጊና ሊታሰብበት የሚገባ ነው። የሚመለከተው ክፍልም እንደሚያስብበት ተስፋችን ነው።

✣ ✣ ✣

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል
አዲስ አበባ

በመጽሔታችሁ ውስጥ የሚገኘው የቦረዳው ድንቅ ዋሻና ሌሎች አስደናቂ የሆኑ ገዳማትና ዋሻዎች ታሪክ አስደስቶኛልና ግፉበት ለተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያለኝም አክብሮትና ፍቅር ጨምሯልና ለምታደርጉት ሐዋርያዊ ተልእኮ የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጸሎትና ምልጃ አይለያችሁ።

ዲ. ሃብታሙ ደምሴ እና ጌቱ ኃ/ማርያም
(ከጊንጪ ቅ/ሚካኤል) ዲፕሎማቲክና
ዓለምአቀፍ ድርጅት አገልግሎት

● አሜን! እናንተም በተሳትፎአችሁ አትለዩን

ለሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል
አዲስ አበባ

በመጽሔታችሁ ተደስተናል ነገር ግን በወቅቱ አይደርሰንምና አስቡበት።

ሠረበ ታደሰ
ድሬዳዋ ቅ/ማርያም ሰ/ት/ቤት

● ሰረበ በስርጭት በኩል በቶሎ እንዲደርሳችሁ መጽሔቱ መውጣቱን እንደሰማችሁ ሰው ብትልኩ በተለይ በቅድሚያ ገንዘብ ካላችሁ 20% ቅናሽ ወስዳችሁ ታከፋፍላላችሁ። ሌሎች አካባቢዎችም እንደዚሁ ብታደርጉ በተቀላጠፈ ሁኔታ ማሰራጨት ይቻላል።

✣ ✣ ✣

ከሁሉም አስቀድሞ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ይክበር ይመስገን አሜን።

ሐመሮች:-

በሥራችሁ እጅግ እኮራለሁ። እስከዛሬም ምንም እንከን አላገኘሁበትም ነበር። ነገር ግን በቁጥር 6 እትማችሁ በኪነጥበብ አምድ ሥር ማዳኑን ያዩ ይናገሩ በሚለው ጽሑፍ እምቤታችን ወይን ጠጅ ማለቁን ያወቀችው በመንፈስ ቅዱስ ተመርታ እንጂ እናንተ እንዳላችሁት ደኪማስን ጠይቃው አይደለም።

ታናሽ እህታችሁ ወለተሥላሴ ከአ/አ

● ወለተ ሥላሴ:- ስለሰጠሽን አስተያየትና እርምት እግዚአብሔር ይስጥልን። በዚህ አጋጣሚ ስለተደረገው ስህተት አዘጋጁ ከፍተኛ ይቅርታን ጠይቋል። ሁለተኛም ላለመድገም በእመቤታችን ስም ቃል ገብቷል ለሁሉም እርሷው ትርዳን ከስህተትም ትጠብቀን አሜን።

✣ ✣ ✣

ሽፈራው ጌታቸው (ከለገጣፎ)፤ ታደለ ገ/መድኅን (ከመቀሌ) ብዙነህ ዘርይሁን (ከርቤም)፤ አዘዘው አበራ (ከጋይንት)፤ አልማዝ ገ/ኢየሱስ (ድሬዳዋ ቅ/ማርያም ሰ/ት/ቤት፤) ደረጀ ፋንቱ (ጅማ ደ/ሰላም ኢየሱስ ቤ/ክ)፤ አበባው ዘውዱ (ኢ.አ.ዩ. 6 ኪሎ) መሰለ በርሔ (አርባምንጭ) እና ሌሎችም አስተያየታችሁ ደርሰውናል። ከልብ እናመሰግናለን። ለወደፊቱም ግፉበት ለጥያቄዎቻችሁ መልሶችን በሚከተሉት እትሞች እናወጣለን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት።

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማና ቀኖና) የምንማርበት ይሆናል።

## የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው።

• ካለፈው የቀጠለ

ከብርሃኑ ጎበና

ማቴ.12፥32

«በሰው ልጅ ላይ ቃልን የተናገረ (የተሳደበ) ኃጢአቱ ይሰረይለታል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተናገረ ግን አይሰረይለትም በዚህ ዓለምም ቢሆን በሚመጣውም ዓለም ቢሆን።»

በብዙ ቦታ ላይ ጌታ ራሱን የሰው ልጅ ብሎ ሲጠራ ይታያል። የሰው ልጅን ባሕርይ ባሕርይ አድርጓልና። ስለራሱ ሲናገር የሰው ልጅ ይላል። ማቴ.24፥27። የሰው ልጅ ብሎ ስለራሱ ከተናገረ ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍና ቁጥር ላይ የሰው ልጅን የሰደበ ኃጢአቱ ይሰረይለታል መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ግን አይሰረይለትም ሲል ራሱን ከመንፈስ ቅዱስ መለየቱ አይደለም።

በመሠረቱ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት በባሕርይ አንድ ሲሆኑ በአካላት ግን ሦስት ናቸው። ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ሥጋን ተዋሕዶ በመገለጡ የተነሳ በዘመኑ የነበሩ አይሁድ ጌታ ራሱን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔርነቱን ሲገልጽ አጋንንትን ሲያወጣ ድውያንን ሲፈውስ አይተው በሥራው ማመን ሲገባቸው እነርሱ ግን ደንዳና ልባቸውን የባሰ አደንድነው በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ስላሉት በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በመካከላቸው በመገኘቱ ሲበላ ሲጠጣ በማየታቸው ዕሩቅ ብእሲ (አምላክነት የሌለህ፥ ፍጡር) ስትሆን «ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር ለምን አስተካክለህ እግዚአብሔር ነኝ ትላለህ» ይሉት ነበር። እርሱም እኔ ሥጋን ተዋሕጄ የሰውነትን ሥራ በመሥራቴ ንቃችሁኛል ሰድባችሁኛል፥ ራሴን ዝቅ አድርጌ በትህትና መገለጤ ምክንያት ሊሆናችሁ ይችላል ዳሩ ግን መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት አድሮ ስለ እኔ የባሕርይ አምላክነት ከገለጸ ካስመሰከረ በኋላ ግን ፍጡር ብትሉኝ ብትሰድቡኝ ኃጢአታችሁ አይሰረይላችሁም። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ሕፁፅ (ፍጡር) የሚል ኃጢአቱ በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው እንደማይሰረይለት መግለጹ ሲሆን ነገር ግን ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለው የታወቀ ነው። ዋናው ነገር በመለኮት አንድ የሆኑትን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን በአንድነት አስተካክሎ ያለማበላለጥ ማመን እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ያስተማረ ስለሆነ እኛም ለዘለዓለም እንዳንኮነን መንፈስ ቅዱስን ፍጡር ከማለት ልንጠበቅ እንደሚገባና ጌታንም ሰው ሆኖ ስለ ተገለጠ ብቻ መካድ ከፍርድ ነፃ እንደማያደርግ መረዳት አለብን።

ሮሜ.8፥34። «የሚፈርድ ማነው ክርስቶስኢየሱስ ሞተ ከሙታ ንም ተለይቶ ተነሳ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል ስለ እኛም ይፊር ዳል» (1)

ይህ አባባል በቅርብ ጊዜ በተተረጐሙት መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል «የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኰንንስ ማን ነው? የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው»

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል ከዘመን ወደ ዘመን ሊቀያየር ወይም ሰዎች እንደራሳቸው እምነት ሊተረጉሙት አልተፈቀደላቸውም።

«ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አል ተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» 2ጴጥ.1፥20–21።

ዳሩ ግን በቀድሞው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም ላይ ያለው ቃል በቅርብ ጊዜ ከታተሙት መጽሐፍ ቅዱሶች ጋር ሐሳቡ ሊጋጭ አይገባም: መቼም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አይጋጭም። ተርጓሚዎች ግን በሚሠሩት ስህተት የሚጋጩ ሐሳቦች ሊገቡ ይችላሉ።

እንግዲህ አብዛኛውን ጊዜ ክርስቶስን አማላጅ ነው የሚሉ ክፍሎች እንደመረጃ የሚያቀርቡት ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን በግእዝና በአማርኛ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ወንጌል «ይፈርዳል» ነው የሚለው። ክርስቶስ ከእንግዲህ ወዲህ የሚመጣው ለመፍረድ እንጂ ለመማለድ አይደለም፤ ይህን የሚያስቡ ካሉ ተሳስተዋልና ንስሐ ይግቡ። ማቴ. 25፥31–46፤ ማቴ. 16፥27፤ ኢሳ. 30፥33፤ ራእይ 20፥10–15።

የዘመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች የጥንቱን አባባል «ይፈርዳል» የሚለውን፤ ትርጉሙ ብዙ (ambiguous) በሆነ ቃል ለውጠውታል። «የሚማልደው» የሚለው ቃል አንድ ዓይነት ሐሳብን የሚገልጽ አይደለም። ለዚህም ነው ትርጉመ ብዙ ያልኩት። ለምን እንደመረጡት ያስጠረጥራቸዋል። ምናልባት ክርስቶስ አማላጅ ነው የሚለውን ትምህርት የሚደግፉ ሆነው ይህን



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

አመለካከታቸውን ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው አድርገው ለማቅረብ ይሆን? ወይስ ሌላ ምክንያት ኖሮ አቸው? የተሳሳተ አመለካከታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ አስመስሎ ለማቅረብ የተደረገ ሤራ ከሆነ «የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስን ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ» ገላ.1፥7። ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው በእነዚህ ሰዎች ተፈጽሞ ይሆን? ብዬ ራሴን በአድናቆት እጠይቃለሁ። ምናልባት በተንኮል የተደረገ ላይሆን ይችላል። ለማንኛ ውም ግን ሁሉ ነገር በእርሱ ዘንድ ግልጥ የሆነው አምላክ ያውቀዋል። እኔ ግን የቀደሙት ትርጉሞች እውነተኛ ትርጉም መሆናቸውን አም ናለሁ፤ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ከመነሻው እስከ መድረሻው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት፥ ፈራጅነት እንጂ አማላጅነት የሚናገር ስላልሆነ ይፈርዳል የሚለው ትክክለኛው የቅ/ጳውሎስ አባባል መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋ ዕለ ሥጋዌው (በሥጋ ተገልጦ በም ድር ላይ በተመላለሰበት ወቅት) የማስታረቅ አገልግሎትን መፈጸሙ በማንም የሚካድ አይደለም። እንዲህ ሲባል ግን እንደፍጡራን አማላጅ ነው ማለት አይደለም። ወዶ ፈቅዶ በገዛ ፈቃዱ የሠራውን የትህትና ሥራ ተዋራጅነት እንዳለበት አድርጐ ከትንሣኤው በኋላም ያማልዳል ማለት ግን ወደር የማይገኝለት የኑፋቄ ትምህርት ነው። ጌታ ከትንሣኤው በኋላ መለመን እንደሌለበት ሲገልጽ «በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም» ዮሐ.16፥26። በማለት መለመን ማማለድ እንደሌ ለበት ገልጾልናል።

በማኅፀን የጀመረው ካሣ በመስ ቀል ላይ ባደረገው መሥዋዕትነት የተፈጸመ መሆኑንና በትህትና ተገልጦ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የፈጸማቸው ሁሉ ለቤዛ ዓለም ለካሣ መሆኑን ገልጦ የመጣበትን ዓላማ መፈጸሙን «ሁሉ ነገር ተፈጸመ» ብሎ ገልጦአል።

ምናልባት ተቃዋሚዎች ያማል ዳል የምንለው በሥጋው ነው ለክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት እነዚህም ያልተዋሐዱ ሲሆኑ መለኮት የመለኮትነትን ሥራ ይሠራል ሰውነት የሰውነትን ሥራ ይሠራል ስለዚህ ሥጋ የመለኮት ተገዢ ስለሆነ ክርስቶስ በሥጋው ያማልዳል ማለት አይገባ ቸውም ከተዋሕዶ በኋላ ምንታዌ የለምና አባባሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ የፍልስፍና አነጋገር ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነርሱ እንደሚሉት ሁለትነት ያለው ሁለት ባሕርይ አለመሆኑን አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን መጽ ሐፍ ቅዱስን ዋቤ አድርገን ልንገልጥ እንወዳለን። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስረዱን መለኮት ትስብእትን (ሰውነትን) ተዋሕዶ በሥጋ የአምላክ ነትንም የሰውነትንም ሥራ ኹሉ እንደ ሠራ ነው። ከዚህ አልፈው ከተዋሕዶ በኋላ ባንድ ክርስቶስ ምንታዌ (ሁለትነት) (dualism) ኖሮበት ትስብ እቱ ለመለኮቱ ተገዛ የሚል ንባብ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በሃይማኖተ አበው አይገኝም።

ይህንንም በተጨባጭ ለማስረዳት ሁላችንም ባንድነት የምንቀበለውን መጽሐፍ ቅዱስ ምሥክር ልናደርግ ይቻላል።

1ኛ. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመርከብ ላይ ኾኖ በባሕር ላይ ሲሔድ ማዕበል ተነሥቶ መርከቡን ያማታው ጀመረ ደቀ መዛሙርቱ አቤቱ ተነሥተህ አድነን ልናልቅ ነው ብለው ቀሰቀሱት።

ጌታም እናንተ ሃይማኖተ ጎደሎዎች ምን ያስፈራችኋል አለና ተነሥቶ ነፋሳቱንና የባሕሩን ማዕበል ፀጥ እንዲል አዘዘው ሁሉም ነገር በጌታ ትእዛዝ ፀጥ ርጭ እንዳለ በማቴ.8፥23–27። እናገኘዋለን።

መተኛትና መቀስቀስ የሰውነት ሥራ ነፋሳትንና ማዕበላትን ገሥጾ ፀጥ ማድረግ የአምላክነቱ ሥራዎች መኾና ቸው፥ ሠሪያቸው ግን አንድ ክርስቶስ መኾኑ የማይካድ ነገር ነው።

ሁለት ባሕርይ ባዮች እንደሚሉት የመለኮትን ሥራ መለኮት የትስብእ ትን ሥራ ትስብእት (ሰውነት) ተከፋ ፍለው የሚሠሩት ኾኖ ቢኾን ነፋሳት ንና ማዕበላትን መገሠጽ በተለይ የመለኮት ሥራ ስለኾነ ትስብእትን ባልቀሰቀሱትም ነበረ።

እንግዲህ የተኛውና የተቀሰቀሰው ማዕበላትንም ፀጥ ያደረጋቸው ያው አንዱ ክርስቶስ ከኾነ አንድ እርሱን (ሥግው ቃልን) ኹለት አድርጐ ገዢና ተገዢ ነው ማለት እንደምን ይቻላል? አይቻልም።

ስለዚህ ክርስቶስ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ብሎ ሁሉንም ሥራ ለአንዱ (ለሥግው ቃል) መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

2ኛ. ጌታ ስለ እርሱ ማንነት የሰዎች አመለካከት ምን እንደሚመ ስል ሐዋርያትን ከጠየቀ በኋላ በመ ጨረሻ እናንተስ እኔን ማን ትሉኛ ላችሁ የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረበላ ቸው «ማን ትሉኛላችሁ?» የሚለው ጥያቄ ክርስቶስ አንድ መሆኑን ሁለትነት የሌለው መሆኑን የሚገልጥ ሲሆን የቅ.ጴጥሮስ መልስ ደግሞ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሚለውን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊነቱን ያጐላዋል። «ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ አለው» ማቴ.16፥16።

እንግዲህ ጴጥሮስ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ገዝፎ የሚያ የውን አካል የሕያው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ አንተ ክርስቶስ ነህ ብሏል። በዚህም የዮና ልጅ ስምዖን ይህን ምሥጢር (የክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆን) የሰማይ አባቴ እንጂ ሥጋዊ ደማዊ መምህር አልገለጸልህምና ንዑድ ክቡር ነህ ተብሎ ተመስግኖበታል።

3ኛ. ዮሐ.1፥18። «እግዚአብ ሔርንስ ከቶ ያየው የለም (በመለኮታዊ ክብሩ) በአባቱ እቅፍ ያለ (ከአባቱ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያልተለየ) አንድ ልጅ (ወልድ ዋሕድ) እርሱ ነገረን።»

እንግዲህ በዚህ አባባል ውስጥ ሁለት የሚል ነገር ተጠቅሷል? መለኮትን ከሥጋ ጋር አዋሕዶ አንድ ልጁ እያለ ሥጋ የመለኮት ተገዢ ነው በማለት መከፈል በሌለበት በአንዱ ጌታ ላይ፤ አንዱን ጌታ አንዱን ባሪያ ማድረግ ኑፋቄ አይባልም? እኛስ ወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ከሐዲው ንስጥሮስ ሁለት አድርገን በክርስቶስ ላይ አንቀል ድም። አካላትን አዋሕደው ባሕርይን የሚተው ያው ከንስጥሮስ ሃሳብ የራቁ አይደሉምና አካል ሲዋሐድ ባሕርይ ተለይቶ አይቀርም ባሕርይ አልተዋ ሐደም ከተባለ አካልም አልተዋሐ ደም ማለት ነው።

4ኛ. የሐዋ.20፥28። «እግዚአ ብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን...»

ከዚህ አባባል የምንረዳው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዕርቃኑን እንደ ብራና የተወጠረው የፍጥረታት ጌታ እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን ነው። የተሰቀለው ሰውነት ብቻ ነው እንዳንል ለይቶ እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ነው ያለው «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» ደም የሰውነት ገንዘብ ነው። ዳሩ ግን መለኮት በተዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ ገንዘብ አድርጓልና «እግዚአብሔር በደሙ» ተባለ። አይሁድ የቸነከሩት መለኮትን የተዋሐደ ሥጋን እንጂ ዕሩቅ ብእሲን አይደለም። መለኮትን ያልተዋሐደ ዕሩቅ ብእሲ ቢሆንማ ኖሮ ሊያድነን ባልቻለም ነበር። ያዳነን አምላካችን እግዚአብሔር ባሕርያችንን ባሕር ይው አድርጎ ራሱን ዝቅ አድርጎ የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ ነው። እንግዲህ መለኮታዊ ባሕርይ ከሥጋ ባሕርይ ጋር አልተዋሐደም ካሉ «የመዳናችን ነገር ወዴት አለ?» ምክንያቱም ዕሩቅ ብእሲ ሊያድን አይችልምና። እኛ ግን አንድ የሆነው እርሱን አምላክ ወልደ አምላክ ብለን ስለምናምን መለኮት ሥጋን ተዋሕዶ አዳነን እንላለን።

5ኛ. ዕውር ሆኖ የተወለደ ሰው በመንገዱ ላይ ሲያልፍ አይቶ በምድር ላይ ተፍቶ በምራቁ ጭቃ በማድረግ የዚያን ዕውር ዐይኑን ቀባው በሰሊሆም መጠመቂያ ታጥቦ እንዲመጣ አዘዘው ዕውሩም የተባለውን አደረገ አየም።...

ጌታችንም ያን ዕውር ሆኖ የተፈወሰን ሰው አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን አለው። ያ ሰውም መልሶ አቤቱ አምንበት ዘንድ እሱ ማን ነው። ብሎ መለሰለት ጌታ ኢየሱስም የምታየው ካንተ ጋርም የሚነጋገረው እርሱ ነው አለው። አቤቱ አምናለሁ አሉና ሰገደለት። ዮሐ.9፥1–39።

በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን ብሎ የጠየቀው ከድንግል ማርያም የተወለደው ነው። አምን ዘንድ እርሱ ማን ነው? ብሎ ለጠየቀው የሰጠው መልስ የምታየው ካንተ ጋርም የሚነጋገረው እርሱ ነው የሚል ግልጽ የሆነ መልስ ነው። መለኮት በሥጋ ታይቷልና ሥጋን ተዋሕዶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ስለተወሰነ እንዲህ ሊል ቻለ፥ ታዲያ እዚህ ላይ ሁለትነትን ወይስ አንድነትን የሚያስ ገነዝበው? መለኮታዊ ባሕርይ ከሥጋ ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ አንድ ባይሆን ኖሮ የሥጋ የሆነ ምራቅ የዕውሩን ዓይን ባላበራው ነበር። በየትም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጌታ ሁለት ባሕርይ እንዳለው የሚገልጽ የለም።

ድካሙም ኃይሉም ብርታቱም ማዘኑም ማልቀሱም ሁሉም የአንዱ የሥግው ቃል ሥራ ነው። በአንድ ክርስቶስ ሁለትነት ፈጽሞ የለም። ያዘነው፥ ያለቀሰው የሥጋ ባሕርይ ኃይል ተአምር የሚያደርገው የመለ ኮት ባሕርይ ብለን መከፈል በሌለበት በአንዱ ጌታ ላይ መከፈልን የምንፈ ጥር ከሆን ቁጥራችን በክርስቶስ ዳንን ብለው ከሚያምኑ ወገኖች ሳይሆን ከአላውያን (ከከሐድያን) ነው።

በመሠረቱ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የትርጉም መዛባት እንዳለ የሚያረጋ ግጥ ቃል በዚሁ ምዕራፍ ሜሉት በሮሜ.8፥27። ላይ እናገኛለን።

«ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይ ነገር መቃተት ይማልድልናል» የሚ ለው የቅርብ ጊዜ ትርጉም የሥላሴን ትምህርት የሚያፋልስ ነው።

ምክንያቱን እጠቅሳለሁ 1ኛ. መንፈስ ቅዱስ ፍጡር ይመስል መቃ ተት የለበትም፤ ወይም ከላይ ክርስ ቶስን በሥጋው ያማልዳል እንዳሉት መንፈስ ቅዱስን በሥጋው ይማልዳል እንዳይሉ ሥጋን ተዋሕዶ እንደ ወልድ አልታየም። ስለዚህ መቃተት የሥጋ ለባሽ ባሕርይ ሲሆን ሥጋን ተዋሕዶ ያልተገለጠውን አምላክ በማይነገር መቃተት ይማልዳል ብሎ መተርጐም ስህተት ነው። በዚህ አባባል መንፈስ ቅዱስና ወልድ አማ ላጅ አብ ተማላጅ ከሆኑ ብቸኛ አምላክ አብ ብቻ ነው ወልድና መን ፈስ ቅዱስ ከአብ ያንሳሉ እንደማለት ነው። ዳሩ ግን የቀደሙትን ትርጉሞች ብንመለከት «በመንፈስ ቅዱስም ከድካማችን ይረዳናል እንግዲያማ ተስፋችንን ካላወቅን ጸሎታችን ምንድን ነው ነገር ግን እርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ስለመከራችን ስለችግ ራችን ይመልስልናል እርሱ ልቦናች ንን ይመረምራል ልብ ያሰበውንም እርሱ ያውቃል ስለ ቅዱሳንም ይፈርዳል » በሁለቱም ላይ ይፈርዳል የሚለው ይማልዳል በሚለው ቃል ተተክቷል። ምናልባት በተርጓሚዎቹ አመለካከት የሚማልደው የሚለው አባባል ፈራጅነትን የሚያመለክት ከሆን መልካም ግን ግልጽ የሆነን አባባል አስወግዶ አሻሚ ቃልን መምረጥ አግባብ አይሆንም።

ስለዚህ ጳውሎስ ለሮም ሰዎች ክርስቶስ ዛሬም በአብ ቀኝ ተቀምጦ ያማልዳል ሳይሆን ይፈርዳል ነው ያለው። ስለሆነም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር የተካከለ እንደ አብ ጸሎትን የሚቀበል (የሚማለድ) እንጂ እንደ ቅዱሳን አማላጅ አይደለም።

ዕብ.5፥7። «ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜም በታላቅ ጩኸትና ዕንባ ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ እውነቱንም ሰማው።»

ይህ አባባል የሚገልጸው ጌታ ራሱን በፈቃዱ ዝቅ አድርጐ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ በዚህ ምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ወቅት ስለ ሰው ልጆች ሲል በፈቃዱ ጸሎትንና ምል ጃን ማቅረቡን የሚገልጥ ሲሆን ይህም ሰለ አዳምና ስለ ልጆቹ ለመካስ የመጣ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። በክርስቶስ ካሣ ከባርነት ነጻ መውጣታችን የታወቀ ነው። አዳም በጸለየው ጸሎት ፍጹም ድኅነት ስላላገኘ እግዚአብሔር ወልድ የአዳምን ሥጋ ተዋሕዶ ዳግማዊ አዳም ሆኖ ስለሰው ልጆች ሁሉ እሱ ተገብቶ (ተወክሎ) ያቀረበው ጸሎትና ምልጃ ነው።

በዚህም በሰይጣን ምክር ተታሎ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሶ ኃይሉ ደካማ ጸሎቱ የማይሰማ ሆኖ ተፈር ዶበት በመንጸፈ ደይን ወድቆ በእግረ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አጋንንት ይጠቀጠቅ (ይረገጥ) የነበረው የአዳምን ሥጋ ተዋሕዶ አዳም በበደለው በደል ሁሉ ኢየሱስ ክረስቶስ ካሣ ከፍሎ የረከሰውን ቀድሶ ያረጀውን አድሶ የቀደመ የአዳም ክብሩን ልጅነቱን መልሶ የአዳም ልጆች ጸሎት ተሰሚ የሚያቀርቡት መሥዋዕትም ጉዳይ ፈጻሚ እንዲሆን ለማድረግ ለቤዛ ዓለም ያደረገው የቤዛነት ሥራ ነው እንጂ ማድረግ ተስኖት ኃይል አጥቶ በዕንባና በጩኸት ኃይል ወዳለው ከእርሱ በአምላክነት ወደተለየ አብ ኃይል እንዲሰጠው እንደ ነቢያት መጮኹ አይደለም።

በሌላም በኩል ወደዚህ ዓለም የመጣው ለእኛ አብነት ለመሆን ነውና «እኔን ምሰሉ» ባለው አምላካዊ ቃሉ መሠረት በመከራችን ወቅት ወደ እርሱ በምን አይነት ሁኔታ ልንቀርብ ልንጸልይ እንደሚገባን ሊያስተምረን ነው።

በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካሣ አዳም ተገፎ የነበረውን ክብርና ልጅነት ካገኘ በኋላ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳይገናኝ ለይቶት የነበረው የጠብ ግድግዳ በጌታ መሥዋዕትነት (እስታራቂነት) ከፈረሰ ወዲህ «እኛ በክርስቶስ ፈንታ ክርስቶስን መስለን እንደ ክርስቶስ እንለምናለን እግዚአብሔርም በእኛ ስብከት ልጅነትን በእኛ ጸሎት (አማላጅነት) ተድላ መንግሥተ ሰማይን ይሰጣችኋል» ለማለት በቃ 2ቆሮ.5፥20።

እንግዲህ ጌታ አንድ ጊዜ የማማለድ (የማስታረቅ) አገልግሎትን ባርኮ ከሰጣቸው በኋላ በክርስቶስ ያመኑ በቃሉ መሠረት ራሳቸውን የቀደሱ ቅዱሳን የማማለድን ሥልጣን አግኝተዋል ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ በክርስቶስ ፈንታ ዛሬ የሚያማልዱን ቅዱሳን ናቸው ጌታ ግን ተማላጅ ነው።

ማመሳከሪያ


1. አዲስ ኪዳን (በአማርኛ) በዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ በናሽናል ባይብል ፕሬስ ፊላዶልፊያ 1938 ዓ.ም.

2. ሐዲስ ኪዳን (በግእዝና በአማርኛ) በሊቃውንት ጉባኤ ታርሞ የተዘጋጀ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1975ዓ.ም.


• ይቀጥላል

## እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

(ከዲ. ተክለጻድቅ)

ዘፍ.28፥10–12።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ አባታችን ቅዱስ ያዕቆብ የአባቱን የይስሐቅን በረከት ከተቀበለ በኋላ ከላባ ልጆች መካከል ሚስት የምትሆነውን ለመሻት ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን በአደረገው ጉዞ ላይ ያጋጠመውንና የተገለጠለትን ታላቅ ምሥጢር እንመለከታለን። ቅዱስ ያዕቆብ በጉዞ ላይ ሳለ በአንድ ሥፍራ ሲደርስ መሸበት – ፀሐይም ጨልማ ነበርና በመንገድ ላይ አደረ። ሌሊቱን ግን አስደናቂ ምሥጢር ሲመለከተ አደረ። እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደሰማይ ደረሰ:- እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር። እነሆም እግዚአብሔር በላዩ ቆሞበት ነበር።» ይህን የቅዱስ ያዕቆብን ሕልም የቤተክርስቲያናችን አባቶች አምልተውና አስፍተው ተርጉመውታል።

በዚሁ መሠረት ያዕቆብ ያያት መሰላል የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ ስትሆን የተንተራሰው ደንጊያ ወላዲተ አምላክ በትንቢተ ነቢያት ጸንታ የመቆየቷና የመገኘቷ ምሳሌ ነው። መሰላሊቱ ከምድር እስከ ሰማይ መድረሷና መላእክት ሲወጡባትና ሲወርዱባት መታየቱ እመቤታችን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጸመው የእርቅ መሠረት መኾኗንና ከዚህ እርቅ በፊት ለተልእኮ መውረድ መውጣት ያቋረጡት መላእክት ተልእኮአቸውን የመጀመራቸው ምሳሌ ነው። በሌላ በኩልም ቅድመ ሥጋዌ ማለት ከአምላክ ሰው መሆን በፊት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ጸብ በድንግል ማርያም አማካኝነት መወገዱንና መላእክት ከሰው ጋር ለመዘመር ወደ ምድር መውረዳቸውን:- የሰውን ልመናና ምስጋና ለማሳረግ ወደ ላይ ወደ ሰማይ መውጣታቸውን ያጠይቃልና አባቶቻችን በሚያምርና በሚስማማ ትርጉም እንዲህ አስቀምጠውታል።

ያች መሰላል ግሩም ናት። ከሥጋዌ በፊት በሰማያት እግዚአብሔርን በማመስገን ብቻ ጸንተው የነበሩ ቅዱሳን መላእክት በኋለኛው ዘመን በሥጋዌ (በእግዚአብሔር ሰው መሆን) ተደንቀው ይህንኑ ለማብሠር እንዲወርዱና ከእረኞች ጋር «ስብሐት ለእግዚአብሔር» እንዲሉ ምክንያት ሆናለች። ሰውና እግዚአብሔር እንዲታረቁ ምክንያት ሆናለች። ምድራውያን ከሰማያዊው እግዚአብሔር ጋር እንዲገናኙ:- ሰማያውያን ከምድራውያን ጋር እንዲገናኙ አማናዊት መሰላል ሆናለች። እርሷ በርግጥ የድንግል ማርያም ምሳሌ ነበረች። ድንግል ማርያም እመቤታችንም በአዳምና ሔዋን በደል ምክንያት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ እንዲፈርስ:- የምሕረትና የሰላም ግንኙነት እንዲኖር ምድራዊው ሥጋ ሰማያዊ እንዲሆን:- መዋቲው ሰው ሕያው እንዲሆን:- ሰማያዊው እግዚአብሔር የሰውን ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ ምክንያት ሆና እግዚአብሔር ወልድ በተዋሐደው ሥጋዋ ሰውን ከፈጣሪው አገናኝታ መላእክትን ለዝማሬ ወደ መሬት እንዲወርዱ አድርጋለችና አማናዊት (እውነተኛይቱ) መሰላል እርሷ ናት።

በዚህ መንገድ ይጓዙ የነበሩት ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐናም ያፈሩት እንደአባቶቿ ሁሉ የምታስታርቀውን ቅድስት ድንግል ማርያም ነው። እርሷ ሰውንና እግዚአብሔርን የምታስታርቅ ሆናለች። ያንን አብነት አድርጎ ዛሬም አስታራቂ መሆን:- እግዚአብሔርንና ሰውን በማገናኘት የእውነተኛ ሃይማኖትና የአበው ሥርዓት መገኛ መሆን ይገባል። እንዲህ የሆነ እንደሆነ የቅዱሳን መላእክት መመላለሻና የበረከታቸው ተካፋይ የእርቅና የሰላም ባለቤት ለመሆን ይቻላል። እንግዲህ ከምድር እስከ ሰማይ የደረሰችውና እግዚአብሔር በላይዋ የተቀመጠባት መሰላል በሆነች በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የምንታመን ሁሉ ችግራችንን ለእርሷ ብንነግራት ምድራውያን ለሆንነው ለእኛ ሰማያዊ በረከትንና መፍትሔን የምታሰጠን መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። ይቆየን ✣

# መዝሙርና ምሥጢራዊ ሥርዓቱ

ዐቢይ ኃ/ጊዮርጊስ

## ማኅሌት

ማኅሌት ማለት ኃለየ – ዘፈነ፥ ዘመረ፥ አመሰገነ ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሆኖ የምስጋና መዝሙርን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ማለት ነው። የዚህም ይዘትና አፈጻጸም በአጠቃላይ አቋቋም ይባላል። አቋቋም ማለትም የመቆም ሥርዓት፥ የዜማውን ስልት የሚገልጽ ነው፥ በዚህም ውስጥ በበዓላት ቀኔ ማኅሌቱ የሚባልባቸው 10 መንገዶች አሉ።

እነዚህም

1. መቃኘት
2. መቀበል
3. መምራት
4. መመራት
5. ዝማሜ
6. ቁም ንዑስ መረግድ (በወርኃ ጾመ ሽብሸባ)
7. ዓቢይ መረግድ
8. ጽፋት (ከአመላለስ–መልስ–ወረብ) ጋር
9. ድርብ ጽፋት
10. የጭብጨባ ጽፋት ናቸው።

ለምን አሥር ሆኑ ቢባል ነቢዩ ዳዊት ወበመዝሙር ዘአሠርቱ አውታሪሁ እዜምር ለከ ማለት አሥር አውታር ባለው መዝሙር አመሰግን ሃለሁ ያለውን መሠረት በማድረግ ነው።

እነዚህም ግሩም የሆነ ምሣሌና ታሪካዊ ትርጉም አላቸው።

1ኛ መቃኘት – ቃለ እግዚአብሔርን መዘምራኑ እንዲያስታውሱትና በአንድ ቃል እንዲዘምሩት ለማድረግ ሲሆን አይሁድ ጌታን ለመያዝ ይሁዳን አመልካች አድርገው ለመፈለጋቸው ምሳሌ ነው።

2ኛ.መቀበል – የተቃኘውን ቃለ እግዚአብሔር ከቃኘው ተቀብሎ በማስተካከል መዘመር ነው፥ ትርጉሙ ግን የአይሁድ ጭፍሮች ጌታን ከይሁዳ ተረክበው ፈቃዳቸውን ለመፈጸማቸው ምሣሌ ነው።

3ኛ. መምራት – ቃለ እግዚአብሔሩን በሥርዓቱ ለሌላው ማቀበል ሆኖ ምሥጢሩ ግን ሊቀ ካህናቱ ሐና ጌታን እንዲይዙ ጭፍሮቹን ለመላኩ ምሳሌ ነው።

4ኛ. መመራት – ቃለ እግዚአብሔሩን ከመሪው ተቀብሎ ማሰማት ነው፥ ይኸውም የአይሁድ ጭፍሮች በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት ጌታችንን ይዘው መጀመሪያ ከሊቀ ካህናቱ ሐና ፊት ለማቅረባቸው ምሣሌ ነው። ዮሐ.18፥13።

ሀ. ከግራና ከቀኝ የመሪውን ቃል ማንሣታቸው ጌታን በእየተራ ተቀባብለው የፈረዱበት የቃያፋ፥ የጲላጦስና የሔሮድስ ምሣሌ ነው። ሉቃ. 23፥7። ዮሐ.28፥24።

ለ. በመጨረሻ ቃለ እግዚአብሔሩ ለመሪው ተመልሶ በእርሱው ማለቁ ነገረ መስቀሉ በሊቀ ካህናቱ ሐና ተፈጽሟልና ለዚያ ምሳሌ እንዲሆን ነው።

5ኛ. ዝማሜ፥ (ዘንግ) ከመቋሚያ ጋር ግራና ቀኝ መዝመምና ቀና ብሎ መቋሚያውን ከዜማው ጋር አስማምቶ ከመሬት ላይ መጣልና መደሰቅ ነው፥ ምሣሌው ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐና ወደ ቀያፋ ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ መመላለሱንና በቀራንዮ መሰቀሉን ማመልከት ነው። ደግሞም «መኑ ኰርአከ ተነበይ ለነ» «ማነው የኰረኰመህ እስቲ ዕወቅልን?» እያሉ በዘንግ እራስ እራሱን ደብድበውታልና ኩርዓተ ርእሱን ለማስታወስ ነው ማቴ.26፥6።

6ኛ. ቁም (ንዑስ መረግድ) በወርኃ ጾም ሽብሸባ ዝማሚውን በዘንግ ከጨረሱ በኋላ በጸናጽልና በከበሮ ብቻ በንዑስ አመታት ረጋ አድርጐ መዘመር ነው።

7ኛ. ዐቢይ መረግድ – ቁም ዜማውን ለቀቅ አድርጎ በልዩ ዜማ የሚዘመረው ነው፥ ይህ ዜማ በከበሮው አመታት በጸናጽሉም አጣጣልና አወራረድ የተለየ መልክ አለው። የአካልንም ንቅናቄ ጭምር የሚያስከትል ነው። ይህም አይሁድ በሕጋቸው 40 ሲገርፉት ረጋ ብለው ከጀመሩ በኋላ ግርፋቱን በማክበድ ተሳሳትህ መልስ እያሉ 6666 ጊዜ እንደ ገረፉት ለማስታወስ ነው።

8ኛ. ጽፋት – ከአመላለስ (ምልስ ወረብ) ጋር ቃለ እግዚአብሔሩን በዜማው እያፋጠነ በጸናጽልና በከበሮ መዘመር ነው፥ ምሳሌውም ጽፋት ማለት በጥፊ መመታት ማለት ነው፥ ጌታ በጥፊ መመታቱን ለማሰብ ነው።

ለ. ወረብ ወይም ለዘብ – (አመላለስ) የተመረገደውን በመከተል ሌላም ዐረፍተ ነገር በመጨመር ወይም በመለወጥ መልስ የተባለውን ዜማ በማስመሰል መወረብና በታላቅ ስሜትና ተመስጦ በልዩ ከበሮ አመታት በጭብጨባ (በሽብሸባ) መዘመር ነው።

ሐ. ድርብ መረግድ – በተለይ በክብረ በዓላት ቀን ወረብ ሲወረብ በርጋታ ተጀምሮ የነበረውን በማድመቅ በዐቢይ መርግድ ላይ የከበሮውን አመታትና ሽብሸባ ጠበቅ አድርጐ በመደራረብ መዘመር ነው፥ ምሳሌውም ጌታን ደጋግመው እንደገረፉትና እንደደበደቡት ማስታወስ ነው፥ ካህናቱ ግራና ቀኝ ሆነው ማስረገጣቸውም አይሁድ ከመጀመሪያው



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

እስከ መጨረሻው 340 ጊዜ ረግጠውታልና ለዚህ መታሰቢያ አድርገው ከመሆኑም ሌላ በክርስቶስ ካሣና መከራ ስቅለትና ሞት ጠላት ዲያብሎስ ተረግጦ ተጣለ ለማለት ነው።

9ኛ. ድርብ ጽፋት – በጸናጽልና በዜማው ቃና (ጉሮሮው) ከተራው ጽፋት በላይ በክበሮ አመታት ለየት አድርጐ መዘመር ነው። ምሳሌውም አይሁድ ጌታን ደጋግመው በጥፊ እንደመቱት (እንደጸፉት) ለማስታወስ ነው።

10. የጭብጨባ ጽፋት ከተራው ጽፋት ጋር በጉሮሮው (በአጣጣሉ) በመጠኑ ፈጠን ፈጠን አድርጐ በጸናጽል ፈንታ እያጨበጨቡ በከበሮ መዘመር ነው፣ ምሳሌውም ከላይ በ8ና በ9 ተራ ቁጥሮች ላይ እንደተገለጸው ነው።

ይህን ከልብ ከተረዳን ለያሬዳዊ ዜማ ማጐልመሻ የሚሆኑ ንዋያተ ቅድሳትና ሁኔታዎች ሁሉ ከየት እንደመጡና ለምን እንዳስፈለጉ እንመለከታለን።

1ኛ. ካህናት በማኅሌት ሲያመሰግኑ ለመሣሪያነትና ለመደገፊያ አድርገው መቋሚያ ይይዛሉ። ይህን መቋሚያ በመጀመሪያ አባ አንጦንስ የሠሩት ሲሆን ምሳሌውም እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው የትእምርተ መስቀል ተስፋ ነው። ስለሆነም አባ አንጦንስም፣ ቅዱስ ያሬድም በምስጋና ጸሎት ጊዜ ይህ እንዲያዝ አደረጉ፣ ይህም ልቦ ወለድ ሳይሆን ሙሴ እስራኤልን ባሕረ ኤርትራን ባሻገረ ጊዜ ተአምራት ያደረገው በዚህ ትእምርተ መስቀል ነው። ይህን ትእምርተ መስቀል ሙሴ በእስራኤል መካከል «ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ሰቡሐ ዘተሰብሐ» በማለት አመስግኖበታልም ብለው ነው፣ ስለዚህ በሥርዓቱ ቤተክርስቲያናችን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ትእምርተ መስቀል መያዝ ግዴታው ነው። ቢቸግረው እንኳ አፈር ቢኖር መስቀል ስሎ፣ ድንጋይ ቢሆን በምራቁ አመሣቅሎ እንዲጸልይ ያዛል በሥርዓተ ቤተክርስቲያናችንም መቋሚያ መያዝ የክርስቶስን መከራ ለማሰብ ነው ብለው በጐጃም ክፍለ ሀገር መሬት ዋፋ በምትባል ስፍራ ይኖሩ የነበሩ መምህር ዐፅቀ ድንግል የሚባሉ የአጼ ልብነ ድንግል ወንድም መቋሚያ መያዝ የክርስቶስን መከራ ማሰብ መሆኑን አምነው በተደገፉት ቁጥር እንዲዋጋቸውና የክርስቶስን መከራውን እንዲያስታውሱ 15 እሾህ የፈሰሰበት መቋሚያ አሠርተው ነበር ይባላል። ይህንም አርአያ አድርገው በሸዋ ክፍለ ሀገር በመንዝ የነበሩት መነኮሳት ይሠሩበት ነበር እየተባለ ይተረካል። የክርስቶስን መከራ በማሰብ ከመከራ ሥጋ፥ ከመከራ ነፍስ እንዲዳንበት አምነው ስሙን ተአምኖ ብለውታል።

2ኛ. እስራኤል ባህረ ኤርትራን በየብስ ሲሻገሩ የሙሴ እኅት ማረያም ከበሮ ይዛ ከእስራኤል መካከል እግዚአብሔርን ታመሰግን ነበረች፥ አሁንም በካህናት መካከል አንዱ መቋሚያ ይዞ ሌላው ከበሮ እየመታ ማመስገናቸው ስለዚህ ነው፥ የከበሮ ግራና ቀኝ መመታት ግን ለመዝሙሩ ውበትና ለመስጠት ሆኖ ዋና መልእክቱ ግን አይሁድ ጌታን በጥፊና በአይበሉባ አክረው እንደመቱት ለማሰብ ነው።

3ኛ. በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚታየው መዘምራኑ ካህናቱ በቀኝ እጃቸው ጸናጽል ይይዛሉ ይህም በቀድሞው ዘመን ግብጻውያን እግዚአብሔርን ያመሰግኑበት ስለነበርና በመዝሙረ ዳዊትም ስለተጠቀሰ ነው። መዝ.150፥5።

ይህም ምሣሌ አለው፣ ላዩ ቀስተ ደመና ይመስላል እንዲት ቢሉ እሰይም ቀስተየ በውስተ ደመና ከመ ኤይማስና ለምድር ዳግመ በማየ ኅይህ ዘፍጥ.9፥11–20። ብሎ ስላሳየ ነው፣ አራት ዘንጐች አሉት የአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ምሣሌዎች ቅጠሎች የፍጥረተ ዓለም ምሣሌዎች ናቸው። ከአራቱ ባህርያት የተፈሩ ሰዎችን እንስሳትንም አላጠፋም ብሎ ለኖሕ ቃል ኪዳን ገብቷልና ካህናትም በጸናጽል ሲያመሰግኑ ኪዳነ ኖሕን አሰብና በኃጢያታችን አታጥፋን ብለው ማሳባቸው ነው።

ደግሞም ጸናጽል ያዕቆብ ብሎዛ ያየው መሰላል አምሣል ነው። ግራና ቀኝ ያሉት ዘንዶች (ጋድሞች) የመውጫ መውረጃው ምልክቶች ናቸው። በእነዚህም የተንጠለጠሉት ቅጠሎች ይወጣ ይወርዱ የነበሩት መላእክት አምሣል ናቸው። ድምጻቸው የምስጋናቸው ድምፅ መታሰቢያ ነው። ደግሞም በቀኝና በግራ የቆሙት የብሉያትና የሐዲሳት የሁለቱ ዓበይት ሕግጋት (ጋድሞች የፍቅረ እግዚአብሔርና የፍቅረ ቢጸ የሁለቱ ቃላት፣ በእኒህ የተንጠለጠሉት በሌሎች መጻሕፍት ያሉት) ቅዱስ ወንጌል» ወበ ዝንቱ ክለኤቱ ተእዛዛት ተሠቅሎኰሌ ኦሪት ወነቢያት» እንዳለ ብለው አሠርተውታል። በሽብሸባ ጊዜ መቋሚያ እና ጸናጽል ይዘው ወደ ኋላና ወደፊት፣ ወደግራና ቀኝ ማለታቸው መስቀል ነውና ማማተብን ያመለክታል። ማማተብ መጀመሪያ አይደለምን? ሲሉ በተናገሩ ቁጥር ማማተብ እንደሚገባ ተወስኖአል። ነገር ግን ካህናት በቤተክርስቲያን ለማገልገል በቆሙ ጊዜ መቋቋሚያና ጸናጽል ሲይዙ የክርስቶስን መስቀል መሸከም ማሰብ ይገባቸዋል። ደግሞም ጌታችን ክብር ይግባውና መስቀሉን ተሸክሞ ሲሄድ አይሁድ ወገቡን በገመድ አሥረው ገመዱን በአራት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ወገን አትርፈው ከፊት ያሉት ጉትተው ያዳፉታል፥ ይወንጥሉታል። ከኋላያሉትም ጉትተው ጻፉታል። የቀኝና የግራዎቹም እያወዛወዙ ይወንጥሉት ያደክሙት ነበር። ለዚህም መታሰቢያ እንዲሆን የኢትዮጵያ ቤ/ክርስቲያን ካህናት ከወገባቸው በላይ ቀሸመሪ (ዋንግ ድርብ) ታጥቀው ሽማቸውን (ቋዳቸውን) በቀሸመሪ አስረው ወደኋላው ተርፎ ለነበረው ገመድ መታሰቢያ እንዲሆን ቋዱን ወደኋላ ያተርፋሉ ወደፊትም ተርፎ ለነበረው ቀሸመሪውን ወደፊት አትርፈው ወደቀኝና ግራ ተርፎ ለነበረው ገመድ መታሰቢያ ቋድን በሁለት ወግኑ ሽማቸውን አትርፈው አንዱን ወገን ከመቋሚያ ጋር ይይዙታል።

አንዱን ወገን ወትርፈው በጐናቸው በኩል ያተርፋሉ ከዚህም በኋላ ደፋ ቀና ወደቀኝና ወደግራ እያሉ በዜማ ያመሰግናሉ። ጌታ ደፋ ቀና ማለቱን ለማሰብ ደፋ ቀና እያሉ ወደ ቀኝና ወደግራ መወንጠሉን ለማሰብ ደፋ ቀና እያሉ ወዲያና ወዲህ እያሉ ትእምርተ መስቀል የሆነ መቋሚያቸውን ተሸክመው ትእምረ መስቀል (ኵዳን) የሆነ ጽናጽናቸውን ይዘው ለአክሊለ ሦክ መታሰቢያና ምሣሌ የሆነ ጥምጥማቸውን ጠምጥመው ሲያገለግሉ ይታያሉ። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ይህንን ለጊጥና ለታይታ የሚያደርጉት ቢኖር ከትዕቢት ይቆጠራልና መጠንቀቁ ያሻል።

1ኛ. አሁንም በዕለተ ዓርብ ጌታችን ከሊቶስጥራ እስከ ቀራኒዮ ድረስ ያን እጅግ ከባድ የሆነ መስቀል ተሸክሞ ሲጓዝ ከድካሙ የተነሣ መስቀሉን አንዳንድ ጊዜ ከመሬት ያሳርፈው ነበር። የኢትዮጵያ ካህናትም ይህንን ለማሰብ አንዳንድ ጊዜ መቋሚያቸውን እንደ ማማተብ አድርገውና ለቃለ እግዚአብሔር (ለዜማው) ምልክት አድርገው ከተከሻቸው አውርደው በመሬት ያሳርፉታል። አንዳንዴም ለሌላው ሰው ይሰጡታል። ደግሞም በዕለተ ዓርብ መድኃኒታችን በሰውነቱ ከመስቀሉ ክብደት፥ ከመንገላታቱም ብዛት የተነሣ ፈጽሞ በደከመ ጊዜ ያሳብነውን (የፈለገነውን) ነገር ከአሰብነው ስፍራ አድርሰን ሳንፈጽም ይሞትብናል፥ ብለው መስቀሉን ለሌላ አሸከመው ባዶውን እያጣደፉ እያዳፉ ይነዱት ነበር። ለዚህም መታሰቢያ ካህናቱ ቀስ ብለው የዘመሩትን ዜማ በፍጥነት ይናገሩታል መልሰውም ይጀምሩታል ተእምርተ መስቀል የሆነ መቋሚያቸውን ከትከሻቸው ላይ አውርደው ለሌላ ሰው ይሰጡታል። ቃለ እግዚአብሔሩን፥ ዜማውን ወዲህ ወዲያ እያሉ (እየተመላለሱ) በመዘመር በእጃቸው ያጨበጭባሉ፥ ይህም ለደስታም ሆነ ለሐዘን ለመከራ ምልክት ይሆናል ሕዝ.11፥11–17።

ካህናቱ እያጨበጨቡ መዘመራቸው ለምንድነው? ቢሉ መድኃኒታቸው በዓፀኑበት መከራ እጅግ ተገርሞና አዝኖ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ.23፥31 እንደገለጸው «በዝርጠብ ዕፅ ከመዝ–ዘገብሩ አፎኑመ እነጋ ይከውን በይቡሰ ማለት በዚህ እርጥብ እንጨት (መለኮት) በተዋሐደው ዕውነት ይህን ያህል ጸዋትዎ መከራ ከአብዙ፥ በደረቅ ዕንጨት ማለት በሩቅ ብእሲ ተራ ሰውማ እንዴት ያደርጉበት ይሆን?» ብሎ እጁን በእጁ እንደመታው (እንደጻፈው) ለማሰብ ነው።

5ኛ. መድኃኒታችን የተቀበለውንና የሚቀበለውን ጽዋትዎ መከራ ከልብ ተመልክተው የእስራኤል ሴቶች እጅግ አዝነው ያለቅሱ ነበር። ጌታችን አታልቅሱ ብሎ አፍናንቶአቸዋል። በዚህን ጊዜ ሰሎሜ የምትባል አንዲት ሴት የድካሙን ጽናት የላቡን ብዛት አይታ ለላቡ መጥረጊያ በእጇ ያለውን መሐረብ ሰጠችው። ጌታችንም በመሐረቡ የፊቱን ላብ በጠረገበት ጊዜ መልኩ በመሐረቡ ላይ ተሳለ። መልሶ ሰጥቷት ለዘላለም ለመልኩ መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል።

ስለሆነም የኢትዮጵያ ካህናት በአገልግሎታቸው ጊዜ በጣታቸው መሐረብ ይይዛሉ። ከዚህም ሌላ ከላይ እንደገለጽነው መድኃኒታችን መስቀል ይዞ ሲንገላታ እየተከተሉ የሚደረግበትን ግፍ እያዩ ያለቀሱለት ለነበሩ ሴቶች መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የኢትዮጵያ መእመናት ሴቶችም በቤተክርስቲያን ለጌታም ሆነ ለእምቤታችን በዓል እየተገኙ እልል ይላሉ ለምን ቢሉ ይህ ቃል በዘመናቸው ለደስታም ሆነ ለኀዘን ያገለግል ስለነበሩና በዚያ ጊዜም የነበሩት ሴቶች ያሉት ይህንኑ ቃል ስለሆነ ነው። ✣

«ጠባዩን ያጸናና (ያልለዋወጠ) ከሁሉ ጋር የተስማማ ሰው ምክሩ የቀና ፍቅሩ የጸና ይሆናል። ተወዳጅነቱም በብረት ላይ እንደተቀረጸ ምስል በሚወዱት ሰዎች ልብ ውስጥ ተቀርጾ ይኖራል።

የሰውየው ጠባይ አንድ ጊዜ ደረቅ አንድ ጊዜ ልስልስ የሆነ እንደሆነ ምክሩ ተለዋዋጭ ሐሳቡ ወጭ ወራጅ ሆኖ ከዋለበት የማያድር ካደረበት የማይውል ግብዝና ፍቅረቢስ ይሆናል። ይህም ማለት ቶሎ እንደመውደድ ቶሎ ይጠላል ማለት ነው።

ተሠርቶ ተቀጥቶ ያደገ ብልህና አስተዋይ የሆነ ሰው ግን ወዳጅን ያየው እንደሆነ ዓይኖቹን ከርሱ ዞር ያደርጋል ልቡን ቶሎ አይሰጠውም ቢያየውና ልቡን ቢሰጠውም ቅሉ ቀስ እያለና ምክሩን በመስጠት እያደረገ ደስ ያሰኘዋል። በእንደዚህ ያለ ፍቅር መካከል መነቃቀፍና መነዋወር አይኖርም» ጋሊኖስ።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

ጾም ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል ማለት ነው። ወይም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጐመጅውን ነገር መተው ማለት ነው። ሃይማኖት ባለበት ቦታ ሁሉ ጾም አለ። ጾም ከሃይማኖት ጋር ዘላለማዊ ዝምድና አለው። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ አለው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት ወራት እህል ውኃ ባፋቸው አይገባም ነበር። ዘጸ.34፥28። በኃጢአት ብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ቁጣው የሚበርደው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር። ዮና.3፥5–10።

በአዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሠራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው የሥራ መጀመሪያ አድርጐ የሠራው ሕግ ነው። ማቴ.4፥2፤ ሉቃ.4፥2። መድኃኒታችን በስስት፥ በፍቅረ ንዋይና በትዕቢት የሚመጣብንን ጠላት ዲያብሎስ በጾም ድል እንደምናደርገው አሳየን። አርአያ ሆነን ይህም ብቻ ሳይሆን በቁራኝነት አብሮ የሚኖር ርኩስ ሰይጣን እንኳ በጾም የሚወገድ መሆኑን መድኃኒታችን ተናግሯል። ማቴ.17፥21፤ ማር.9፥2። በዚሁ መሠረት በጾም ከሰይጣን ቁራኝነት መላቀቅ ለእኛ ታላቅ ጸጋ እና ኃይላችን ነው።

ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም ከመንፈስ ቅዱስ በየጊዜው ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እያሉ ነበር። የሐዋ.13፥2። ይህም የሚያመለክተው ጾምና ጸሎት የማይነጣጠሉ መሆናቸውንና ስንጾም ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ እንደሚቀርበን ነው። በጾም የተዋረደ እና ለጸሎት የተጋ ሰውነት ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ የተዘጋጀ በመሆኑ እግዚአብሔር ያዝዘናል እኛም እንታዘዛለን። ለስብከተ ወንጌል የሚያገለግሉ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሾሙትም በጾምና በጸሎት ነበረ። የሐዋ.13፥3፤4፥25። እነ ቆርኔሌዎስ ያላሰቡትን ክብር ያገኙት በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማልደው ነው። የሐዋ.10፥20። ጾም እንኳን የጠበቅነውንና ያሰብነውን ቀርቶ ያላሰብነውንና ያልጠበቅነውን ፈጽሞም የማይገባንን ጸጋና ክብር የሚያሰጥ ነው።

## እውነት ጾም አይጠቅምም

የጾም ሃይማኖታዊ ትርጉም ፈጣሪን መለመኛ ከኃጢአት ቁራኛ መላቀቂያ መሣሪያ ስለሆነ በጾም ወራት ለአምሮት ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኃይል ተቃራኒ የሆኑ ሥጋዊ ፍትወትን የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦችን ሥጋንና ቅቤን ወተትና ዕንቁላልን ማራቅ ታዟል። ባልና ሚስትም በአንድ ምንጣፍ አይተኙም። 1ቆሮ.6፥5። «ነዳያንን ለመመገብ የሚጾም ነውድ ነው ክቡር ነው።» እንደተባለ ጦመኛው ለምሳው ወይም ለእራቱ ያለውን ወጭ ነዳያንን እንዲረዳበት ለድኩማን ድርጅት ቢሰጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ነዳያን ቢመጸውት ጦሙን የበለጠ ክርስቲያናዊ ያደርገዋል።

ጾም የታሪክ ድርጊቶችን እያስታወሱ ከኃጢአት ለመንጻት ስለራስ የታሰበውን ለነዳያን በመስጠት የሚጾም መሆኑን መረዳት አለብን። ጾም ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም ይጾማል። በዲዲስቅልያ 1፥5። ለሚያሳድዱህ ጹምላቸው።» ተብሏል። በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም በጾም ወራት ማስታወስና ስለ እነርሱ መጸለይ ይገባል። ቅ/ያሬድ ክፉ ከማየት ክፉ ከመናገር እና ክፉ ከመስማትም ጭምር መጾም እንደሚገባ ተናግሯል።

በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ባሕልና ትውፊት መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ስለሆነች የጾም ሕግና ሥርዓት አላት። እነዚህም ሰባት የጾም ወራት ናቸው።

1ኛ. የመጀመሪያው ጾም ዓቢይ ጾም ወይም ሁዳዴ ይባላል ጌታ ከተጠመቀ በኋላ የጾመው የአርባ ቀን ጾም ነው። ማቴ.4፥1። ምእመናን ጌታቸው ያደረገውን ተከትለው ይጾሙታል። ዓቢይ ጾም ስምንት ሳምንታት 58 ቀኖች አሉት ከእነዚህም ቀኖች ውስጥ ሰባት ቅዳሜና ስምንት እሑዶች አሉት አሥራ አምስት ቀን ማለት ነው። ከጥሉላት እንጂ ከእህል ውኃ ስለማይጦሙ የጦሙ ወራት አርባ ቀን ብቻ ነው። በሌላ መልኩ የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል የመጨረሻው ሳምንት ደግሞ ሰሙነ ሕማማት ይባላል።

ሕርቃል በ614 ዓ.ም. የቢዛንታይን ንጉሥ ነበረ። ይህ ሳምንት በስሙ የተጠራበትም ምክንያት በዘመኑ ፋርሶች ኢየሩሳሌምን ወርረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር። ምእመናን ተዋግተህ አስመልስልን አሉት እሱም «ሐዋርያት ነፍስ የገደለ መላ ዘመኑን ይጹም ብለዋል ስለዚህ ይኸንን የዕድሜ ልክ ጾም ፈርቼ እንጂ ደስ ይለኛል ሲል መለሰላቸው። እነርሱም ያንድ ሰው ዕድሜ ቢኖር ሰባ ሰማኒያ ዘመን ነው እኛ ተካፍለን እንጾምልሃለን ስላሉት ፋርስ ዘምቶ መስቀሉን ከእነዚያ ነጥቆ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ምእመናንም አምስት አምስት ቀን ተካፍለው ጹመውለታል። መታሰቢያም እንዲሆን ይህን የጾም ሳምንት በቀኖና ውስጥ አስገቡት ታሪኩ የመስቀል ፍቅር የተገለጠበት ታሪክ ነው። የመጨረሻው ሳምንት ሕማማት ነው። ሐዋርያት የጌታችንን መከራና ሞት እያሰቡ የጦሙት ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ከዓቢይ ጾም ጋር እንደመርገፍና እንደ እጅታ ስለተያያዘ ከዓቢይ ጾም ይቆጠራል። ዓቢይ ጾም መባሉ የጌታ ጾም ስለሆነና ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች ድል የተነሡበት ድል የሚነሡበትም ጾም ስለሆነ ነው።

2ኛ. የሐዋርያት ጾም (የሰኔ ጾም) ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከመሄዳቸው በፊት የጾሙት ነው። መምህራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ጾምን የሥራ መጀመሪያ አድርጐ ነበርና። ሐዋርያት ይኸንን ጾም እንደ ሚጾሙት ጌታ አስቀድሞ ተናግሮት ነበር። «ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።» ማቴ. 9፥15። ምእመናን አባቶቻቸው ሐዋርያትን ምሳሌ አድርገው ከጰራቅሊጦስ በበነጋው ጀምረው ይጾሙታል።

3ኛ. የፍልሰታ ጾም (ጾመ ማርያም) የፍልሰታ ጾም ከነሐሴ 1–15 ነው በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚተረከው እመቤታችን ያረፈችው ጥር 21 ቀን ነው በግምት በ50 ዓ.ም. ገደማ ሐዋርያት በድኗን ሊቀብሩ ወደ ጌቴሴማኒ ይዘዋት ሲሄዱ አይሁድ በተኗቸው። በዚህን ጊዜ መላእክት የእመቤታችንን አስከሬን ወስደው በገነት አኑረውታል። በስምንተኛው ወር በነሐሴ አስከሬኗን እንደገና ከጌታ ተቀብለው በጸሎትና በምህላ ቀበሯት። በዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ አልነበረም። ቅ.ቶማስ ከሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ያገኛታል። በዚህ ጊዜ ትንሣኤዋን ሌሎች ሐዋርያት አይተው ለእሱ የቀረበት መስሎት ተናዶ «በፊት የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ አሁን ደግሞ የአንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀርቼ ነው» ብሎ ከደመናው ሊወረወር ቃጣው። በዚህ ጊዜ እመቤታችን ቶማስን አጽናናችው። ከርሱ በቀር ትንሣኤዋን ሌላ እንዳላየ ነገረችው ለምስክር እንዲሆነውም ሰበኗን ሰጥታው አረገች። ቶማስ ሐዋርያት ወደአሉበት ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ እመቤታችንን እኮ ቀበርናት ብለው ነገሩት። እሱም አውቆ ምሥጢሩን ደብቆ አይደረግም «ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር» አላቸው። ለማሳየት መቃብር ሲከፍቱ አጧት። በዚህ ጊዜ እሱ እመቤታችን ተነስታ አርጋለች ብሎ ሁኔታውን ተረከላቸው። ለምስክር ይሁንህ ብላ የሰጠችውንም ሰበኗን አሳያቸው። ሰበኗን ለበረከት ቆራርጠው ተከፋፍለው ወደየሀገረ ስብከታቸው ተበታትነዋል። በዓመቱ ትንሣኤሽን ቶማስ አይቶ እንዴት እኛ ይቅርብን ብለው ከነሐሴ 1 ጀምረው ሱባዔ ገቡ በነሐሴ 14 ቀን ትኩስ በድን አድርጐ አምጥቶ ሰጣቸው ከቀበሯት በኋላ በ16 ተነስታለች። በዚህ ቀን ጌታ ቀድሶ እመቤታችንም በልጅዋ እጅ ቆርባለች። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሐዋርያት ቤተክርስቲያን የእመቤታችን በረከት ለማግኘት ትጾማለች።

4ኛ. ጾመ ነቢያት ከኅዳር 15 እስከ ታህሣሥ 28 ቀን ያለው ነው። ይህን ጾም የምንጾመው ነቢያት በየዘመናቸው ስለመሲህ መምጣት በናፍቆት በመጠባበቅ ይጾሙ ይጸልዩ ስለነበር የእነርሱን አርአያ ተከትለን የክርስቶስን ልደት ከማክበራችን ቀደም ብለን ይህን ጾም እንድንጾም በሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሥርዓት ተሠርቷል። አጀማመሩ ስንክሳር መንፈቀ ኅዳር ስለሚል ጾሙ ኅዳር 15 ቀን ይጀምራል «ወጥንተ ዚአሁ መንፈቀ ኅዳር ወፋሲካሁ በዓለ ልደት» መጀመሪያው የኅዳር እኩሌታ ፋሲካው በዓለ ልደት ነው።

5ኛ. ጾመ ገሀድ ግልጥ ማለት ነው። አንድም ጋድ ይለዋል ለውጥ ማለት ነው። ገሀድ የጥምቀት ብቻ ነው ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ በሚውልበት ተለውጦ ይጾማሉ በነሱ ለውጥ ጥምቀት የሚውልባቸው ረቡዕና ዓርብ የፍስክ ቀን ሆነው ይከበራሉ። ገሀድ የረቡዕና የዓርብ ለውጥ ነው ብለናል ነገር ግን በሌላም ቀን ቢውል የጥምቀት ዋዜማ ይጾማል። ይኸውም ይሁን ሲጾም አንድ ጊዜ ሲቀር እንዳይረሳ ነው ገሀድ ለጥምቀት ብቻ ቢሆንም በልማድ ግን የልደትንም ዋዜማ ገሀድ እንለዋለን። ነገር ግን ልደት የሚውልባቸው ረቡዕና ዓርብ የፍስክ ቀን ሆነው እንዲከበሩ ቢታዘዝም በዋዜማው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስ ከጾመ ነቢያት ጋር የተያያዙ ስለሆኑ መጾማቸው የግድ ነው። ጾመ ነቢያትን የማይጾሙ ሰዎች ግን ሲበሉ ቆይተው ዋዜማውን ብቻ ገሀድ ነው ብለው ይጾሙታል።

6ኛ. ጾመ ነነዌ (ዩና.3፥1–10) ይህ ጾም የሦስት ቀን ጾም ነው የቤተክርስቲያን አባቶች ይህን ጾም የወሰኑት የነነዌ ሰዎች በጾምና በጸሎት ከመዓት ከጥፋት እንደዳኑ ምእመናንም በጾምና በጸሎት ከፈጣሪያቸው ምሕረትና በረከት እንዲያገኙ በማለት ነው። የነነዌ ሰዎች ንስሐ ለሚገቡ ሰዎች አብነት ናቸውና።

7ኛ. ረቡዕና ዓርብ ረቡዕን የምንጾምበት ምክንያት የአይሁድ ሸንጐ ጌታን ዓርብ ዕለት ለመስቀል የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላለፉበት ዕለት ስለሆነ ነው። መድኃኔዓለም ለሰው ልጆች ሲል የተወሰነበትን የሞት ውሳኔ ሁልጊዜ በማስታወስ ክርስቲያኖች በዚህ ዕለት እንዲጾሙ ታዟል። ዓርብም እንደሚታወቀው ጌታ የተሰቀለበት የሞተበት ብዙ ዘመን ሲጠበቅ የነበረ ተስፋ የተፈጸመበት ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በጾምና በጸሎት



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ሲታወስ ይኖራል። (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሚለው ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ የተወሰደ።)

ጾም ወደ እግዚአብሔር ለተመለሰ ሕዝብ ምልክት ነው። «አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ።» ኢዩ.2፥12 «በጽዮን መለከትን ንፉ ጾምንም ቀድሱ። ጉባኤውንም አውጁ» ኢዩ.2፥15። አዳም ከማዕረጉ የተዋረደው በመብል ምክንያት ነው ዘፍ.3፥1–24። ከይሁዳ ወደ ቤቴል ተልኮ የነበረው የእግዚአብሔር ሰው የተቀጣው አትብላ የተባለውን በመብላቱ ነው። 1ነገ.13፥1–34። በአስቴር ዘመን አይሁድ ከእልቂት የዳኑት በመጾማቸው ነው። አስ.4፥16–17። ጸሎት ከጾም ጋር ሲተባበር መልካም ነው። «ስለዚህም ነገር ጾምን ወደ እግዚአብሔርም ለመንን እርሱም ተለመነን። «ዕዝ.8፥23። ሥጋዊ ጉልበትን በጾም ማድከምና መንፈስን ማበረታታት ቅብአትነት ካላቸው ሥጋዊ ምግቦች መከልከል ተገቢ ነው። «ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ። ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ» መዝ.108፥24። ሠለስቱ ደቂቅ እና ዳንኤል የቤተ መንግሥትን የድሎት ምግብ ንቀው በጥሬ እና በውኃ ተወስነው በመጾማቸው ፊታቸው አምሮ ሥጋቸው ወፍሮ ተገኘ እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ ዕውቀትን እና ማስተዋልን ሰጣቸው። ዳን.1፥8–21። ለመብል ለመጠጥ መገዛት መንፈሣዊውን ሕይወት ማርከስ ነው። «ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ» ዳን.1፥8። ሦስቱ ወጣቶች ወደ እሳት ዳንኤል ደግሞ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ቢጣሉ ሁሉም ዳኑ። ዳንኤል በጾሙ ወራት ለአምሮት ለቅንጣት ከሚበሉ ምግቦች ይከለከል ነበር። «እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርሁ። ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም። ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም። ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት (ቅቤ) አልተቀባሁም።» አለ ዳን.10፥2። የሥጋን ምኞት የዓይንን አምሮት ማሸነፍ እንዲህ ነው። ለእግዚአብሔር ሰዎች ጮማቸው፥ ማራቸው እንጀራቸው፥ ወተታቸው የእግዚአብሔር ቃል ነው።» አድምጡኝ በረከትንም ብሉ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው። ጆሮአችሁን አዘንብሉ ወደ እኔም ቅረቡ ሰውነታችሁም በሕይወት ትኖራለች። »ኢሳ.55፥2። «ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ» መዚ 118፥103። ነቢዩ ሕዝቅኤልም የእግዚአብሔር ቃል በአፌ ውስጥ እንደማር ጣፈጠኝ ብሏል። ሕ.3፥3። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» በማለት ሰይጣንን አሳፍሮታል። ማቴ.4፥4። እኛም ዛሬ በጾም ወራት ብሉ የሚሉንን እንዲህ ልናሳፍራቸው ይገባል። በዚህ በመጨረሻው ዘመን መስቀልን የሚጠሉ ማለትም በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ቤዛነት የሚንቁ መስቀልን የማያከብሩና የማይሳለሙ ነውር ኃጢአት ክብር የሚመስላቸው አሳባቸው ምድራዊ የሆነ ሆዳቸውን ስለሚያመልኩ አይጾሙም ፊል.3፥18።

ዋናው ነገር ጾም እንጂ መብል ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም መብል ከእግዚአብሔር ዘንድ ግዳጅን አይፈጽምም ብንበላ የምናተርፈው ባንበላ የሚጐድልብን ነገር የለም። 1ቆሮ.8፥8። ቅ.ጳውሎስ «ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን አይጠቅምም ሁሉ ተፈቅዶልኛል። በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሰለጥንብኝም።» ብሏል። 1ቆሮ.6፥12። እንግዲህ የማይጠቅመውን ነገር መተው ብልህነት ነው። በዕብራውያን መልእክቱም «ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ት/ት አትወሰዱ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና።» ብሎናል ዕብ.13፥9። በጊዜአችን ጾም አይጠቅምም የሚለው እንግዳ ት/ት በመሆኑ በዚህ አንወሰድ። «የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና እንደዚህ አድርጐ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው።» ሮሜ.14፥17። ይህ የሚያስተምረን የእግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ እንደማትወረስ ነው። አንድም ቢፈጽሟት መንግሥተ ሰማያትን የምታወርስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ፍቅር ሰላምና እምነትን እንጂ መብልና መጠጥን አትሰብክም ማለት ነው አንድም በመብል በመጠጥ ለጸና ሰውነት መንግሥተ ሰማያት የተባለች ወንጌል አትስማማውም ማለት ነው። ቅዱሳን ሰዎች እስከ ዘላለሙ በሰዎች ዘንድ የሚመሰገኑት በጾምና በጸሎት ተወስነው ሰውነታቸውን ለመብል ሳይሆን ለክርስቶስ በማስገዛት ደስ በማሰኘታቸው ነው።

ወገኖቼ ጾም አይጠቅምም ብለን ለመብል ለመጠጥ ከምንጓጓ ይልቅ ብሉ ተብለን የታዘዝነውን የክርስቶስን ሥጋ እንብላ ደሙንም እንጠጣ ሕይወት ይሆነናል። ዮሐ.6፥53። አንዳንዶች ዛሬ አባቶች ማቅ ለብሰው አመድ ላይ ተኝተው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የሠሩልንን ሥርዓት በመናቅ በፈቀድኩት ጊዜ መጾም እችላለሁ ይላሉ። ዳሩ ግን መንፈሳዊ ሕይወት እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚጓዙበት ሰፊ ጐዳና ሳይሆን ጠባብ ነው ማቴ. 7፥13። እንኳን ለመንፈሳዊው ሥርዓት ለሥጋዊው ለዓለማዊው ሥርዓት እንኳን እንድንገዛ ታዝዘናል። «ስለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ።» ጴጥሮ.2፥13። እንግዲህ በጾም በጸሎት በስግደት በምጹዋት እንድንጸና የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# አምላኩ የቀረበው ማነው?

ዘዳ.4፥1–8። ከባሮክ

«አምላኩ ወደ እርሱ የቀረበው ታላቅ ሕዝብ ማነው?» የሚለውን ቃል የተናገረው ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ ነው። ሙሴ እስራኤላውያን በምድረ ግብፅ በባርነት ግዞት በመከራ ይሰቃዩ በነበረበትና ከአይሁድ ወገን የሆነ ሁሉ እንዲገደል የፈርዖን አዋጅ በጸናበት ጊዜ ነበር የተወለደው። በዚህ አዋጅ ምክንያትም በቅርጫት ተከቶ በባሕር ላይ የተጣለ ነበር። ዘፍ.2፥1–ፍጻሜው። ይሁን እንጂ ሰው የናቀውን መምረጥ ሰው የጣለውን ማንሳት ልማዱና የባሕርይ ገንዘቡ የሆነው እግዚአብሔር ሙሴን ከቅርጫት አውጥቶ በፈርዖን ቤት እንዲያድግ አደረገው።

ያልተለየውና ከተጣለበት ያነሣው እግዚአብሔር ለሕዝቡ መሪ አድርጎም ሾመው። ዘጸ.3፥6። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራትም ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ። ይህን በባዕድ ሀገር በግዞት መከራ ተጠርቆ የሚሰቃየውን ሕዝብ ሲመራ እግዚአብሔር ልበደንዳናውን ፈርዖንን ያሳፍር ዘንድ በሙሴ እጅ ብዙ ድንቅ ተአምራትን ያደርግለት ነበር። ከዚህ ሌላ ከሕገ እግዚአብሔር እየተለዩ፣ በሚገባ መመላለስ ተስኖአቸው ፈጣሪያቸውን ያሳዘኑትን እሥራኤላውያን በተደጋጋሚ ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቅ ኖሮአል።

ነቢዩ ሙሴ ሕገ ኦሪትንና ታቦተ ሕጉን ከእግዚአብሔር ተቀበሎ ከደብረሲና ሲወርድ የጥጃ መልክ ያለው ጣዖት ሠርተው አምልኮተ ባዕድን ጀምረው ለጣዖታቸው ሲሰግዱ በደረሰ ጊዜ እጅግ አዝኖ እያለ ከፈጣሪው የለመነው ነገር ቢኖር እርሱ ጠፍቶ ሕዝቡ ግን ይቅርታን እንዲያገኝ ነው። በሞቱ ለእሥራኤል ሕይወትን የለመነ ደገኛ መንፈሳዊ መሪ ነበር። ከዚህ ጋር ለሕዝበ እሥራኤል የሃይማኖት የሥርዓትና የሕግጋት መምህርና አባት ሆኖ ከግብፅ እስከ ዮርዳኖስ ወንዝ አፋፍ ሲመራቸው ነበር። እግዚአብሔር የሰጣቸውን የሕይወት ሕግና የአምልኮ ሥርዓት የአባቶቻቸውንም ሃይማኖት እንዲጠብቁ እንዳይጨምሩበትም እንዳይቀንሱለትም፤ የተሰጣቸውን እንዲያጸኑ። ቢጠብቁት የተዘጋጀላቸውን (ምድረ ርስታቸውን) እንደሚወርሱና በእግዚአብሔር ፊት በሕይወት እንደሚኖሩ ያስተምራቸው ነበር። (እውነተኛና በእግዚአብሔር የተመረጠ መምህር ነውና በሞገስ ያስተምራቸው ነበር።)

በተአምራት የተጠራውና የአሕዛብ መምህር እንዲሆን የወንጌል የክብር ዕቃ ሆኖ የተለየው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለዕብራውያን በጻፈው መልእክት የተናገረው ከዚህ ከሙሴ አነጋገር ጋር አንድ ዓይነት ነው «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን (አበውን) አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው መስሎአቸው በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው።» ዕብ.13፥7። ይህ አነጋገር የአበውን ሃይማኖት ሥርዓትና ትምህርታቸውን በሚገባ መጠበቅና አጥብቆ ይዞ ከዚያ የሚገኘውን ጸጋ መካፈል እንዳለብን ያስተምረናል። ነቢዩ ሙሴና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔር ምርጦች በመሆናቸው በአንድ መንፈስ አንድ ዓይነት ትምህርት አስተማሩን። ተመሳሳይ ቃል ነገሩን።

ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁ ያላቸው የቀደሙት አበው:- ሃይማኖትን ጠብቀው በሥርዓት ኑረው ይህን ዓለም በድል ያሸነፉትን ቅዱሳን ነቢያት፥ ሐዋርያት እንዲሁም ተከታዮቻቸውን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን ነው። ቃላቸውና ቋንቋቸው የእነርሱ ትምህርትና ሥርዓታቸውም የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት ነው። በእነዚህ አበው ትምህርትና እነርሱ በሠሩት ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ብላ ትናገራለች። ሃይማኖታችሁ ጎደሎ ነውና እመኑ፥ ከሥርዓት ወጥታችኋልና በሥርዓት ኑሩ፥ ምግባራችሁ ጎደሎ ሆኗልና ፍሬ ምግባር ይኑራችሁ፥ በሥጋችሁ ፈቃድ መሄድን ወድዳችኋልና እርሱን ትታችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመላለሱ:- በጠራችሁት ጊዜ እንዲሰማችሁ ሕይወታችሁን ለእግዚአብሔር የተመቸ አድርጉ:- እንዲቀርባችሁ – እንዲጠብቃችሁ ወደ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅረቡ:- በሕጉና በትእዛዛቱም እየተጓዛችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ምድር ውረሱ የገነትና የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች ሁኑ ትላለች ቤተ ክርስቲያን– በቀደሙት አበው ቃል።

ዛሬም በዘመናችን እንደቀድሙት እሥራኤል የሰው ልጅ ከፈጣሪው ተጣልቶ ከሕገ እግዚአብሔር ወጥቶ የአባቶቹን ሥርዓት ሰማያዊውን ጸጋ ትቶ ምድራዊና ሥጋዊ ሥርዓት ሠርቶ በዚያ እየሄደ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ቤት ርቋል። ስለዚህ እንደነቢዩ ሙሴ ሰው በናቀውና በጣለው ሕይወት በፍጹም ትሕትና የእግዚአብሔርን ጥሪና ምርጫ መሠረት አድርጎ የተነሳ የእግዚአብሔር ሰው ያስፈልጋል። ይህን የተሰጠውን ሰማያዊ ተስፋና የዘለዓለም ሕይወት በሥጋው ፍላጐት ተሸንፎ እንደሌለ በመቁጠር ዓለም እያሸበረቀች አሥራ ተስፋውንና ሕይወቱን በምድር ያሚጠጠችበትና ከፈጣሪው ጋር የተጣላ ትውልድ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቅ ሙሴ ዛሬም ያስፈልጋል።

ለአስታራቂነት የተመረጠ ለዚህ ደገኛ ተግባር የተለየ ሰው ዛሬ ለዓለማችን ያስፈልጋታል። የሰው ልጅና እግዚአብሔር ተጣልተዋልና። በእርግጥ ሽማግሌ ያስፈልጋል። ሕዝቡን –የሰው ልጆችን «ከእናንተ እግዚአብሔር የቀረበው ታላቅ ሕዝብ ማነው?» ብሎ የሚጠይቅና ስለ ኃጢአታቸው የሚገስጽ ዳግመኛ ሙሴ ዛሬም ለዓለማችን ያስፈልጋል። ይህ ዓለም ለሕግዚአብሔር ሕግ—ለቃሉ እንዲገዛ ራሱን እስከመስጠት ፍቅሩን የሚገልጥ—በሕዝቡ መዳን የራሱን ሕይወት የሚለውጥ—ለዚህ ታላቅ ገድል ራሱን ያዘጋጀ ሙሴ ዛሬ ለዓለማችን ያሻታል።

ይህ ብቻ አይደለም:- በሥጋዊ ፍላጐት ንረት – በምድራዊ አምሮቱ ብዛት ለእግዚአብሔር አልገዛ ያለውን በኃጢአት ብዛት የቆሸሸውን ሕይወቱን ለውጦ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ የተዘጋጀ ትውልድ። ራሱን ወደፈጣሪው ያቀረበ ራሱን ከፈቃደ ሥጋ የለየ ታላቅ ሕዝብ ዛሬ ያስፈልጋል። የአባቶቹን ሃይማኖት ያልተወ የአባቶቹን ሥርዓት ያልናቀ በበረከታቸው የተባረከ ከጸጋቸው የተካፈለ የእምነትና የሥርዓት ለውጥ ሳይሆን የሕይወት ለውጥ ማድረግ የሚገባው መሆኑን ያወቀ ታላቅ ሕዝብ ዛሬ ለእግዚአብሔር ያስፈልገዋል። በዚህ ሕይወት የሚኖር ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር የቀረበና አምላኩም የቀረበው ታላቅ ሕዝብ ነው። ዓለማችን ግን የዚህን መሰል ሕዝብ ረሀብተኛ ናት።

ዛሬ እንዚያ ከዘመናት በፊት የተነገሩት የነቢዩ የሙሴ ቃላት ሳያረጁ አዲስ ሆነው አሉ። የሚናገራቸው ሙሴ – ለኃጢአትና ለፈቃደ ዓለም የተጣለ ለጽድቅና ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተነሳ ሙሴ ግን የለም። ዛሬም እንዚያ ሕግጋተ እግዚአብሔርና ያ ሥርዓተ አምልኮ በወንጌል ተተርጉሞአል። ብሉይ ኪዳን ንባብ ሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ ነውና። የሚሄድበት የሚያከብረውና የሚመራበት ሰው ግን የለም። የሰው ሕይወት ከኃጢአት የተነሣ አርጅቷል ዝጓል ከሐዲስ ተፈጥሮው (በክርስቶስ ካገኘው ሕይወት) ተፈጥሮው ተለውጧል ለጽድቅ ሳይሆን ለኀጢአት ተገዝቷል። ታላቅ ሕዝብ እንዲሆን ሁሉን ወደሚገዛው እግዚአብሔር እንዲቀርብ የተጠራው ሕዝብ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረው የሰው ዘር ሁሉ ነበር። ሰው ግን ይህን ጥሪ ሊሰማ አልወደደም። ከመዳን ይልቅ ሞትን መረጠ። ስለዚህም ሰው አላወቀም እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ። መዝ.48፥12። ኢሳ.1፥12።

ከእኛስ እንግዲህ ማነው እንደሙሴ ሕዝብን ለማገልገል ራሱን ከዓለም የለየ? ማነው ለኃጢአተኛ ለፈቃደ ሥጋ የተጣለ፣ የተዋረደ፣ የሞተ፣ ሆኖ ለጽድቅ ራሱን ያነሳ? ማነው የአበውን ሃይማኖትና የአምልኮ ሥርዓታቸውን ገንዘብ አድርጐ በሄዱባት መንገድ በጠባቧ የገድልና የትሩፋት ጐዳና ለማጓዝ የተዘጋጀ? በረከታቸው የሳበው ጸጋቸው የኀበኘው እንደሙሴ በወጣትነቱ ራሱን ለቤተ እግዚአብሔር የሰጠ ማነው? ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚቀና ለምእመናን የአበውን የሃይማኖት ጉዞ የሚተርክ የሚያስተምር ማነው? ራሱን በትህትናና በፍቅር በሃይማኖትና በምግባር በሕይወትና በቅድስና ወደ እግዚአብሔር ያቀረበ ማን አለ? ታላቅ ሕዝብ እንሆን ዘንድ (የሚያስተጋባውን) የዘወትር የቤተክርስቲያን ጥሪ ለመስማት ዕዝነ ልቡናችን የተከፈተ እነማን እንሆን? እግዚአብሔር እንዲቀርበን በሥርዓቱ የምንጓዝ:- ለሕግጋቱ የምንገዛ ለዚህ ዓለም ፈቃድና ለሥጋዊ አምሮት ራሳችንን ያዋረድንና ዓለምን አሸንፈን የእግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብ ለመባል የተዘጋጀን ከቶ እንገኝ ይሆን? የለንም።

ታዲያ እስከመቼ በተዳፈነና በተሸነፈ ውስጥ ባዶ በሆነ ሕይወት እንቆያለን? ዘመናችን ሳያልፍ—በእግዚአብሔር ቃል ተወቃሽ ሳንሆን የቀደመ ማንነታችንን ለውጠን በአዲስ ሰውነት በአዲስ የሃይማኖት ጽናት የአበውን ሃይማኖታቸውን ሥርዓታቸውን ተረክበን ልንከተላቸው በሄዱበት ልንሄድ ጊዜው አሁን ነውና ለዚህ መዘጋጀት ያስፈልጋል። በተዳደፈ ሰውነት ኃጢአት በአቆሸሸው ልቡና:- ምግባር በተለየው ሕይወት ሆኖ የቀደሙትን አበው ትምህርተ ሃይማኖት:- ሥርዓትና ክርስቲያናዊ ውርስ መረከብና መሸከም ስለማይቻል የራስን ሕይወት በንስሐ መመርመር ያስፈልጋል። ከዚህ በኋላ ነው ሥጋውን በልቶ ደሙን ጠጥቶ ወደ እግዚአብሔር የቀረበ – እግዚአብሔር አምላኩ የቀረበው ታላቅ ሕዝብ ለመሆን የሚቻለው። በድንግል እናቱ አማላጅነት እረሱ መቅረቡን ይስጠን አሜን። ✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

> ወደ እግዚአብሔር ቤተ በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ፥ ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መስዋዕት ይበልጣልና፤ እነርሱም ክፉ እንዲያደርጉ አያውቁምና። እግዚአብሔር በሰማይ፤ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን፤ በእግዚአብሔርም ፊት ቃልን ይናገር ዘንድ ልብህ አይቸኩል፤ ስለዚህም ቃልህ ጥቂት ይሁን።
>
> መክብብ.5፥1–3።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ኪነጥበብ

ቤታቸው ውስጥ በጸሎት ላይ እያሉ ነበር፥ የፊት በራቸው በኃይልና በችኩላ የተንኳኳው።

ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው አዳ መጡ፥ ገጭ፥ ገጭ፥ ገጭ በፍጥነት – እኒያ የሮማ ወታደሮች ናቸው ብለው ነበር የገመቱት። ሕዝበ ሮማ የቆስጠንጢኖስን መንግሥት መደገፍ በመጀመሩ ክርስቲያኖች በምዕራባዊ ሮማ ገዥዎች መሳደድ ጀምረዋል። ካታኩምቦች ከምድር በሚሸሹ ክርስቲያኖች እየተጥለቀለቁ ነው።

ገጭ – ገጭ – ገጭ – «አባ–አባ ክፈቱልኝ» የሴት ድምጽ ነበር። ከፊተኛው ይልቅ የአሁኑ ድምጽ አስደነገጣቸው «ማንናት? በዚህ ሰዓት፤ መሽቷል። ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት!»

«አባ – አባ – እኔ ነኝ» ልጅቷ እየተርበተበተችና በስርቅታ ድምጽ ነበር የምትጣራው።

እማተቡና በሩን ከፍተው ቆሙ።

«ኡኹ – ኡኹ – አባ – አባ»

አባ– «ማነሽ» አሉ ቀስ ብለው። የሮማ ጨረቃ አካባቢዋን ጤፍ በሚያስለቅም ብርሃንዋ አድምቃዋለች ቀስ በቀስ ቤቱንም በብርሃንዋ ሞላችው።

«አባ – እኔ ነኝ፣ ቬነስያ»

አባ – «ሰ – ዓ – ሊ – ለነ – ቅ – ድስት» ራሳቸውን ያዙ «ምነው ምን ሆንሽ ልጄ» በሩን መልሰው ዘጉና እጆቻቸውን ደረታቸው ላይ ለጠፉዋቸው

«አመ...ለ...ጥቋቸው አባቴ እህ...እህ» ጫን ጫን ትተነፍሳለች

አባ – «እነማንን፥...እነማንን ልጄ?»

አባ በመደነቅ ፊቷን ተመለከቷት

«ለቬንስ...መስፍን ሊሸጡኝ...» አልጨረሰችውም ዕንባዋ ቀደማት እጇን ይዘው ወደ ጸሎት ቦታቸው ወሰዷት።

ቬነስያ!

## ቬነስያ

ከዳንኤል ክብረት

የመክስምያኖስ ተወዳጅ ልጅ። ብቸኛ ቀዳሚ ተከታይ የሌላት። በቁንጅናዋ ተወዳዳሪ ስላልተገኘላት ነበር የዜውስ ካህን ቬነስያ ብለው የሰየሙዋት። ፀጉርዋ ትከሻዋ ላይ ሲያዩት የተኛ ዘንዶ ይመስላል። ከሁሉም በላይ የሮማን ጀግኖች ልብ የሚፈታተነው ደግሞ እንደ አጥቢያ ኮከብ የሚያበራው ዓይንዋ ነበር።

ንጉሥ መክስምያኖስ «ልጄ የልዕልቶች ልዕልት ናት!» እያለ ለመኳንንቱ ሳይናገር ውሎ አያድርም። ከግቢ አትወጣም። ብትወጣም እንኳን በደንገጡሮቿ ተከባ በሐር በተሸፈነ ሠረገላዋ ውስጥ ሆና ነው።

የሮማ ጀግኖች ‹እውነተኛዋ የፍቅር አምላክ ቬነስ በመክስምያኖስ ቤት ትገኛለች› እያሉ ለውበትዋ ሊሰግዱ ጠዋት ማታ ከዚያ የተንጣለለ ግቢ አይጠፉም። እንዲያውም ብዙ ልውላን ‹መክሰምያኖስን ዜውስ የበደለው ነገር ቢኖር ቬነስያን ልጁ ማድረጉ ነው። ባትሆን ኖሮማ ያለርሱ የሚያገባት ባልተገኘ ነበር› እያሉ ይተርታሉ።

ስለ ቆንጆዎች በተነሳ ቁጥር ተምሳሌት የምትሆነው የመክስምያኖስ ብርቅዬ ልጅ ቬነስያ ናት። በልቡ ያልተመኛት፥ በሕልሙ ያልዳሰሳት፥ በዓይኑ ያልተከተላት ሮማዊ ቢኖር ምናልባት አባቷ ብቻ ሊሆን ይችላል።

የሮማ ልውላን ሁሉ በንጉሡ ፊት ጀግና ለመባል ለመመረጥና በውበታቸው ቁንጠኞች ለመሆን ዘወትር የሚጥሩትና ከጥቂት ዓመታት በፊት በሮማ ቤተ መንግሥት ዙርያ የማይጠፉት ቬነስያን ለማግባት ደጅ እየጠኑ ስለሆነ ነው እያለ የሮማ ሕዝብ በየአደባባዩ መጠቋቆምና መንሾካሾክ ከጀመረ ሰንብቷል።

ንጉሥ መክስምያኖስ ልጁ ላንዳፍታ እንኳን ካጠገቡ እንድትለይ አይወድም። ስታለቅስ ቀርቶ ሲከፋት ማየት አይሻም። ሲወጣም ሆነ ሲገባ ስለርስዋ ውበትና ሕይወት ይጨነቅላታል። ከናቷ ይልቅ ስለመብልና መጠጧ የሚያስብላት እራሱ ነው። ቬነስያ ካለች ለሰይጣን እንኳ ግዛት ይሰጠዋል።

አንድ ቀን ልዕልት ቬነስያ በሮማ አደባባይ ሐር በተሸፈነው ሠረገላዋ ውስጥ እንደ ሠራተኛ ንብ በከበቧት ደንገጡሮቿ ታጅባ ስትጓዝ ግንዲላ የሮማ ወታደሮች አንዱን አዛውንት እያዳፉ ሲወስዱት አየችና ሠረገላዋን አስቆመች። ደንገጡሮቿ ደነገጡ ልዕልታቸውም እንባ ያዘሉ ዓይኖችዋን ስትጠርግ እዩዋት። ወዲያው በእግርዋ ሥር ተንበርክከው ምልጃ እንደሚጠይቅ ጸሎተኛ አንጋጠው እዩዋት።

«ምን ሆኑ እሜቴ?» የደንገጡሮች እመቤት ጠየቁ

«እነዚያን ወታደሮች ጥሪያቸው» ቬንስያ ጣትዋን እየተደበደቡ ወደሚሄዱት አዛውንትና ወደ ከበቡዋቸው ወታደሮች አመለከተች።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የደንገጡሮች እመቤት – ጠርሲዳ ይደበድቡ የነበሩትን ወታደሮች ሲያነጋግሩ የመሸበር ሁኔታ ታዩባቸው፥ ዱላቸውን ወደ ብብታቸው መልሰው አዛውንቱን ከያዘው ወታደር በቀር ሁሉም ወደ ሠረገላው መጡና ለጥ ብለው መሬት ከሳሙ በኋላ በተጠንቀቅ በልዕልት ቬነስያ ፊት ቆሙ።

«እኒያን አዛውንት አምጡ – ዋቸው» ቬነስያ አዘዘቻቸው።

«ክርስቲያን ናቸው» መቶ አለቃው መለሰ

«ክርስቲያን ምንድነው?» ወደ እመቤት ጠርሲዳ ዞር ብላ ጠየቀቻቸው

«ኢየ–ሱ–ስ ክርስቶስ የተባለ አምላክ የሚያመልኩ ናቸው እሜቴ»

«ለምን ትደበድቡዋቸዋላችሁ ታድያ»

«ሲሰብክ አግኝተነው ነው» መቶ አለቃው ተናገረ

«እስቲ አቅርቡዋቸው»

አዛውንቱን የያዘው ወታደር መሬት ለመሬት እየጐተተ ይዟቸው መጣ። ልዕልት ቬነስያ ፊት ሲደርስ ፈታቸው። አዛውንቱ ተነስተው ቆሙ። ይንቀጠቀጣሉ። ፊታቸው በደም ተሸፍኖአል። ቀኝ እጃቸው ተሰብሮአል። ቬነስያ አንጀቷ ተንሰፈሰፈ። ከልጅነቷ ጀምራ ይኼ ለሰው የማዘን ባህርይ ነበራት። ደንገጡሮቿ ይኼን ባህርያዋን ከእናቷ የወረሰችው ነው ይላሉ። እናቷ እንዲሁ ሆደ ባሻ ናት።

ወታደሮቹ የልዕልቷን ፊት ሲመለከቱ ፍርሃት ወረራቸው። መክሰም ያኖስ ልጁ ይሁን ያለችውን ከመቀበል አይመለስም።

«አባት ምን አድርገው ነው?» ቬነስያ ጠየቀቻቸው።

«ለኔ የሞተ–ል–ኝንና ከሲዖል ባር–ነ–ት ነፃ ያ–ወ–ጣ–ኝን ጌታዬን በማ–መ–ኔ–ነዋ– እሜቴ»

እኒህ ሰውዬ የሚናገሩት በሙሉ አልገባሽ አላት ‹ሲዖል...ጌታ› ...ምንድናቸው።

«ማን ይባላሉ»

«አባ ሄርማን»

«ልቀቁዋቸው ይሂዱ? አስጠራዎታለሁ የት ነው የሚኖሩት!»

አባ ሄርሜን አድራሻቸውን ከተናገሩ በኋላ የተሰበረ እጃቸውን ደግፈው፥ በደም የተሸፈነ ፊታቸውን እየጠረጉ ወደ መንደሮች መሐል ገቡ። ከዓይንዋ እስኪሰወሩ ድረስ ተከተለቻቸው።

ከዚያች ሰዓት ጀምሮ የኒያ ጐስቋላ አባት መልክ ተቀረፆባት ቀረ። ባሰበቻቸው ቁጥር ዕንባዋ ይመጣል። የተሰበረ እጃቸው ደም የከበበው ፊታቸው ድቅን ይልባታል። በዚያ አሳዛኝ ፊታቸው መሐል ግን ደስተኝነታቸውን የሚያሳይ ፈገግታ ይነበብ ነበር።

እመቤት ጠርሲዳ የቬነስያን የዚያን ቀን ገጠመኝ ካስተዋሉ በኋላ ስለክርስቶስ ለመንገር በሩ ተከፈተላቸው። እርሳቸው ለእልፍኙ የሚሆን ዕቃ የሚገዙ በመሆናቸው የንግድ ከተሞችን ሁሉ በየጊዜው ያዳርሱ ነበር። በዚህ ወቅትም በነዚያ የክርስቲያኖች ጽናትና ሕይወት እንደተደነቁ ይኖሩ ነበር። በመጨረሻ ታዲያ በአንድ የመኳንንት የገበያ አዳራሽ ውስጥ ከአብሮ አደግ ጓደኛቸው ጋር ባለፈው ዓመት ተገናኙ። ጓደኛቸው ክርስቲያን ነበረችና በሚያስደስትና በሚያጓጓ ሁኔታ ስለአዲሱ ኑሮዋ አጫወተቻቸው። በክርስቲያኖች ሕይወት የሚገኘውን ፍቅር፥ አንድነትና መተሳሰብ ጽናትና ቆራጥነት እንዲገረሙበትና እንዲሳቡበት አደረገቻቸው። በተለይም ደግሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ፍቅር ሲል ስለደረሰበት መከራ ከተረከችላቸው በኋላ የሰማዕታትን ዜና አበሰረቻቸው።

እመቤት ጠርሲዳ በንጉሥ መክስምያኖስ ግቢ ያለውን የራሳቸውን ሕይወትና በካታኩምቡ ውስጥ ከምድር በታች የሚገኘውን የክርስቲያኖች ኑሮ አነጻጸሩት መሸቆጥቆጥ፥ መደንገጥ፥ ለታይታ ብቻ መሥራት፥ አንዱ አንዱን ባይነቁራኝ መከታተል፥ መተማማት፥ ገላን በድብቅ ለመኳንንት መሸጥ...የሚያስጠላና የውርደት ኑሮ በዚያ የተንጣለለ ግቢ እየኖሩ መሆኑን ተረዱት። ከዚህም በላይ ደግሞ ስለወዲያኛው ዓለም ባሰቡ ቁጥር ተስፋቸው እየመነመነባቸው መጣ። በዚህች ምድር የቀመሷት ስቃይ በወዲያኛውም እንዳ ይከተላቸው ያስባሉ።

ስለዚህ እመቤት ጠርሲዳ ወደ ገበያ በሄዱ ቁጥር ዘመድ ጥየቃ ብለው እያመካኙ ወደ ክርስቲያኖች ቤት በድብቅ መገስገሳቸውን ከአምና ጀምረው ተያይዘውታል። ያ–በትረካ ብቻ የሰሙት ሕይወት እርሳቸውም ተካፈሉበት። ያጽናኑዋቸዋል፥ ይጸልዩላቸዋል፥ እዚያ የፍቅር ማኅበር ደርሰው ሲመለሱ የመንፈስ ብርታትን የአእምሮ ሰላምን ይጐናጸፋሉ።

እመቤት ጠርሲዳ ልዕልት ቬነስያን በዚያ ገጠመኙዋ ተንተርሰው ስለ ክርስቲያኖች ሕይወት በሚተርኩበት ጊዜ ስቃያቸው፥ ረሃባቸው ግን ደግሞ ጽናታቸው፤ ፍቅራቸው ያንዱን ሞት አንዱ ሊሞት የሚያደርገውን እሽቅድምድም ስትሰማ ያ–ለዓይንዋ ቅርብ የሆነው ዕንባዋ ይቀድማት ነበር። እመቤት ጠርሲዳ የልዕልቷን መመሰጥ ሲመለከቱ ስለርሳቸው ሕይወት አወሩላት።

«ለዚህ ነው እመቤት ጠርሲዳ ምንም ነገር ቢመጣብዎ የማይሸበሩት! አንድ ነገር በሆነ ቁጥር አባቴ እንኳን ሲረበሽ ሲያጽናኑት እገረም ነበር። ደግሞ ለአገልጋዮች ሁሉ ሩህሩህ ነዎት» ልዕልት ቬነስያ የነገሩትንና የርሳቸውን ባህርይ ታነጻጽርላቸው ጀመር።

«እኒያ የተደበደቡት አዛውንት ታላቅ መምህር ናቸው። ለሰዎች ሁሉ የደኅነትን በር የከፈቱ ናቸው።»

እመቤት ጠርሲዳ ያንን ገጠመኝ ሲያወጉ ልዕልት የተሰበረው እጃቸውና በደም የተሸፈነ ፊታቸው ታወሳት።

«እመቤት ጠርሲዳ እኔ ክርስቲያን መሆን እችላለሁ?» ልዕልት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቬነስያ ዕንባዋን ጠራርጋ የጠየቀቻቸው ጥያቄ ነበር።

«ትችያለሽ ልዕልት ችግሩ በአባትሽ ቤት ያለውን ጣዖት አምልኮ ለማሸነፍ ያለሽ ጽናት ነው»

«እመቤት ጠርሲዳ ኢየሱስ ክርስቶስ ደካሞችን ይረዳል አላሉኝም»

«ልክ ነሽ ልዕልት»

«ታድያ እኔንስ አይረዳኝም? ወይስ ልዕልት ነች ብሎ ይተወኛል»

«እግዚአብሔር ሰው አይመርጥም ነገር ግን ቆራጥ ልብና ጽኑ እምነት ይጠይቃል»

«ይኼንን እንዴት ነው የማገኘው»

«የወንጌል ትምህርት ስትማሪ፥ ስትጸልይ»

«ማን ያስተምረኛል እመቤት ጠርሲዳ? እንደርስዎ ተደብቄ መሄድ አልችል?»

እመቤት ጠርሲዳ ከዚያች ቀን ጀምሮ የክርስትናውን ሕይወት በደንብ ያስተምሩዋት ጀመር። የሐዋርያትን ገድል፥ የደጋግ እናቶችን ታሪክ በልቧ ጽላት ቀረጹላት በተለይ ደግሞ ከሻሻቸው አምልጦ ግንባራቸው ላይ ያንቀላፋ የሚመስለውን ሽበት ወደ ጐን እየላጉ የእናትነት ለዛ ባለው ቅላጽያቸው ሲያወጉዋት ያላየችውን ሕይወት ያየችው የኖረችበት ያስመስላታል። በቬነስያ እልፍኝ ውስጥ የሚያድሩት እመቤት ጠርሲዳ በመሆናቸው ሌሊት ሌሊት በድብቅ አዲሱን ኑሮ መኖር ጀመሩ። ይጸልያሉ፥ ያስተማሯትን መዝሙር ለሆሳስ ይዘምራሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ያነባሉ።

ልዕልት ቬነስያ ሁልጊዜ የሚያሳስባት የአባትዋ ሕይወት ነበር። ስለዚህ ጉዳይ ዳር ዳር ብላ በወሬ ወሬ የሰማች መስላ ብታነሳበት ፊቱ ሲቀያየር ተመለከተችውና ዝም አለች። በመሐል ሮማ የቆመውን የራሱ የአባቷን ሐውልት የሮማ ሕዝብ እንደሻሺ ተነጥፎ ሲሰግድለትና ሲሳለመው እየዋለ መክሰምያኖስ ክርስቲያን ይሆናል ማለት ዘበት መሆኑን ተረዳችው።

እርስዋ ግን በክርስቲያንነቷ ፀናችበት።

በንጉሥ መክስምያኖስ ግቢ ልዕልቷን ፍለጋ የሚያቶስቱሱት መኳንንት እየበዙ መጡ። ይህችን እያደር እየፈካች፥ እያበበች የምትሄደውን ጽጌረዳ ለመቅጠፍ የመክስምያኖስን ደጅ አጣበቡት። ንጉሡ ይፈልጋል የተባለው ነገር ሁሉ በመኳንንቱ ይጐተታል የልዕልቷን ልብ ለመስለብ ከሩቅ ምሥራቅ የመጡ ስጦታዎች ውድና ብርቅ የሆኑ ልብሶች ይኸጐደጐዳሉ። ልዕልት ቬነስያ ግን የሚመጣላትን ሁሉ በእመቤት ጠርሲዳ እጅ ለክርስቲያኖች እየላከች «እንድጸና ጸልዩልኝ» ትላቸዋለች።

በዚህ መሐከል ግን የመክስምያኖስን ልብ ቀስፎ የሚይዝ ዜና ግቢው ውስጥ ደረሰ። የምሥራቅዋ ሮማ ገዢ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያኖች በነጻነት እንዲኖሩ አወጀላቸው። ስለዚህም ከምድር በታች በስቃይ የነበሩት ሁሉ ወደ ቁስጥንጥንያ መገስገስ ጀምረዋል። አንዳንድ የጠረፍ መኳንንትም ክርስቲያን በመሆናቸው የምዕራብዋን ሮማ ግዛት አሳልፈው ሊሰጡ ነው እየተባለ መወራት ተጀመረ።

የሮማ መኳንንት በንጉሡ ዙርያ ከበው፥ የሰሙዋቸውን ወሬዎች ሁሉ እያጋነኑ አስጨነቁት። ክርስቲያኖች ሁሉ ከቆስጠንጢኖስ ጋር ሆነው ሊወጉት የተዘጋጁ መሆኑን ጨምረው ጨማምረው አስደነገጡት ይህ ወቅት ነበር መክስምያኖስ ጀግና የፈለገበት ጊዜ።

ዝነኛው የጦር ሰው የቬነስያው ልዑል ማልኩስ የመክስምያኖስን ቀልብ መሳቡን እንዳረጋገጠ ከጐኑ አልጠፋም አለ፥ ስለውጊያው ዕቅድ፣ ስለወታደር ምልመላ፥ ስለስንቅ፥ ስለቆስጠንጢኖስ የጦር ስልት አብረው ሌሊት ሳይቀር ይወያያሉ፥ ያወጣሉ ያወርዳሉ። በዚህም የተነሳ ልዑል ማልኩስ ቤተመንግሥት ከመዋል አልፎ ማደርም አመጣ።

ንጉሥ መክስምያኖስ በፈረሰኞኑቱና በጦረኛነቱ የሮማ ሕዝብ አንቱ የሚለውን ልዑል «ቀኝ እጄ ነው» እያለ ማውራት ከጀመረ ሰነበተ። በሚወጣባቸው አደባባዮች እንኳን ሳይቀር ከቀኙ የሚቆመው የቬነሱ ልዑል ማልኩስ ከሆነ ውሎ አደረ። የሮማ ሕዝብ «ወደ መክስምያኖስ በተጠጋህ ቁጥር ወደ ጽጌረዳዋ ትጠጋለህ» ያሉት የቅርብ ጊዜ ተረታቸው የሠራ ይመስላል።

መክስምያኖስ አንድ ምሽት የጦሩን ሁኔታ ከልዑል ማልኩስ ጋር ሲነጋገር ከቆየ በኋላ «ዛሬ ራት ከልዕልት ቬነስያ ጋር ነው» ብሎ ወደ እልፍኝ ወሰደው። እመቤት ጠርሲዳ የንጉሡንና የልዑሉን መምጣት ሲሰሙ የግድግዳ ሥዕሎችን በሙሉ አውርደው ደበቋቸው።

«እንደምን ዋልሽ ቬነስያዬ» ንጉሥ መክስምያኖስ ነበር።

«እንደምን ዋልክ አባዬ» ደረቱ ላይ ተለጠፈችና ሳመችው

«ቬነስያዬን ታውቃታለህ ልዑል»

«በውበትዋ ዝና መላዋን ሮማ ስታጥለቀልቃት የንጉሤ ልጅ በመሆንዋ ከምኰራባት በቀር አንተዋወቅም» ልዑል ማልኰስ በዓይኑ አተኩሮ ማየት አቅቶት መሬት መሬት እያየ መለሰ።

«በል ተዋወቃት ልዕልት ቬነስያ የውቦች ሁሉ ቁንጮ ናት» እጇን ስቦ ለልዑሉ ሰጠው ልዑል ማልኩስ የእጁ መንቀጥቀጥ እንዳይታወቅበት እየተጠነቀቀ ጨበጣት።

ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ልዑል ማልኩስ ሐሳቡ ሁሉ ስለ ልዕልት ቬነስያ ሆነ እርስዋን አግብቶ በውበትዋ የቬነስ ከተማ በሠረገላው ሲሽከረከር ይታየው ጀመር። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመክስምያኖስ ምትክ ንጉሠ–ሮማ ሆኖ ልዕልት ቬነስያ በግቢው ውስጥ እንደ ፀሐይ ስታበራለት ይታየዋል።

እመቤት ጠርሲዳ የልዑሉ ሁኔታ አላማራቸውም። የቬነስን ልዑል አሳምረው ያውቁታል። ውበትን ለመቅጠፍ የሚሽቀዳደም፣ አያሌ የሮማ ቆንጆዎችን ውበት ያበላሸ መሆኑን ሰምተዋል።

ንጉሥ መክስምያኖስ የቆስጠንጢኖስ ጦር ምዕራባዊ ግዛቱን ሰብሮ ገብቶ የተደበቁትን ክርስቲያኖች እያሰለፈ ሮማ ከመድረሱ በፊት ልዑል ማልኩስን የመሰለ ጀግና ድንበሩ ላይ ጠብቆ ድል እንዲያደርግለት ይፈልጋል። ልዑል ማልኩስ ደግሞ ያለምንም ነገር ድንበር ላይ አይቆ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ምም። አመሉን ያውቀዋል። የዚህ ሰሞን ማንጕበብም ልዕልት ቬነስያን ፍለጋ መሆኑ ገብቶታል። ስለዚህ ትናንት ማታ ወደ ልዕልት እልፍኝ መጣና

«ልዕልቴ ልጅነቱ አይበቃም» ብሎ ፈገግ አለ

«እንዴት አባዬ» ቬነስያ ልቧ ተሸበረ

«ይኼንን ግቢ በሠርግሽ አድምቂዋ» ሊወጣ የሚተናነቃትን ዕንባዋን በግድ ገታችው። አባቷ ለቬነሱ ልዑል ያጫት መሆኑን ጠርጥራለች። እመቤት ጠርሲዳ ደግሞ የልባቸውን ዘርግፈው ስለልዑል አጫወቷት።

ልዕልት ቬነስያ ማልቀስ ጀመረች።

«አይገባም ልዕልት። ክርስትያን ጽኑ ነው። እግዚአብሔር የልብሽን ሐዘን ያያል» ይሏት ነበር እመቤት ጠርሲዳ። ነገር ግን የሠርጉ ቀን በቀረበ ቁጥር የቬንስያ ሐዘን እየባሰ ሄደ። ያ ውበትም ደመና ውስጥ የሠረገች ጨረቃ መሰለ። ከአልጋ አትወርድም፤ አልያም ደግሞ በእመቤታችን ሥዕል ፊት ተደፍታ ታለቅሳለች። ዕንባ ቀለቧ ሆነ። እየከሳች እየመነመነች መጣች።

«እግዚአብሔር ሆይ ልጅህ እንድሆን አትፈልግም? ለምን አሳልፈህ ትሰጠኛለህ» ትላለች ዘወትር። እመቤት ጠርሲዳ የልዕልት ቬነስያን መታመም ሲያዩ ባለመድኃኒት ናቸው በማለት መክስምያኖስን አስፈቅደው አባ ሄርሜንን ይዘዋቸው መጡ።

አባ ሄርሜን በመስቀላቸው ዳስሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያጽናኑዋት ነበር። የራሳቸውን ታሪክ ሲነግሩዋትም ጽናትዋ ያይልባት ጀመር። አባ ሄርሜን ከመጡ በኋላ ፊትዋ እየታደሰ ተስፋዋ እየለመለመ መጣ። ጽናት ተሰማት። ንጉሥ መክስምያኖስም የባለመድኃኒቱን ውጤት ሲያይ በዚያው እንዲቆዩ ተማጸናቸው። ልዕልት ቬነስያ የተጠመቀችው በዚህ ወቅት ነበር።

አባ ሄርሜን በልዕልት ሕይወት የማይጠፉዋት ሰው ሆኑ። ከዚያች የመንገድ ላይ ገጠመኝ ጀምሮ ታስባቸው የነበሩት ጽኑ ሰው አጠገብዋ ሆነው በደንብ አስተማሩዋት ከመክስምያኖስ ይልቅ አባትዋ የሚመስሉዋት እርሳቸው ነበሩ። ሕይወታቸው ራሱ ለርስዋ ትልቅ ትምህርት ነው። ጽናትና ቆራጥነትን ጨምሮላታል። እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ አስተምሮአታል።

አባ ሄርሜን የተፈቀደላቸውን ጊዜ ጨርሰው ተለዩዋት የሠርጉዋ ቀንም እየደረሰ መጣ።

የጥንቱ ሐዘንና ለቅሶዋም አገረሸባት። በተለይማ ልዑል ማልኩስን ባየችው ቁጥር ያንገሸግሻት ጀምሮ አል። በግቢው ውስጥ ደግሞ ድግሱ ቀልጧል። የቬነስ መንገዶችም ልዕልቷን ለመቀበል አሸብርቀዋል። የሮማ ሕዝብም የሰሞኑ ወሬው ይኼው ሆኖአል። ሌሎች መኳንንት ደግሞ አኩርፈው ከግቢው ጠፍተዋል። ልዑል ማልኰስ ብቻ ይንጐራደዳል።

እመቤት ጠርሲዳ የሚያደርጉት ጠፍቷቸዋል። የልዕልት ቬነስያ ሁኔታ እያሠጋቸው መጥቷል። ባንድ በኩል ልዑሉን ብታገባ ሕይወቷ ምን እንደሚሆን ያውቁታል። ለቬነስ ጣዖት መስገድ ይኖርባታል። ያም እንኳን ልዑል ማልኰስ ካልጠገባት ነው። አለበለዚያ እንደሌሎቹ ሴቶች አንድ ቤት ተወርውራ በሐዘን ተቆራምዳ ትሞታለች። የሮማ ነገሥታት እንደሁ አይታመኑም ይገለባበጣሉ።

እመቤት ጠርሲዳ «ልዕልት እውነቴን ነው የምልሽ እመቤቴ ማርያም እዚህ ማጥ ውስጥ አትከትሽም» ይሏታል።

«ምን ላድርግ እመቤት ጠርሲዳ ትቼው ወደመጣሁት ኃጢአት ተዘፍቄ ደግሞ ጌታዬን ላሳዝነው...» ዕንባዋ ይቀድምባታል።

ሌሎች ደንገጡሮች በውበትዋ ስለተነካው ልዑል እያነሱ ያደንቁላታል። ስለዝናዋ ይተርኩላታል። በቆንጆዋ የቬነስ ከተማ እንዴት ደልቷት እንደምትኖር ያጫውቷታል። በዚህ ጊዜ «እባካችሁ ተውኝ ሌላ ጨዋታ አምጡ» ብላ ትቆጣቸዋለች።

በውበትዋ፥ በሀብትዋና በልዕልትነትዋ ከምታገኘው ክብርና ዝና ይልቅ ለቬነስያ ደስታዋ የክርስትና ሕይወቷ ነው። ከመክስምያኖስ ግቢ ለርስዋ የሚናፍቃት የምድር በታቹ በቅዱሳን ዕፅም የተሞላው ጨለማው ዋሻ ነው። የቬነስን ልዑል አግብታ ከምታገኘው ቅብጠት ይልቅ ደስታዋ ከክርስቲያኖች ጋር ሰማዕት ብትሆን ነበር። ከሮማ ዳንሰኞች የክርስቲያኖች ለቅሶ ይናፍቃታል– ልዕልት ቬነስያ።

በውበትዋ የምትኰራበት ቢሆን ኖሮ የሮማ ጐበዛዝት እንደ «ፍቅር አምላካቸው» ቬነስ ሊሰግዱላት ደርሰው ነበር። በሃብትዋ ብትተማመን ኖሮ መክስምያኖስ ያለርስዋ ሌላ ወራሽ ባልኖረው ነበር። ልዕልትነትዋ ቢያኮራት ኖሮ የሮማ መኳንንትን በግቢዋ ዙርያ እንደ እንዝርት ባሽከረከረቻቸው ነበር። ግን ለርስዋ ይኼ ሁሉ አልነበረም የደስታዋ ምንጭ፥ የሐሴቷ መዲና። ክርስቲያንነቷ፥ የእግዚአብሔር መሆንዋ ነበር የሚያረካት፤ ልቧንም የሚያስፈነድቀው። የዕለት ተዕለት ምኞቷም የሐር ልብሶች መለዋወጥ ሳይሆን አባ ሄርሜን የነገርዋትን የክርስቲያኖችን የፍቅር ኑሮ መኖር፥ የክርስቶስን ሥጋና ደም መቀበል ነበር። ግን አባትዋ የደገሰላት ኑሮ የዚህ ተቃራኒ የሰሜንና ደቡብ ያህል የተራራቀ በልብዋ አስባው በአእምሮዋ ስላው የማታውቀው ነበር።

ያ–ቀን ያ–ለርስዋ የተረገመ ቀን ዕንባና ሐዘን ያስከተለባት ቀን እየቀረበ እየተሳበ መጣ።

እመቤት ጠርሲዳ ደግሞ የቬነስያን ፊት በተመለከቱ ቁጥር ልባቸው በሐዘን መድማት ጀምሮ አል። ምን ያድርጉዋት የት አስገብተው ይደብቁዋት ሮማ እንደሆነች የመክስምያኖስ ናት።

እመቤት ጠርሲዳ ዕቃ ሊገዙ ወደ ገበያ በወጡ ጊዜ አባ ሄርሜን ጋ ሰው ላኩባቸው አባ ሄርሜን መልካቸውን ቀይረው ወደ ሠረገላዋ መጡ። እመቤት ጠርሲዳ የዕቃ ክርክር የያዙ መስለው ስለሁኔታው ሁሉ ለአባ ሄርሜን አጫወቷቸው። አባ ሄርሜን ቤታቸው ሮማ ከተማ በመሆኑ እንደማያስቸግር ነበር እመቤት ጠርሲዳ የሚያስረዱዋቸው በተለይም ከከተማዋ ግንብ አጠገብ በመሆኑ ለሁሉም መልካም ነው ይሏቸዋል።

ወደ ቤተ መንግሥቱ ሲመለሱ ቬነስያ አልጋዋ ውስጥ ሆና ታለቅስ ነበር። ድግሱ ደግሞ በግቢው ውስጥ ቀልጧል ልዑል ማልኰስም ወደ እልፍኝዋ እየመጣ ነበር።

• ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ማዳኑን ያዩ ይናገሩ

ካለፈው የቀጠለ

ከባስልዮስ ዘቂሣርያ

የመቶ አለቃውን ያገኘሁት በሠራው ምኩራብ በጸሎት ላይ ሳለ ነበር። እስኪጨርስ ጠበቅኩና የመጣሁበትን ጉዳይ ነገርኩት። እርሱም በፍቅር ከተቀበለኝ በኋላ ወደቤቱ ይዞኝ ሄደ። ታሞ የዳነውንም እንደ ልጅ የሚወደውን ባሪያውን አስተዋወቀኝ። ከዚያም ወደ እንግዳ መቀበያው ገባንና ምሳ ከተጋበዝኩ በኋላ ጌታ ስላደረገለት ተአምር ጠየቅኹት።

መቶ አለቃ – አዎን በዚያን ጊዜ እጅግ የተጨነቅኹበት ጉዳይ ነበር። ብላቴናውን በጣም እወደዋለሁ። ቀናና ፀባየ መልካም ልጅ ነው። በጠና ታሞ ሳስታምመው ሰንበትኩና በመጨረሻ እጄ ላይ እንዳለ ሕይወቱ አለፈች። በዚያ ጊዜ በጣም ተደናገጥኩ የማደርገው ጠፋኝ ብርክ ያዘኝ። ከቤት ወደደጅ እየተንጐራደድኩ ሳለሁ ከወደከተማው ጫጫታ ተሰማኝ። ወታደሮቼም የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቅፍርናሆም ከተማ መግባቱን ነገሩኝ። ወዲያው በደስታ ፈነደቅኹና ወደምኩራብ ቅድም የተገናኘንበት ሄጄ የምኩራብ ሽማግሌዎችን እንዲያማልዱኝ ነገርኳቸው።

ተርቢኖስ – ይቅርታ አንዴ ላቋር ጥሀና ራስህ ለምን አልሄድክም?

መቶ አለቃ – እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ። ምናልባት ያኋደልኩት ፍርድ ያላግባብ ያሰቃየሁት ወታደር ይኖራል። በመሆኑም ራሴ መሄዱን ልቀበለው አልቻልኩም። ክርስቶስ ራሴ ብሄድ የሚያባርረኝ ሆኖ አልነበረም ግን ራሴን ስለማውቀው ከእኔ የተሻሉ ሰዎችን መላኩን መረጥኩ። ለዚህም ስል የምኩራብ ሽማግሌዎችን ላክሁ። ደግሞ ጌታዬ አላሳፈረኝም ለምን ራስህ አትመጣም አላለኝም ትህትናዬን ተቀብሎ ወደ እኔ መጣ እንጂ።

ተርቢኖስ – መቶ አለቃ! ለመ ሆኑ የምኩራብ ሽማግሌዎች ሄደው ሲያማልዱ ዝም ብለው አንተ ስለላ ክኻቸው ብቻ ሄዱ ወይስ ምን ይዘው ቀረቡ?

መቶ አለቃ – በኋላ እንደነገሩኝ ሁለት ነገሮች ይዘው ነው የቀረቡት። ምኩራብ አሠርቷል፥ ሕዝባችንን ይወ ዳል ብለነዋል ነው ያሉኝ።

(በዚህ ጊዜ በር ተንኳኳ፥ አንድ ረዥም ሽማግሌ ገቡ)

መቶ አለቃ – ተዋወቃቸው የምኩራብ አለቃ ናቸው።

(ጉልበት ስሜ ተቀመጥኩ)

ተርቢኖስ – በጣም ይገርማል የእግዚአብሔር ነገር ጥያቄዬን ወደርስዎ ላዙር። ያኔ ስለብላቴናው ልታማልዱ ወደ ጌታ ስትቀርቡ ለምን ነበር ምኩራብ አሠርቷል፥ ሕዝባችንን ይወዳል ያላችሁት?

አለቃ – አንድ ሰው ሲያማልድ ከሚማለድለት ሰው የእጅ መንሻ ያስፈልጋል። እንዲሁ ባዶ እጅ አይኬድም። ብዙዎቻችን ቅዱሳንን ለምልጃ ስንጠራቸው ባዶ እጃችንን ሆነን ነው። ነገር ግን አማላጅ ባዶ እጅ አይሄድም የሚያማልድበት ትንሽ ነገር ያስፈልጋል። ዐውቀን ኃጢአት እየሠራን፥ መሥራት የምንችለውን ያህል ለጽድቅ ሳንሮጥ እግዚአብሔርን ለማገልገል፥ በሕጉ ለመኖር ፍላጐት ሳይኖረን አማልዱን ማለት ከንቱ ነው። ቅዱሳን የሚያማልዱን በጉዞ አችን ወቅት ለደከምንባቸው፥ ለወደቅንባቸው ነገሮች ነው።

ተርቢኖስ – እሺ ወደ መቶ አለቃ ልመለስና ለምንድነው ጌታ ወደቤትህ በመምጣት ላይ ሳለ «እዚያው ሆነህ ቃል ተናገር ብላቴናዬ ይፈወሳል በጣርያዬ ሥር ልትገባ አይገባኝም» ያልከው?

መቶ አለቃ – ጌታችን እኮ አምላካችን ነው። ለእርሱ የሚሳነው ነገር የለም። በግድ ወርዶ ሲዳስሰን፥ ሲያነሣን ማየት አልያም በሕልምና በራእይ መገለጽ አለበት እንዴ? ሁሉም ነገር በእምነት ይሆንልናል። ስለዚህ ቃሉ ለእኔ በቂ ነበር። ዛሬ ብዙዎችን ሰይጣን በተአምር፥ በምልክት የሚያስተው በሚታይ በሚዳሰስ ነገር ብቻ ስለምናምን ነው። ይህ ግን መሆን የለበትም። ልዑል እግዚአብሔር ከጐናችን ነው ስንጠራው ይሰማናል በአስደናቂ ጥበቡ ይመልስልናል ይህን ማመን ነው ያለብን።

ተርቢኖስ – እሺ መቶ አለቃ በልዑል እግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ።

ተሰናብቼ በሠረገላዬ ጉዞዬን በዚያው ከተማ ውስጥ በሉቃስ መንደር ከፍተኛ 4 ቀበሌ 38 ወደሚኖሩት የቅዱስ ጴጥሮስ አማት ቤት አመራሁ።

ሽምገል ያሉ ቀይ ሴት ናቸው። ወገባቸውን በመቀነት ታጥቀው ግቢ ሲጠርጉ እቤታቸው በር ላይ ሠረገላዬን አቁሜ ሰላምታ አቀረብኩ «ምነው የእኔ ልጅ» አሉኝ። ላነጋግራቸው እንደምፈልግ ነግሬያቸው እዚያው እግቢያቸው ውስጥ ከአንድ የወይን ዳስ ሥር ተቀመጥን።

ተርቢኖስ – እማማ ጌታ ወደር ስዎ ሲመጣ ምንድነበር በሽታዎ?

እማማ – አየ...ልጄ የጠና–የጠና ወባ ነበረችብኝ። ከልጅነቴ ጀምራ ታሰቃየኝ ነበረች። አሁን እየውልህ እርጅና መጣ መሰለኝ ሰውነቴ ሲደክም ጊዜ በረታችብኝና አልጋ ላይ ስታማቅቀኝ ከረመች። በኋላ... እልሃለሁ ጌታችን መጣና መታመሜን ሲሰማ ወደ ቤቴ ገባ። ከዚያም በነዚያ መድኃኒት በሆኑ መንፈስ በሚያነቁ እጆቹ ዳሰሰኝና ንዳዱን ሲገሥጸው ጊዜ ልክ እንደልጅ ሆኜ ተነሳሁ።

ተርቢኖስ – እማማ በዚያን ጊዜ ታመው ከርመው ሰውነትዎ ሳይጠና ተነሥተው ክርስቶስን ለምን አገለገሉት?

እማማ – አዬ ልጄ ሲያንሰኝ ነው። ያን ከመሰለ የአልጋ ቁራኝነት አላቆኝ ማገልገል ይብዛብኝ። ይኼማ ውለታ ቢስ መሆን ነው። ያገራችን ገበሬ የዘራውን እህል አላበቅልለት ያለውን መሬት ዘረ ቅርጥም ይለዋል። እንደዚያ መሆን ነው።

ተርቢኖስ – ታዲያ ከዚህ እኛ ምን እንማራለን ይላሉ?

እማማ – ብዙ ጊዜ ችግሩ ምን መሰለህ ስናጣ፥ ስንታመም፥ ስንወድቅ፥ ስንጨነቅ፥ ስንከስር፥ ስንታሰር እንዲያው በጭንቋ፥ ቀን በጣለን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እንዞራለን። እርሱም አይጨክንብንም ምሕረቱን፥ ጸጋውን፥ ቸርነቱን ይለግሰናል ከዚያ ችግር እንላቀቃለን። ታዲያ ምን ያረጋል የበላንበትን ወጭት ሰባሪዎች ሆነን እንቀራለን። የተሳልነውን ረስተን፥ የነበርንበትን ዘንግተን እግዚአብሔርን ማገልገል ሲገባን «ታም የተነሣ እግዜርን ረሳ» ነው እንኰበል ላለን ይህ ታዲያ አምላካችንን ያሳዝነዋል።

ተርቢኖስ – አሁን እንዴት ነዎት ?

እማማ – ክብሩ ይስፋ፥ እንደም ታየኝ ኰረዳ መስያለሁ። ከዚያን ቀን ወዲህ የቅዱሳን ማረፊያ ሆናአል ቤቴ እኔም ጠዋት ማታ ጸሎቴ አያቋርጥም አልጋዬን ባየሁ ቁጥር ጌታየን አስታውሰዋለሁ።

ተርቢኖስ – እግዚአብሔር ይባርክዎት እማማ አመሰግናለሁ።

• ይቀጥላል



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

እነሆ ዳገቱ ላይ ደርሰናል፥ ሰላም የሐመር ወዳጆች ወደ ዘንባባ ዮሐንስ ጉዞአችንን ቀጥለናል፥ አባ ዘውዱ ከፊታችን የሩጫ ያህል ይራመዳሉ እኛ ደግሞ ከኋላቸው እናለከልካለን ብቻ እንደዘንዶ የረዘመውን የዳገት መንገድ ተጉዘን ዘንባባ ዮሐንስ ስንደርስ ታቦቱ ሊወጣ ሕዝቡ ቤተ ክርስቲያኑን ከብቦት ነበር። የመጥምቁ ዮሐንስና የዮሐንስ ወልደነጐድጓድ አብያተ ክርስቲያናት የሚያወጉ ይመስል ጉንለጉን ዳገቱ ላይ ተተክለዋል። የመጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ሲሆን የዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ደግሞ በ1950ዎቹ ተሠርቶ ያለቀ ነው።

አባ ዘውዱ ስለአካባቢው ታሪክ ይነግሩኝ ዘንድ አንድ አባት እንዲፈልጉልኝ ነግሬያቸው አባ ማሞ የተባሉ የ80 ዓመት አዛውንት ፈልገው አገናኙኝ። በመጀመርያ ደስ አላላቸውም ነበር። «ወሬ ምን ያደርጋል» አሉኝ ደግነቱ አባ ዘውዱ «ቤተ ክርስቲያኑ ይረዳ ዘንድ ነው» ብለው ስለነገሩዋቸው ሊያነጋገሩኝ ፈቃደኛ ሆኑ እንጂ

አባ ዘውዱ ራሳቸውም ሆኑ የአካባቢው መነኰሳትና ሕዝብ እንደሚናገሩት ለብዙ ዘመናት በዚህ ቦታ የቆዩ የቅዱሳን አገልጋይ ናቸው። ይህ ገዳም በገዳምነት ሳይሠራ ከቤተ ክርስቲያኑ ሥር ባለው ዋሻ የሚወጡ ቅዱሳን ነበሩ ይህን ቤተክርስቲያን የሚቀድሱበት። የአካባቢው ሕዝብ የእነዚህን ቅዱሳን ሁኔታ እያየ ሊያምን ባለመቻሉ ከሌላ አካባቢ የመጡ ካቶሊኰች የሚቀድሱ ይመስላቸው ነበር።

በዚህ ቦታ አባ ማሞ ከዚያም ቀጥለው እማሆይ መዐዛ ማገልገል ጀመሩ። ወደ 1940ዎቹ መጨረሻ። እነዚህ ሁለቱ አገልጋዮች ለቅዱሳን እያገለገሉ እየተላላኩ ሲኖሩ የአካባቢው ሕዝብ ግን ካቶሊኰችን እያመጡ ያስቀድሳሉ እያሉ ስለሚያሙዋቸው በክፉ ዓይን ይመለከታቸው ጀመር።

በተለይ አባ ማሞ እንደነገሩን ብዙ ጊዜ የአካባቢው ሕዝብ ደብድቦዋቸዋል። ነገር ግን ሁሉን ችለው ተቀመጡ ቅዱሳንም በዚህ ቦታ አገልግሎታቸውን ቀጠሉ።

## ከቦረን ዋሻ እስከ እቴየ ማርያም መዳረሻ

ክፍል 2 – ከሐመር ዘጋቢ

ሐመር – ቅዱሳኑ ከየት አካባቢ ነው የሚመጡት?

አባ ማሞ – ከዚህ ከቤተ ክርስቲያኑ ሥር ካለው ዋሻ ውስጥ

ሐመር – ወደ ዋሻው ውስጥ ገብተው ያውቃሉ?

አባ ማሞ – አዎን ገብቻለሁ

ሐመር – ውስጡ ምን ይመስላል?

አባ ማሞ – በመጀመሪያ ስትገባ ደረቅ ነው መሐሉ ግን ሐይቅ አለው ተዚያ በኋላ ነው ቅዱሳኑ ያሉት እኔ እዚያ ድረስ ብቻ ነው የገባሁት

ሐመር – እንዴት ሊገቡ ቻሉ?

አባ ማሞ – እዚህ መጥተው ከቀደሱ በኋላ አብረን ገባን ተዚያ በኋላ እነሱ በውኃው ላይ ሲሄዱ እኔ ቀረሁ።

ሐመር – መቼ መቼ ነው የሚወጡት?

አባ ማሞ – በተለይ ምሽት ይወጣሉ

ሐመር – ወጥተው የት ይሄዳሉ?

አባ ማሞ – እዚያ ተራራው ላይ ይቀመጣሉ ሲቀመጡ ያን ጋራውን ይሞሉታል።

አባ ማሞ – የጠቆሙኝ ጋራ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ በኩል ያለ ዳገት ነው ከዚያ ላይ ነው ይቀመጣሉ ያሉኝ። ዛሬ ግን አባ ማሞ እንዳሉኝ ቅዱሳኑ መምጣታቸውን አቁመዋል። ከ3 ዓመት ወዲህ ምክንያቱን ጠይቄያቸው ነበር።



የዘንባባ ዮሐንስ ሁለቱ ቤት ክርስቲያኖች



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አባ ማሞ – የዚህ ሃገር ሰው ከፋባ ቸው መሬታችንን ሊወስዱ ነው እያለ

ሐመር – መሬታቸውን ለምን ይወስዳሉ?

አባ ማሞ – ገዳሙ ተበረታና ተቀና ብዙ መነኰሳት ያመጣሉ አዲያ ጠንቅቆ ይገደምና ቦታው ይወሰዳል ብለው

ሐመር – በዚያ ምክንያት ነው የቀሩት ማለት ነው።

አባ ማሞ – መነሻው ይኼው ነው ግና በኋላ ጃርት አለችበት ብለው ዋሻውን ደፈኑት

ዛሬም ዋሻው ተደፍኖአል ቅዱ ሳኑ ግን ለሚወዱት አልፎ አልፎ ይገለጻሉ። እንደ ድሮው ግን በብዛት መገለጻቸው ቀርቷል።

አባ ማሞን ስለ እማሆይ መዐዛ ጠይቄያቸው ነበር። ብዙ ተአምር ያዩ እናት ናቸው በተለይ ቤተ ክርስ ቲያኑን ለማሠራት በጣም ደክመዋል። ቅዱሳን ወደ አፄ ኃይለሥላሴ ብዙ ጊዜ ይልኳቸው ነበር። አንዴ እንዲ ያውም መኳንንቱ ምን አገባሽ ብለው ሽንት ቤት ውስጥ አሥረዋቸው ነበር። በኋላ ግን ንጉሡ ንዝንዛው እየበዛ ሲመጣና ልዩ ልዩ ሰዎችም ሲያመ ላክቷቸው ሰው ወስነው አሠሩት ነገር ግን የእማሆይ ሥራ የሀገሬው ሰው አልወደደላቸውም በአንድ ወቅት ችግር ገጠማቸው ይህን ጉዳይ በይበልጥ ያጫወተችኝ የእህታቸው የልጅ ልጅ ናት ደብረብርሃን ቅዱስ ጊዮርጊስ ተገናኘተን።

ሐመር – እስቲ እማሆይ መዐዛ ያጋጠማቸውን ነገር አጫውቺኝ?

ጽዮን – እማሆይ መዐዛ አንድ ጊዜ ወደ ንጉሥ ኃይለሥላሴ ተልከው ሲመለሱ የሀገሬው ሕዝብ መንገድ ላይ አገኙዋቸውና ወደገደሉ ወረወ ሩዋቸው

ሐመር – የት ገደል?

ጽዮን – ከቤተክርስቲያኑ ማዶ ያለው ገደል መንገዱ ዳር

ሐመር – ከዚያስ?

ጽዮን – ከዚያማ ሞተዋል ብለው ሲያዝኑ ሐዘናቸውን አውጥተው እንደተቀመጡ በወሩ ወደ ቤት መጡ። ቃላቸው ተዘግቷል ከሦስት ቀን በኋላ ሲከፈትላቸው ለአንድ ወር ያህል ከቅዱሳን ጋር አብረው ነበሩ። ሲወድቁ እነሱ ተቀብለው ወደ ዋሻው ወስደዋቸው አብረው ኖሩ በኋላ ልጆቼን አልተሰናበትኩም ብለው ስለ ነገሩዋቸው መልሰው አመጡዋቸው።

ሐመር – እማሆይ ዛሬ የት ነው ያሉት?

ጽዮን – ሐምሌ 28/በ83 ዓ.ም. አርፈዋል።

የቅዱሳን ማረፊያ መግለጫ የሆኑ ዋሻዎች እዚያ ቦታ ብቻ አይደለም የሚገኙት ከዘንባባ በስተሰሜን በኩል የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ከዚያ ሥርም ታላቅ ዋሻ እንዳለ አባ ማሞ ነግረውኛል። አንዴ እንዲያውም ወደ ሁለት ዓመት ገደማ ታቦት ከነ ልብሱ ከዋሻው ውስጥ ተገኝቷል። ወደ ውስጥ ገብቶ ለማየት የደፈረ የለም እንጂ ብዙ ቅርስ እንዳለው ይነገርለታል።

በአጠቃላዩ ግን በዚያ ቦታ እጅግ ምሥጢራዊ የሆኑ ቦታዎች አሉ። የአካባቢው ሕዝብና መነኮሳት ሲናገሩ እንደሚሰማው ብዙ ዋሻዎች ገና አልተደረሰባቸውም። በመሆኑም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ታሪክ ተመራማሪዎች ቦታውን ሊዳስሱት ይገባል። በጣም የሚያሳዝነው ነገር ግን ከቦረን ዋሻ ተነሥተን እስከ እቴየ ማርያም የምናገኛቸው ጥንታውያን አድባራት በሙሉ የሚተዳደሩት በመስቀል እህል (መስቀል ተይዞ የሚለመን) መሆኑ ነው።

የዘንባባውን ጉብኝት ጨርሰን ሐምሌ 1 ቀን ወደ ደብረ ብርሃን ጉዞ ሆን የዘንዶ ጉር ጊዮርጊስና የእቴየ ማርያም አድባራት በቀኝ ይገኛሉ በተለይም የእቴየ ማርያም ደብር ከተራራ ቁንጮ ላይ ስላለች መሰበ ወርቅ ትመስላለች ጠጋ ብዬ ታሪኳን ለመቃኘት ግን ጊዜ አላገኘሁም – ባይኔ ተሰናበትኳት።

ዘንባባ ዮሐንስ ክብረ በዓሉ ሰኔ 30 ቀን ነው የሚመጣው ግን ወጣቱ ትውልድ መሆኑ ያስገርማል። እናቶችና አባቶች ይህንን የቅዱሳን ማረፊያ የሆነ ገዳም በተቻላችሁ ለመ ሳለምና ለመርዳት ትጉ ወጣቱም የቤተክርስቲያንን በረከት ለማግኘትና ታሪኳን ጠብቆ ለማቆየት ቢበረታ በእጅጉ መልካም ነው ያለበለዚያ ትዝታ ሆነውብን እንዳይቀሩ ያሠጋል።

በሉ በሚቀጥለው ደግሞ ወደ መንዝ ላቀና ነው እግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን አንድ አስደናቂ ታሪክ ይዤ ብቅ እላለሁ ጸልዩልኝ ጉዞ ወደ... ✣



ከመሐል አባ ማሞ በግራ አባ ዘውዱ




©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል»

ከመምህር ሀብተ ማርያም ተድላ – የሊቃውንት ጉባዔ ም/ሰብሳቢ



ሥር ሳይምሱ፥ ቅጠል ሳይበጥሱ፥ መድኃኒት ቤቶችን ሳያስቡ፥ የትም ቦታ ሳይልከሰከሱ የሞት መልእክተኛ ከሆነም አስፈሪ በሽታ መዳን የሚቻለው የእግዚአብሔርን ስም በመጥራትና ትእዛዙንም በመጠበቅ ብቻ እንደሆነ የሰው ልጅ ሁሉ ሊያውቀና አውቆም ሊጠቀምበት ይገባል።

በመሠረቱ ልዑል እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው እንደመላእክት ሕያው ሁኖ ሲያመሰግነው እንዲኖር እንጂ በሕመምና በመከራ እንዲሠቃይ በሞት እንዲፈርስና እንዲበሰብስ አልነበረም፥ ሰዎች ራሳቸው ሞትን ጠሩት ጓደኛም አደረጉት እንጂ። (ጥበብ.1፥13–16)

ሰዎችም ሊሳሳቱ የቻሉት በመጥፎ አማካሪ በዲያብሎስ እንጂ በራሳቸው ፍላጐትም አልነበረም። ዲያብሎስ በተፈጥሮው ከረቂቃን መላእክት ሲሆን የመጀመሪያውን ሰው አዳምንና ሚስቱን ሔዋንን ሊያሳስት የቻለው ሥጋ ለባሽዋን እባብን መስሎ ነው። ዘፍ.3፥1–22።

ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን ላይ በፈጸመው የማታለል ተግባር ብቻ አልተወሰነም፤ የበለጠ ደባ የፈጸመው በልጅ ልጆቻቸው እስካሁንም ባለው ትውልድ ጭምር ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ርኩስ የሰውን ልጅ በመንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወቱ ላይ ሲፈታተን ኑሯል፤ አሁንም እየተፈታተነ ነው። 2ኛቆሮ.10፥4፤ 6፥10–20። ራእ.13፥1–18፥ ዮሐ.14፥30፥

አባታችን አዳም አቤል ከሞተ በኋላ ሴትን ወለደ፤ ሴት ማለትም ምትክ ማለት ነው፥ የሟቹ የአቤል ምትክ ነውና ሴት ሔኖስን ወለደ፥ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ስም፥ መጥራት ተጀመረ። እግዚአብሔር በጸፈጸፈ ሰማይ ሀያ ሁለቱን ፊደላት (አሌፋት) ሥሎ ለሔኖስ አሳየው በተቃራኒ ዲያብሎስም «ፔንሙ» በሚባል ጭፍራው ለሰው ልጆች ሟርትን ጥንቆላን፥ ምትሐትንና ዛር መሳብን የመሳሰሉትን ሁሉ አስተማረ፤ ከዚህ የተነሳ ኃጢአተ በምድር ላይ ነገሠች፤ የቃየል ልጆች በዝሙት፥ በክህደት ተበከሉ ሔኖ. 19፥16–29። ዘፍ.4፥25፤26።

የሴትም ልጆች ከእነዚህ ከቃየል ልጆች ተባበሩ፤ ኖሕ ብቻ (አንዱ ቤተ ሰብእ) የእግዚአበሔረን ትእዛዝ የሚጠብቅና ስሙን በሃይማኖት የሚጠራ ሆኖ ሲገኝ የሰው ዘር በሙሉ ለመናፍስት ርኩሳን ተገዢ ሆነ፥ ካደ፥ አመነዘረ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የጥፋት ውሀን በምድር ላይ አዘነመ። የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራና ትእዛዙን የሚጠብቅ ኖሕ ስምንት ራሱ ሲድን ስሙን ያልጠሩ ትእዛዙን ያልጠበቁ በእግዚአብሔር ልጅ «የተጠሉት የሴት ልጆችም በአንድነት ተደመሰሱ ዘፍ.7፥17–24።

የእግዚአብሔርን ስም ያቃለሉ ግብፃውያንና ንጉሣቸው ፈርኦን በዓሥር መቅሠፍትና በዓሥራ አንደኛ በባሕረ ኤርትራ ሥጥመት ሲቀጡና ሲደመሰሱ፥ የእግዚአብሔርን ስም የጠሩ እስራኤላውያን ግን በምድረ ግብፅ ከወረደው መቅሠፍት ነፃ ሁነው የኤርትራን ባሕር በተአምር ከሁለት ከፍለው ተሻገሩ። ዘፀ.7፥10–12፤29፥14፥21–30፤ 16፥11–6። የሐሥ.7፥26–28።

እስራኤል በአንድ ወጣት ኢያሱ አመራር የእግዚአብሔርን ስም መሣሪያ በመታጠቅ 31 ነገሥታትን ድል አድርገው ምድረ ርስት ኢየሩሳሌምን ወረሱ። የእግዚአብሔርን ስም ያቃለሉ ከነአናውያንና አጫፋሪዎቻቸው ግን ተማረኩ። ኢያ.9፥1። ም.12፥24።

እሥራኤል እግዚአብሔርን አምላካቸውን ትተው ነቢያተ ሐሰትን በመከተል በአምልኮተ ባዕድ አመነዘሩ፥ ነቢያተ ጽድቅ እነኢሳይያስ እነኤርምያስ የመሳሰሉት የሚነግሩአቸውና የሚያስተምሩአቸውን ቸል አሉ፥ ናቁ አቃለሉ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ትተው አሕዛብን ስለመሰሉ በአሕዛብ እንዲማረኩ ሆነዋል። 2ኛዜና.መ.28፥1–27። የእግዚአብሔርን ስም ባለመጥራታቸው ሕጉን ባለመጠበቃቸው ኢየሩሳሌም ተቃጠለች። ተመዘበረች፥ የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ ተዘርፎ ባቢሎን ገባ። በጠቅላላ የተቀደሰው የቤተ ማቅደስ ዕቃ ለቤተ ጣዖት ተደረገ። 2ኛነገ.25፥8–26። ኤር.25፥9፤26፥17–20፤50፥24–30፤ሰቆ.ኤር.1፥1–2።

እስራኤል በባቢሎን ምርኮ ሳሉ ንጉሥ ናቡከደነጾር «ዱራ» በተባለ ሜዳ ላይ 90 ጫማ ወይም 60 ክንድ ቁመት 9 ጫማ ወይም 6 ክንድ ወርዱ (ስፋት) ያለው ምስል አቆመና ሰው ሁሉ ለቆመው ምስል እንዲሰግድ አዘዘ፥ በትእዛዙ መሠረት ሰው ሁሉ ለጣዖት ተንበረከከ ሰገደ። «እናንያ አዛርያና ሚሳኤል» የሚባሉ እስራኤላውያን ወጣቶች ግን በእግዚአብሔር ስም ተመክተው ጸንተው «አንሰግድም» አሉ። ተጠርተው ወደ ንጉሡ ቀረቡ፥ ንጉሡ ተበሳጭቶና በቁጣ ተመልክቶ ወጣቶቹ ሲቀርቡ «እናንተ ሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ እኔ ላቆምኩት ለወርቁ ምስል አለመስገዳችሁ፥ የእኔን አምላክ አለማምለካችሁ እውነት ነውን? አሁንም የመለከቱንና የእምቢልታውን፥ የመሰንቆውንና የክራሩን፥ የበገናውንና የዋሽንቱን...ድምፅ ስትሰሙ ተደፍታችሁ ላቆምሁት ምስል ብትሰግዱ መልካም ነው፥ ካልሰገዳችሁ ግን በሚነድደው እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችሁ ከእኔስ እጅ የሚያድናችሁ አምላክ ማን ነው» በማለት በድፍረት ሲነግራቸው፥ በእግዚአብሔር ስም የተመኩት ወጣቶች ግን እምነታቸውን አጠነከሩ፥ «ንጉሥ ሆይ...የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው እሳት ያድነናል፥ ባያድነንም ላቆምኸው የወርቅ ምስል አንንበረከክም» አሉ (ዳን.3፥1–19።)

እዚህ ላይ ማስተዋል ይገባል፥ የወጣቶቹ እምነት እጅግ የጠነከረ ከመሆኑ የተነሳ በእምነት ለሚመስላቸው ሁሉ ከፍተኛ መልእክት አስተላልፈዋል፥ እሱም «እግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያድነናል፥ ባያድነንም ለጣኦት አንን በረከክም» ማለታቸው ነው። እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ፕሮግራም አለውና እነዚህ ወጣቶች በእሳት ተቃጥለው በሰማዕትነት ወደ እሱ የሚኸዱበት ጊዜ ከሆነ በደስታ መቀበላቸውን ሲያረጋግጡ ማንም ሰውም ቢሆን ራሱ በተመኘው ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖር «ይኩን ፈቃድከ» በማለት ፈቃዱን በደስታ እንዲቀበል እንጂ «እኔ ያልሁት ብቻ ይሁንልኝ በማለት ከእግዚአበሔር ፈቃድ እንዳይወጣ ነው።

በዚህ ጊዜ ንጉሡ እጅግ ተቆጣ፥ እሳቱ በይበልጥ ሰባት ዕጥፍ እንዲያይል ነዳጅ አስጨመረበት፥ ወጣቶቹ ልብሳቸውን እንደለበሱ እጅ እግራቸው ታስረው ወደ እቶኑ እንዲጣሉ አዘዘ። ኃያላን ተመርጠው ወደ ሚነድደው እሳት ወስደው ሲወረውሩ አቸው የእሳቱ ወላፈን ኃያላኑን (የሚወረውሩአቸውን) በላ፥ ገደላቸው፥ የእግዚአብሔርን ስም የጠሩት ሦስት ወጣቶች ግን ልብሳቸውም ሳይቀነብር በእሳቱ መካከል ሲንጐራደዱ፥ አራተኛም በመካከላቸው ቁሞ ነበር፥ የእግዚአብሔርን ስም ስለጠሩ ዳኑ፥ ኢዮ.2፥28–32፤ የሐሥ.2፥16–22።

ናቡከደነጾር ተመለከተና አደነቀ፥ ሦስት ሰዎች አስረን በእሳቱ ውስጥ ጥለን አልነበረምን? እነሆ አሁን አራት ሰዎች በእሳቱ መካከል አያለሁ እንዲያውም አራተኛው የእግዚአብሔር ልጅ ይመስላል አለ። ዳን.3፥19–26።

«አራተኛው የእግዚአብሔር ልጅ ይመስላል» የተባለው መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ነበር፥ ቅዱስ ገብርኤል በዚህ በታህሳስ ወር በ2 እና በ19 ዕለት በየዓመቱ የሚታሰበውም ይህ ንኑ በማስታወስ ነው።

ይህ መልአክ ሁል ጊዜ ስለሰው ልጅ ደኅንነት ከእግዚአብሔር ስለሚላክ «ሰው ገብርኤል» ይባላል፥ (ስለ ት ስብእተ ወልደ እግዚአብሔር) አምላክ ሰው ስለመሆን፥ ሰው ደግሞ አምላክ ስለመሆኑ የሚያበስር መልአክ ብሥራት በመሆኑም ብእሲ ወአምላክ (አምላከ ወስብእ) ይባላል።

ነቢዩ ዳንኤል ማቅ ለብሶና አመድ ነስንሶ ሲጸልይ፥ ስለራሱና ስለ እስራኤል ሲናዘዝ ይህ ድኅነትን የሚያበስረ መልአክ ሰው መስሎ ስለተገለጸለት «አስቀድሜ በራእይ አይቸው የነበረ ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ» ይላል። ነቢዩ የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ በመጸለዩ እስራኤል ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም የሚመለሱበትና ጠቅላላ የሰው ልጅ ድኅነት የሚፈጸምበት የመሲሕ ክርስቶስን መምጣት መሰቀል መሞት በመልአኩ ተረድቷል። ዳን.9፥3–26።

ሊቁ ቅዱስ ያሬድ «ገብርኤል ብሂል ብእሲ ወአምላክ እምኀበ እግዚአብሔር ዘተፈነወ ለእለ» ይለዋል። ይህም ገብርኤል ማለት ከእግዚአብሔር የተላከ ሰውና አምላክ ነው» ማለት ይሆናል። ስለዚህ ማንኛው ሰው የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ከሚያስፈራው ነገር ሁሉ እንዲያድነው ቢጸልይ መልአክ ምሕረቱን በመላክ እንደሚረዳው ሳይጠራጠር መጸለይ ይኖርበታል። የመላእክተ ምሕረት ተግባር ይህ ነውና።

## አሁን የዓለም ሕዝብ እንዴት ይድናል።

ዓለማችን የሰላም መልሕቅዋ ተሰብሮ ባለመተማመን ውቅያኖስ በመዋለል ላይ በምትገኝበት በአሁኑ ጊዜ፥ የዚህ ዓለም ጠቢባን ያልደረሱበትና መፍትሔ ያላገኙበት መቅሠፍት የሰውን ልጅ በመቁጣጠር ላይ ይገኛል። አሁንም ቀደም ወዳለው የሰው ልጅ ታሪክ ስንመለስ ሰብአ ትካት (የጥንት ሰዎች ማለት ነው) ሲበሉ ሲጠጡ፥ ሲሰክሩ ሲሰስኑ ሲየመነዝሩና ሲዘፍኑ ነው ማየ አይሕ ወርዶ የደመሰሳቸው። ማቴ. 24፥38–40፥ ሉቃ.17፥27።

ሰብአ ሰዶምም ተፈጥሮአቸውን ለውጠው፥ እግዚአብሔር በተፈጥሮ የሰጣቸውን የወንድና የሴት አንድነት መዋሐዱ ለውጠው ወንዱ በወንዱ ላይ ሲዳሩ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ አንድ ሎጥ ብቻ ሲድን እሳት ከሰማይ ዘንሞ ደምሰሷቸዋል። ዘፍ.19፥1–30።

አሁን በዚች ዓለም የወንድና ወንድ ጋብቻ በዓል ወሬ ዕለት በዕለት እየቀጠለ ይሰማል፥ የዚህ የኤድስ በሽታ መነሻውም ይህ እንደሆነ ታውቋል፥ ሰለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለውጡ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ። ወንዶች በወንዶች ነውር አድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ። እግዘኢብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይገባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው። ሮሜ.1፥26–29፤ ዘሌ.18፥22።

አሁን የሰው ልጅ ማስተዋል ያለበት ቀደም ሲል ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ በፈጸመው የዝሙት ሥራ «ቂጥኝ፥ ጨብጥና–ከርከር» የመሳሰሉ ደዌያት መጡበት፥ በቴክኖሎጂ ባፈራው ጥበብ መከላከል ሞከረ፥ ይህም ፐንሲልን፥ ሜጋቢልንና ጋብሮ ማሲናን የመሳሰሉ መድኃኒቶችን አዘጋጅቶ መከላከል ሞከረና አሁንም እግዚአብሔርን ትቶ እንደልቡ ይፈነጥዝ ጀመር።

ስለዚህ አሁን መድኃኒት የማይገኝለትን ኤድስን አመጣበት።

ሰለዚህ አሁን የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስና ስሙን ሳይጠራ «ሌላ መድኃኒት እፈልጋለሁ» ብሎ ጥረት ቢያደርግ፥ እግዚአብሔር አውሎ የማያሳድር ሌላ መቅሠፍት ሊያመጣ ስለሚችል ፍቱን መድኃኒቱ ሥር መማስና ቅጠል መበጠስ ሳይሆን ስሙን በመጥራት መጸለይና እሱ በተፈጥሮ በሰጠው ሕግ መሠረት አንዱ በአንዴት፥ አንዱ በአንዷ ተወስኖ መኖር፥ እሱን እያመሰገኑ ከፈቃዱ ውጭ ሳይሆኑ በጸሎት በመጠየቅና ስሙን በመጥራት ከእንዲህ ዓይነቱ ከባድ ፈተና ሁሉ ይድናልና (ሮሜ.10፥13) ኢዮ.2፥32፤ አን. 2፥4፤ ሮሜ.1፥17፤ ዕብ. 10፥30፤ ገላ.3፥11። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ዓምደ ወራዙት

የወጣቶች ዓምድ

## የምንፈልገው ኦርቶዶክሳዊ ወጣት

ከብፁዕ አቡነ ሙሴ

(የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ጉዳይ ጳጳስ)

በለብለብ ክርስቲያንና በኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን መካከል ትልቅ ልዩነት አለ ምክንያቱም ኦርቶዶክስ ማለት ርቱዕ በሃይማኖቱ፥ ርቱዕ በምግባሩ ነውና።

ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል የግሪክ ሲሆን ኦርቶ ማለት የቀና የተስተካከለ፥ ርቱዕ ማለት ሲሆን ዶክስ ማለት ደግሞ ሃይማኖት ማለት ነው። ኦርቶዶክስ ማለትም የቀና የተስተካከለ ርቱዕ የሆነ ሃይማኖት ማለት ነው።

### 1. ርቱዕ በሃይማኖቱ

የኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችንን ልዩ የሚያደርጓት የእምነት ባሕርያት አሏት

#### ሀ. የተረዳች ናት

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በትምህርተ ሃይማኖቷ፥ በቀኖናዋና በትውፊቷ እንከን አይገኝባትም ምክንያቱም ሐዋርያት በቃልም በጽሑፍም ያስተማሩትን በሙሉ ይዛለችና። 2ተሰ.2፥15። ይኸም ዘመኑ ‹የግንጥል ጌጥ›ን ትምህርት ይዞ ለሚያነሳቸው ምሥጢረ ሥጋዌ፥ ምሥጢረ ሥላሴ፥ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፥ የምልጃ ትምህርት፥ አጽዋማት፥ በዓላትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በበቂ ሁኔታ ለመመለስ አስችሏታል።

#### ለ. ርትዕት ናት

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት የሆነች፥ ያልተበረዘች፥ ያልተከለሰች፥ ያልወየበች ያልተጨመረባት፥ ያልተቀነሰላት፥ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝም ልክ ለኢያሱ እንደተነገረው (ኢያ.1፥7) ያላለች ርትዕት ቀጥተኛ ሃይማኖት ነች። አንዳንዶች ጭልጥ ብለው ሲከዱ ሌሎች ደግሞ እውነተኛውን መንገድ ለቀው በመሰላቸው ሰውኛ ፍልስፍና ሲመሩ እርሷ ግን ሐዋርያት እንደተከሏት ሳትዛነፍ በቅብብል (Apostolic Succession) ከኛ ደርሳለች። ሁለቱም ወገኖች ዛሬ ቢያስቡበትና ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ ተመልሰው ልብ ቢሉ ያለምንም ጥርጥር ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው በተመለሱ ነበር።

#### ሐ. ምልዕት ናት

ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት አንዱን ጥላ አንዱን አንጠልጥላ አትሄድም ስለ እምነት ስታስተምር ምግባርን አስተባብራ ነው (ያዕ.2፥26።) ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስታስተምር የእናቱን የቅድስት ድንግል ማርያምን የወዳጆቹን የሐዋርያትን፥ የጻድቃንና የሰማዕታትን፥ የቅዱሳን መላእክትን ክብርና ምልጃ ሳትዘነጋ ነው። ልጆቿ ቅዱሳት መጽሐፍትን እንዲማሩ ስታደርግ በራሳቸው ፈቃድ ሐረግ እየመዘዙ ሳይሰነጥቁ አባቶቻቸው ሐዋርያት ብሎም ከነርሱ በኋላ መንገዳቸውን የተከተሉ አበው ያስተምሩትን በመያዝ ነው። ምክንያቱም እኛ ክርሰትናን ተቀበልነው እንጂ አልጀመርነውምና የቀደሙትን ማየት ያስፈልጋል (ኤር.6፥16) ስለዚህ በመንገዱ መጓዝ እንጂ አዲስ ፈር አናወጣም።

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሥልጣነ ክህነት ስትሰጥ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ተሳትፎ ሳትንቅና የቤተ ክርስቲያን አካል መሆናቸውንም እያስተማረች ነው።

ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊት እምነታችን ምግባር ከሃይማኖት እንደ ዘይትና ክር አዋሕዳ የምታስተምር ናት።

#### መ. መጽሐፍ ቅዱሳዊት ናት

ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ለቀኖናና ለትውፊት ታላቅ ቦታ ትሰጣለች ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ያገኘችው በትውፊት (ከአባቶች በመቀበል ነውና) ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖትም ሆነ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመንፈስ ላነበባቸው ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ፥ ምሥጢረ ሥላሴ፥ ስለ ምልጃ ትምህርት፥ ታቦትና ቤተ መቅደስ –ትምህርቷ እውነተኛነት ይመሰክራሉ።

### 2. ርቱዕ በምግባሩ

የኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ልጆች ልዩ የሆነ የምግባር ባሕርይ አለን።

#### ሀ. የግል ጸሎት

ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ በጸሎት ከአምላካቸው ጋር መገናኘት አለባቸው። አንኳኩ ይከፈትላችኋል ተብሏልና (ማቴ.7፥7) ስለዚህ በቀን የተወሰነ ሰዓት መድቦ ስለራሱ፥ ስለሀገሩ፥ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፥ ስለ ዕለት ሥራው፥ወዘተ. መጸለይ አለበት። ጸሎት ኢየሱስ ክርስቶስ ካስተማረን አቡነ ዘበሰማያት ጀምሮ የአበው የመንፈስ ፍሬ የሆኑ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ትን የጸሎት መጽሐፍት፣ መዝሙረ ዳዊትንና ሌሎችንም ይጨምራል። (ዕብ.11፥7)።

ለ. የማኅበር ጸሎት

አባቶቻችን ሐዋርያት በኅብረት ሆነው ለጸሎት ይተጉ እንደነበረው (የሐዋ.8፥2) በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የምእመናን አንድነት እንዲኖር ጸሎተ ምሕላ፣ ጸሎተ ኪዳን፣ ሰዓታትና ማኅሌትን በመሳሰሉት የአንድነት ጸሎት ሥርዓቶች መካፈል አለብን።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለቅዳሴም ሆነ ለምሥጋና ሰዓት፣ ለዕለት ተዕለት የክርስቲያኖች የወንጌል ምግብነት ያመች ዘንድ መጽሐፈ ግጻዌ (የመጽሐፍ ቅዱስ የዕለት ምንባብ) ተዘጋጅቷል። ለምክር፣ ለተግሳጽ፣ ልብንም ለማቅናት በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይገባል። የዕለት ምግባችንን ስጠን ዛሬ የሚለው ጸሎት የሚያመለክተው እንጀራን ብቻ አይደለምና!

መ. ድርሳናትን ማንበብ

የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የጸድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው ምሳ.10፥7። በተባለው መሠረት ቅዱሳንን በተለያየ መንገድ ታስባቸዋለች። ስለ በረከታቸውም ታከብራቸዋለች። ከዚህም አንዱ ገድላቸውን፣ ተአምራቸውን፣ ጽፋ ለትውልድ ማውረሷ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን አበውን እየጠቀሰ በዕብራውያን 11 ላይ የእምነት ምሥክር እንዳደረጋቸው ሁሉ ይኼው ትውልድ የቅዱሳን አባቶችን ታሪክ፣ ገድልና ምክር በማንበብ መማር አለበት።

ሠ. ማስቀደስና መቁረብ

ጸሎተ ቅዳሴ በውስጡ 3 ነገሮችን ይዞአል። የነገረ መለኮት ትምህርት፣ ጸሎትና ቅዱስ ቁርባን ናቸው። ይኸውም በምሥራቃውያን (ኦርየንታል ቸርችስ) የመንፈሳዊ ዜማ ልህይ (Melody) የሚቀርብ ነው። ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ክርስቲያን በዚህ ጸሎተ ቅዳሴ ላይ መገኘት አለበት። ቅዳሴው «ይበል ካህን፣ ይበል ዲያቆን» እንደሚለው ሁሉ «ይበል ሕዝብም» ይላልና! በዚህ ሰዓት ተገኝቶ ትምህርቱን መማር፣ የጸሎቱ ሙሉ ተካፋይ መሆን በመጨረሻም ሥጋወ ደሙን መቀበል ይገባዋል።

ረ. መጾም

በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት አጽዋማት ይገኛሉ። የአዋጅ አጽዋማት (ኢዮ.1፥14) ረቡዕና ዓርብ፣ የሐዋርያት፣ የነቢያት፣ ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ፍልሰታ፣ ጾመ ነነዌ፣ ጾመ ገሐድ ከአባቶቻችን የወረስናቸው የኑሮ ፍሬዎች ሲሆኑ የእናታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን መከራዋን እያሰብን ፍቅራችንን የምንገልጽበት፣ በሐዋርያት በነቢያት፣ በጻድቃንና በሰማዕታት ፈለግ ለመሄድ እግዚአብሔርን እየጠየቅን ሕይወታቸውን የምንኖርበት የጌታችን የመድኃኒታችንን ስቃዩን መከራውን ለኛ ሲል የሠራልንን የፍቅሩን መግለጫ ሞቱን የምናስነብብበት ወቅት ነው።

የግል አጽዋማትም በፈቃድ ለጸጋ የሚደረጉና በምክረ ካህን፣ በትዕዛዘ ካህን፣ ለንስሐ የሚደረጉትን ያጠቃልላል። እነዚህም የኃጢአት መሠረት የሆነውን ዲያብሎስን ለመዋጋት የሚደረጉ ናቸው (ማቴ.17፥21፣ ሉቃ.2፥36–38) የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ልጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ሕግ በአባቶቻችን ሥርዓት እንደሚገባ መጾም ያስፈልገናል።

ሰ. በቤተ ክርስቲያን በዓል ላይ መሣተፍ

ሰሞነ ሕማማትን በመሰሉ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጸሎት፣ በጾምና በስግደት ቅዱሳን መጽሐፍትን በማንበብና በመዘመር በሚዋልባቸው መንፈሳዊ ሰሞናት የውጭ ተመልካች ሳይሆኑ ከበረከቱ መካፈል።

ሸ. ምክረ አበውን መቀበል

የቀደሙ አባቶች በመንፈሳዊው ጉዞ ብዙ ጸጋ አግኝተውበታልና፣ ከቃላቸውና ከሕይወታቸው ወጣቱ ብዙ ይማራል። ስለዚህም ሊቃውንትና ካህናትን፣ ቀርቦ መንፈሳዊ ምክራቸውን ተጋድሎዋቸውንና ትምህርታቸውን መማር ያስፈልጋል። ጢሞቴዎስ ያደገው በጳውሎስ ምክር ነው። ለጢሞቴዎስ የተላከው መልእክት ጳውሎስ በመንፈስ በተጓዘበት ጎዳና ያገኘውን ትምህርት ለልጁ ያካፈለበት ነው።

በዚህ ዓይነት መንገድ አባቶች ካወጡት ሥርዓት ጋር አንድ ሆነን በእምነትም በምግባርም ኦርቶዶክሳውያን መሆን እንችላለን! በዚህም እግዚአብሔርን እያከበርን በፍቅሩ እቅፍ ውስጥ እንገባለን ነገር ግን በጭፍን ሞራል (fanaticism) አይደለም። ሁሉንም በፍቅር እንቀርባለን ነገር ግን ከእምነታችንና ሥርዓታችን እንዲሁም ትውፊታችን ለሰው ስንል የምንተወው አሊያም የምንለውጠው አይኖረንም። ✣

ምንጭ ኢልከራ።
ቅጽ 2 ቁ.4 – ገጽ 4
ውርስ ትርጉም በዝግጅት ክፍሉ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው።» እንዴት?

ከዲ. ተክለ ወልድ

ባለፈው እትማችን የዚህን ርዕስ ትርጓሜ በሚገባ ካብራራን በኋላ በዚህ ርዕስ ተከልለው በተራ ቁጥር 1 ላይ መዳን የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ አይደለም በማለት ላስቀመጡት አግባብ ያልሆነ ትምህርት ቃል በቃል በሰፊው መልስ ሰጥተንበታል።

ለተቀረው ደግሞ በቁንጽል ሳይሆን በስፋት እንደሚከተለው መልስ እንሰጥበታለን። 2ኛ. መዳን በተግባር አይደለም ብለው በመደምደም ኤፌ.2፥8ን በመጾም በመመጽወት ወይም ግብረ ገብነትን በመፈጸም አንድንም በማለት ሉቃ.18፥9–14 ያለውን ጠቅሰዋል። ወገኖቼ እስቲ አስተውሉ? በጐ ምግባር ጸሎት ምጽዋት (ድሆችን መርዳት) – ግብረገብነት (መልካም ባኽርይ) ማለትም በገላ.5፥22። የተዘረዘሩትን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጐነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት የተባሉትን እነኚህን አፍርቶ መገኘት የማይጠቅምና የማያስፈልግ ከሆነ የክርስትና ትርጉሙ ምንድነው? ሰውስ በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አዳኝነት ፈራጅነትና ዳኝነት በማመን በጐ ካልሠራ ካልመጸወተ፥ ካልጾመ መልካም ባሕርይ ከሌለው የመዳን ምሥጢሩ ምንድነው? እንግዲያውስ አምኛለሁ የሚል እምነቱ በተግባር ያልተገለጠ ሰው ይድናል ማለት ነው? አልጾምም ብሎ ለሆዱ የሚገዛ አልመጸውትም ብሎ የሚስገበገብ ግብረ ገብነት የሌለው መደዴና ምግባረ ብልሹ ይድናል ማለት ነው?

እረ ለመሆኑ ኤፌ.2፥8። የሚያስተምረን ምንድነው? «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። እንጂ ከእናንተ አይደለም። ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።» ይላል። ጸጋ ማለት ቸርነት ምሕረት፥ በጎነት፥ ያለ ብድራትና ያለ ዋጋ የሚደረግ ስጦታ ማለት ነው። በመሆኑም በመስቀል ላይ የተፈጸመው ቤዛነት (የማዳን ሥራ) የእግዚአብሔር ጸጋ (ስጦታ) መሆኑን የሚያመለክት ነው። በእርሱ የባሕርይ አምላክነት የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና የተባለው ለዚህ ነው። ዮሐ.3–16። ቅ.ጳውሎስም በሮሜ.5፥10። ላይ «ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወት እንድናለን።» በማለት እግዚአብሔር አምላካችን እኛን ጠላቶቹን በጸጋው (በቸርነቱ) እንዳዳነን ተናግሯል። ቅ.ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ በቸርነቱ በሃይማኖት ድነናል። ያዳነንም የእግዚአብሔር ቸርነት ነው። እንጂ እናንተ በሙያችሁ በጉልበታችሁ እኛም በሙያችን በጉልበታችን አይደለም። ሲል «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና።» አለ። ይኸንንም ያለው «ከመ አልቦ ዘይትሜካህ» በሙያዬ በጉልበቴ እያለ የሚመካ እንዳይኖር ነው። እንጂ በጐ ምግባር አያስፈልጋችሁም ማለቱ አይደለም። የቆሮንቶስን ሰዎች በመጀመሪያ መልእክቱ በምዕ.1፥29 ላይ «ከመ ኢይትመካህ ኩሉ ዘሥጋ በቅድመ እግዚአብሔር» እግዚአብሔር በሚያውቀው ነገር ሥጋዊ ደማዊ ሰው ሁሉ ጥበበኛ ነኝ ኃይለኛ ነኝ፥ ዘመዳም ነኝ፥ እያለ እንዳይመካ የሚመካ ቢኖር በእግዚአብሔር ይመካ ብሎ እንደመከራቸው የኤፌሶን ሰዎችንም በእግዚአብሔር መመካትን ሲያስተምራቸው ነው።

ስለዚህ የሰው ልጅ የዳነበትን ምሥጢር እያሰበ በመስቀል ላይ በተፈጸመለት ቤዛነት እየተመካ በእምነት እንዲቆም በምግባር እንዲጸና ማበረታታት ነው እንጂ በጐ ምግባር አያድንህም ብሎ ማሳነፍ የክርስትና ትምህርት አይደለም። ጠላታችን ሰይጣን ዛሬ ምግባር አያድንህም ብሎ ካሳተን በኋላ ነገ ደግሞ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ ማመን አለማመን ትርጉም የለውም አሰኝቶ እምነታችንንም እንዳያስጥለን እንጠንቀቅ።

በጐ ምግባር እንደሚያስፈልግ ሐዋርያው ቅ.ያዕቆብ በምዕ.2፥14–26። በሰፊ ዘርዝሮ አስቀምጧል። ሐዋርያው ተግባር አያድንም ብሎ አላስተማረም። «ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል፥ እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ ከእናንተ አንዱም:- በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።» በማለት እምነትን ከምግባር ማዋሐድ ጠቃሚ መሆኑን አስተምሯል። እምነትን በተግባር ማሳየት ይገባል። ለማመንማ አጋንንትም ያምናሉ። ችግሩ በጐ ተግባር የላቸውም። እንግዲህ ተግባር አያድንም ብሎ መስበክ አጋንንትን ምሰሉአቸው ብሎ ማስተማር ነው። ይህ ደግሞ በክርስቶስ እናምናለን ብለው ከሚመኩ የሚጠበቅ አይደለም። ዳሩ በክርስቶስ ላይ ያላቸው እምነት ጐደሎ ከሆነ ሰዎች መልካም ነገር አይጠበቅም። ከእሾህ ወይን፥ ከኩርንችት በለስ አይለቀምለትምና ማቴ.7፥17።



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

ቅ.ያዕቆብ በቁ:20 ላይ «አንተ ከንቱ ሰው እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?» እንዳለው ዛሬም ተግባር እንደማይጠቅም የሚናገሩ ሁሉ ከንቱዎች ናቸው። አብርሃም በእምነት ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራው ጸደቀ። ዘፍ.22፥9–18። ቅ.ያዕቆብ በዚሁ ምዕራፍ ከቁ.24–26 ድረስ «ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁም ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።» ብሏል። እንግዲህ ሰው በሥራው ሳይመካ በእግዚአብሔር ጸጋ እየተመካ በበጎ ተግባር መጠመድ አለበት።

ጌታችን በወንጌል «መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል። ወደ እሳትም ይጣላል። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።» ብሏል ማቴ.7፥19–20። ፍሬ የተባለው ምግባር ነው። ፈቃዱም በጎ ምግባርን መሥራት ነው። በቆላ.3፥17። «በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።» እንደ ተባለ ማናቸውንም ሥራ የምናከናውነው በስሙ ነው። በቁ.23 ደግሞ «ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት። ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና።» ተብለናል። ስለዚህ ለበጎ ተግባር እንተጋለን።

ቅ.ጳውሎስ ከአዳም ኃጢአት ከሲኦል ባርነት እና ከዘላለም ሞት የዳንነው ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ቤዛነት መሆኑን ሲነግረን «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና» አለ። ዛሬም ቢሆን ወደ ክርስትና ያልመጡ አሕዛብም ሆኑ በግብረ አሕዛብ ጸንተን የምንኖር ኃጢአተኞች ከኃጢአት የምንድነው ክርስቶስ በመስቀል በፈጸመልን ሥራ ነው። ዮሐ.19፥30። እንግዲህ ወደ መስቀል ስንመጣ ክፉዎች ክፉ ተግባራችንን ጥለን በጐዎች ደግሞ በጐውን ተግባራችንን ይዘን ነው። በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አምነን ከኃጢአት ከዳንን አዲስ ሕይወት ይኖረናል። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው።» 2ቆሮ.5፥17። ይህን አዲስ ሕይወት እንዳገኘን ለማሳየት መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሆኖ መልካም ሥራ እንድንሠራ ያደርጋል። ገላ.5፥22–23። እምነታችን በመልካም ሥራችን ይገለጣል። መልካም ሥራ የእምነት ፍሬ ነው። እምነት መልካም ሥራን ያስከትላል። መልካም ሥራ ብርሃን ነው። «መልካም ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» ማቴ.5፥16። ቅ.ጳውሎስ በ2ኛ ተሰ.2፥16–17። «ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የወደደን በጸጋም የዘላለምን መጽናናት በጎንም ተስፋ የሰጠን እግዚአብሔር አባታችን ልባችሁን ያጽናኑት በበጎም ሥራና በቃል ሁሉ ያጽኑአችሁ።» ሲል የተሰሎንቄን ሰዎች መርቋቸዋል። ቅ.ጴጥሮስም «ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጐበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።» ብሏል 1ኛ ጴጥ.2፥12።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል በምዕ.18፥14 ድረስ ያስተማረውን ትምህርት ለማን? እና ለምን? እንዳስተማረ በግልጥ ተቀምጦ እያለ የማይገባ ነገር መናገር ወይም ለክህደታቸው ደጋፊ ጥቅስ አድርጎ ማስቀመጥ ተገቢ አይደለም። ጌታ ያስተማረው በምሳሌ ነው። ትምህርቱም በቁጥር 9 እንደ ተጠቀሰው ጻድቃን እንደሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ሰዎች ነው። ራስን ማመንና ሌላውን መናቅ ከክርስትና ሕይወት ውጪ በመሆኑ ክርስቶስ አላስፈላጊነቱን ተናገረ። ዛሬም ቢሆን በሥራቸው የሚታመኑና የሚታበዩ ካሉ ጽድቃቸው የደም ጨርቅ ነው። ምክንያቱም የክርስትና ሕይወት የትህትና እንጂ የትዕቢት አይደለምና ነው። ፈሪሳዊው ሰው በቤተ መቅደስ ቆሞ «እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞች ዓመጸኞች አመንዝራዎች ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ። በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ። ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ።» እያለ በእግዚአብሔር ቸርነት ሳይሆን በሥራው ሲመካ ተገኘ። ቀራጩ ግን ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሳ እንኳ አልወደደም። ነገር ግን «አምላክ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ።» እያለ ደረቱን ደቃ ራሱን አዋረደ። በእግዚአብሔር ምሕረት ተመካ። ከፈሪሳዊውም ይልቅ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ከመሰለ በኋላ «ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና። ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል» አለ። ጌታ በምሳሌ ለማስተማር የፈለገው ትዕቢት እንደሚያዋርድ ትህትና እንደሚያከብር ነው። ከዚህ ውጭ የወንጌሉን አሳብ ሳይረዱ ምግባር አያድንም ብሎ መስበክ ሰውን በጐ ምግባር አትሥራ ብሎ እንደመከልከል ይቆጠራል።

ስለ ምጽዋትም ቢሆን በሚቀጥለው እትማችን በሰፊው እንደምንጽፍ ቃል እየገባን ለዛሬው ግን በአጭሩ ለማስቀመጥ ያህል። ጌታ «የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድረግ?» ብሎ አንድ ሰው በጠየቀው ጊዜ ትዕዛዛቱን እንዲጠብቅ ነገረው ጐበዙ ግን «ይህንንማ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ጠብቄአለሁ። ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው?» በማለቱ ጌታችን መልሶ «ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ» በማለት ያለውን ሁሉ ቢመጸውት ፍጹም እንደሚሆን ነገረው። መመጽወት ማለት ለድሆች መራራት ማለት ነው። በሉቃ.6፥36 » አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩሆች ሁኑ። እንተደባለው ለመመጽወት ርኅራሔ ያስፈልጋል እንግዲህ መመጽወት የሰማዩ አባታችን ለፍጥረታቱ እንደሚራራ ርኅሩኅ ሆኖ መገኘት ነው። ሌላው ደግሞ ጾምን በተመለከተ በጥያቄዎቻችን ዓምድ ላይ የተመለከትነው ጉዳይ ስለሆነ እዚህ ላይ አንደግመውም። እንግዲህ እንደ ፈቃዱ ይኼንን ያህል ግንዛቤ ካገኘን በእምነት እንድንቆም በምግባር እንድንጸና በጾምና በጸሎት እንድንወስን የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን። ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

## ክርስቲያናዊ ቤት

ከዳንኤል ክብረት

የመጀመሪያዋን የመኖሪያ ቤት የሠራት ልዑል እግዚአብሔር ነው። አዳምና ሔዋንን ከፈጠረ በኋላ ትዳራቸው የሚሞቅበት ኑሮአቸው የሚሠምርበት ጐጆ ቀለሰላቸው። ያችም እጅግ ያማረችና የተዋበች በወንዞች ተከባ በአትክልት ያሸበረቀች ገነት ነበረች።

እግዚአብሔር አምላክ የሰው ልጅ ውሱን የሆነ የተለየ መኖሪያ እንደሚያስፈልገው በመወሰኑ እንጂ ምድር ሞላዋ የተሰጠችው ለሰው ልጅ ነበር።

ዛሬም የልዑል እግዚአብሔርን አርአያ ተከትለን ጐጆ ስነወጣ ትዳር ስናሞቅ የአንገት ማስገቢያ የእግር ማጠፊያ ቤት እንቀልሳለን። የኑሮ ማሟያ፥ የፍላጐት ማርኪያ የሆኑ ቁሳቁስ እናስገባለን።

የቤትን አቋምና ትርጉም በትክክል ለመረዳት የመጀመሪያዋን ቤት ቀያሽ የአቀያየስ ሁኔታ መመልከቱ በእጅግ ይጠቅማል። ልዑል እግዚአብሔር ለማየት ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ በዚያን ቤት አስቀምጦ ነበር። ዘፍ.2፥9። ለመብላት መልካም የሆኑ ነገሮች የሞሉባት ነበረች። ዘፍ.2፥9።

ዛሬም የልዑል እግዚአብሔር ልጆች የሆንን ክርስቲያኖች ቤታችን የመጀመሪያዋን ቤት መምሰል አለባት። ያቺ ቤት ሉቦናን የምታረካ ዓይንን የምትማርክ ነበረች። የእኛም ቤት በሸረሪት የታጠረ በጢስ የጠቆረ መሆን የለበትም። ያ ከሆነ ግን ለሰው የተዘጋጀ ቤት ልንለው አንችልም። አንዳንድ ጊዜ ቤታችን ከውጭ ገና ሲያዩት ቀለሙ የተፋቀ፥ ግድግዳው የተሰነጠቀ በርና መስኮቱ የወለቀ ሆኖ ይገኛል። ምንም እንኳን ቤታችን የምንፈልጋትን ያህል ለማማር ባትችል ድኅነታችን ጐድቷት አቅማችን አላቃና ብሏት ብትቸገርም በተቻለ መጠን ቤትነትዋን ልንጠብቅ ያስፈልጋል።

የክርስቲያን ቤት እንግዳን ከውጭ የሚጋብዝ መሆን አለበት። አብርሃም እነዚያን ሁሉ እንግዶች ሊቀበል የቻለው በቤቱ አጠገብ እንግዶችን የሚስብ ከመስቀለኛው መንገድ ዳር የተሠራች የመምሬ አድባር የእንግዶች ማረፊያ ስለነበረችው ነው። መልካምና የሚስብ መዓዛ ያለው አበባ ባለበት ሁሉ ንቦች አይጠፉም። ከሩቅ ይጠራቸዋልና።

በመልካም ሁኔታ ተሠርቶ ለእንግዶች ዓይን የሚማርክ ቤትም የእንግዳ በረከት አይጠፋበትም። ቤት ያምራል ሲባል በቀለም አሸብርቆ፥ በዕቃ ተጨናንቆ በመብራት ደምቆ ይታያል ማለት ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ ሕይወት ሰላም ያለው ለቃለ እግዚአብሔር የተገዛ ነው ማለታችን ነው። ልጆች ለወላጆች ታዛዥ ሆነው ባደጉበት ያገኙትን እየተሳደቡ ሰው በማያሳቅቁበት ወላጆች እንግዶችን በሆድ ሳያማረሩ በፈገግታ በሚቀበሉበት ቤት እንግዶች ሰላመ እግዚአብሔር አቀርበው ለማስተማር፥ ለመባረክ፥ ለበረከት ይዘልቁበታል።

ያማረና የተዋበ ቤት ማለት የኢኮኖሚ ደረጃው የተጠበቀ ማለት ብቻ አይደለም። ግቢው ለአበቦች የታደለ ከወሬ ይልቅ ለሥራ የሚጋብዝ፤ ቢቻል የጓሮ አትክልት የሚለሙበት፥ ከብቶች ሰዎች ከነገር ከሽኩቻ ከሐሜት ርቀው መዋያ ይሆኑ ዘንድ የሚፈነጩበት ማለት ነው እግዚአብሔር በሠራት በዚያች የገነት ውብ ቤት ሰውን የሚያበሳጭ አለያም ደስታውን የሚቀንስ አንዳች አልነበረበትም በክርስቲያኖች ቤትም የስንፍና መግለጫ የገመና ማውጫ የሆኑ ነገሮች መታየት የለባቸውም እንደ አቅማችን ጥራቱና ይዘቱ ያማረ መሆን አለበት።

ባልና ሚስት ከሥራ ሲወጡ ቤታቸው ሊናፍቃቸው ውጡ ውጡ ላያሰኛቸው ይገባል። ልጆቻቸውን ሰብስበው አርፈው የሚዘምሩበት፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያነቡበት መሆንም አለበት። ቤታቸው እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን እንጂ እያነጫነጨ የሚያማርር መሆን አይገባውም።

በዚያች ልዑል እግዚአብሔር በሠራልን የመጀመሪያ ቤታችን ውስጥ ሁሉም ነገር የተሟላ ነበር። የክርስቲያኖች ቤትም በሁሉም ነገር ሙሉ ሊሆን ይገባዋል። ይኸውም ማለት ከአቅም በላይ በሆኑ የቅንጦት ዕቃዎች መታጨቅ፥ በሸቀጥ መታመቅ ማለት ሳይሆን ለኑሮ–በኑሮው መጠን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች መኖር አለባቸው።

ምክንያቱም የክርስቲያን ቤት መሠራት ያለበት ከድሎቱ አንጻር ብቻ ሳይሆን ከክርስቲያናዊ ሕይወቱ አንጻር ጭምር ነው። ለእንግዶች ማረፊያ፥ ለጸሎት ቦታ፥ መወሰን ይገባቸዋል። እግዚአብሔር በረከቱን የሚሰጠን እንደ ዝግጅታችን ነው። የልብ መዘጋጀት ከሰው የምላስ መልስ ከእግዚአብሔር ነውና! ምሳ.16፥1።



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

የክርስቲያን የቤት አቀማመጥ ማንነቱን የሚገልጽ መሆን አለበት። በቤቱ የሰቀላቸው፣ በግድግዳው የለጠፋቸው ሥዕሎች ከክርስትና ሕይወት ውጭ አጉል ፍልስፍናን፣ ዝሙትን የሚያንፀባርቁ፣ ጥቅሶቹ የሰውን ሥነ–ልቡና ሰልበው ለዓለማዊ ሕይወት አሳልፈው የሚሰጡ፣ ፖስት ካርዶች ዳንስ ቤት የሚያስመስሉት ከሆኑ ቤታችን የገነት ነፀብራቅ ሳይሆን የሲዖል ማስታወቂያ ሰሌዳ መሆኑን መገንዘብ አለብን።

በክርስቲያኖች ቤት ሊኖሩ የሚገባቸው ሥዕሎች የቅዱሳንን ገድል፣ የወንጌልን በረከት የሚያስተ ምሩ፣ ጥቅሶቹ መንፈስን የሚገነቡ ከዚህ በተረፈ ቢበዛ መልከዐ ምድ ርን፣ የተፈጥሮ ውበትን ግን– ከክር ስትናችን የማይወጡ ሊሆኑ ይገባል።

የክርስቲያኖች ቤት ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው። ለዚህም ነው ዛሬ ተረሳ እንጂ «ቤት የእግዚአብሔር ነው» ይባል የነበረው። በመሆኑም ቤታችን የእግዚአብሔር፣ እግዚአብ ሔር የሚመሰገንበት፣ ጸሎት የሚደ ረስበት፣ ቴፓችን አሸሸ ገዳሜ እንካ ሰላንትያ ከሚል ይልቅ መንፈሳዊውን መዝሙር የሚያሰማበት፣ ልጆቻችን ቅዱሳት መጽሐፍት የሚማሩበት ቢሆን መልካም ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች የያዙዋትን ቤት በንጽሕና በጤና፣ በቅድስና መያዝ ሲያቅታቸው በድህነታቸው፤ ቤቱ ሰፊ፣ ያማረና በዕቃ የተሞላ እንደ ጐረቤታቸው ባለመሆኑ እግዚ አብሔርን ያማርራሉ። ግን ወገኖቼ ወጣ ብላችሁ በምሽት ሰዓት በየመንገዱ፣ በየበረንዳው፣ በየጥጉ የተኙትን ቤት አልባዎች ተመልከቱ እስቲ! በክረምት ብርዱና ዝናሙ፣ በበጋ ነፋሱ ሲያንገበግባቸው፤ መድረሻ አልባዎች! ታዲያ እኛ እግዚአብሔርን ልናማርረው ይገባ ይሆን? የአገኘናትን በአቅማችን ከጠበቅናት በጸሎት ከባረክናት፣ በፍቅር ካሞቅናት በቂ ናት። እግዚአብሔር እኮ በአብርሃም ድንኳ ንም ተገኝቷል! በስምዖን ቪላ ቤት ብቻ አይደለም።

ክርስቲያን እንደ አባቱ እንደ እግዚአብሔር በሥራው እንከን የለ ውም። ክርስቲያናዊት ሚስት ሙያዋ ያማረ፣ የቤት አያያዝዋ፣ የልጅ አስተ ዳደግዋ፣ የሠመረ መሆን ይገባዋል። ይኼም በአካባቢዋ ክብርን በባልዋ ዘንድ ፍቅርን፣ በእንግዶችዋ ዘንድ ሞገስን ያጐናጽፉታል። የዕቃዋ አቀ ማመጥ ሥርዓት የያዘ፣ ያልተዝረከረከ ቅዱስ ጳውሎስ «ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን» እንዳለው (1ቆሮ.14፥40) የምግብ አሠራርዋ ሥርዓት፣ አለባበስዋ ክርስቲያንነቷን የሚመሰክር ቢሆን መልካምነት አለው «መልካም ሚስት ለባልዋ ዘውድ ናትና»

እናት በልጅዋ ሕይወት ትልቁ ፀሐይ ናት። በመሆኑም ልጆች ለእና ታቸው ልዩ ፍቅር አላቸው። ዘወትር ቃለ እግዚአብሔርን የምታስተም ራቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን የምት ወስዳቸው ከሆነች እግዚአብሔርን መፍራት ቤተክርስቲያንን መውደድ ከልጅነታቸው ተቀርጾባቸው ያድ ጋል...ብልሃተኛ ሴት ቤትዋን ትሠራለች ነውና ምሳ.14፥1።

ክርስቲያናዊ ባልም ቢሆን በጊዜ ወደ ቤቱ የሚገባ፣ ቤተሰቡን በፍቅር የሚመራ፣ ልጆቹን የሚንከባከብ የሚ ያስተምር ለቤተ ሰቡ በመንፈሳዊ ሕይወቱ፣ በሰው አከባሪነቱ መልካም አርአያ ባለቤቱን በሥራ የሚረዳ እንጂ እርሱ ሰክሮ እየገባ ባለቤቱ ላይ የሚደነፋ ልጆቹን በፍርሃት የሚያሸ ማቅቅ መሆን የለበትም። ምክንያቱም ንፁሕ ሕሊና ይዘው የተወለዱት ሕፃናት «እኔም እንደ አባዬ» እያሉ እኩይ ምግባር ተከትለው ያድጋሉና! ቤቱም የመንፈስ እግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ የሰይጣን ስሜትና ፍላ ጐት መፈንጫ ይሆናል።

ክርስቲያናዊ ቤት አንድ ጊዜ አይሠራም። ሲሰራ ይኖራል እንጂ! ልዑል እግዚአብሔር ገነትን ከፈጠረ በኋላ ለአዳምና ለሔዋን ዝም ብሎ አላስረከባቸውም። «ያበጃትም ይጠ ብቃትም ዘንድ» እንጂ ዘፍ.2፥17። በመሆኑም ቤታችን ዘወትር አዲስ እንጂ ዕቃዎቹ በስንፍና የወየቡ፣ አቧራ የጠገቡ፣ በቆሻሻ የነተቡ የሸረሪት ሠፈራ ፕሮግራም የተካሄ ደባቸው ከሆኑ ማበጀት መጠበቁን ዘንግተነዋል ያሰኛል።

እግዚአብሔር ትዕዛዙን ሲሰጥ ለአዳምና ለሔዋን እንጅ ለግል የሰጠው የለም። ‹ጠብቁ ተንከባከቡ› ተባሉ እንጂ ሔዋን በሚስትነትዋ ብቻ ጠብቂ አልተባለችም። በመሆኑም ቤትን በማሣመር አያያዙን በማስተካ ከል፣ ረገድ ባልና ሚስት እኩል ኃላፊነት አለባቸው።

ቤቱ ሲበላሽ እየተመለከተ ለሚ ስቱ ኃላፊነቱን ጥሎ የሚቀመጥ ባል አደራውን በልቷል ማለት ነው።

ቤትን የማሣመሪያው ትልቁ ቀለም ቤተሰባዊ ፍቅር ነው። እርቶ ዶክሳዊ ቤተሰብ በፍቅር የተገነባ ነው። በእናትና አባት፣ በወላጆችና ልጆች፣ በቤተሰብና በጐረቤት መካከል ፍቅር ይገኝበታል። በቤት ውስጥ ሰላም፣ ፍቅርና መተሳሰብ ካለ የቤት ዕቃዎ ችን አቅማመጥ በመለወጥ ብቻ ቤትን አዲስና ማራኪ ማድረግ ይቻላል።

በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ የሚከተሉትን ነጥቦች ቢያጤን መልካም ነው።

- የቤተሰብ ፍቅር የኑሮ መሠረት ነው።
- የክርስቲያን ቤት የክርስቲያንነቱ ነፀብራቅ መሆን አለበት
- የክርስቲያን ቤት የሚዘጋጀው ከክርስቲ ያናዊ ሕይወት አንጻር እንጅ ለድሎት ብቻ አይደለም።
- ቤተሰብን በመጠበቅ፣ በመንከባከብ ኃላፊነት ያለባቸው ባልና ሚስቱ በእኩል ደረጃ ነው።
- የክርስቲያኖች ቤት ቅዱሳት ሥዕሎች በተ ገቢው ቦታ ለጸሎት የሚገኙበት፣ ልጆች በቅዱሳን መጻሕፍት የሚታነፁበት ነው።
- የክርስቲያን ቤት የቅዱሳን ማረፊያ፣ የወንጌል መስፋፊያ፣ የካህናት፣ የዲያቆ ናት፣ የሊቃውንት መፍለቂያ ነው።

እንዲህ ከሆነ እንደ አብርሃም ቤት በእግዚአብሔር ይጐበኛል፣ በቅዱሳን ይባረካል፣ ከጠብ ከንዝንዝ፣ ይር ቃል። በፍቅር የፀና በምግባር የቀና ነውና–የጻድቅ ቤት ፀንቶ ይኖራል። (ምሳ.12፥7።) ✣



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# በረከተ ወንጌል

## ይህ ሕፃን ምን ይሆን?

ሉቃስ.1፥57–66።

ከዜና ድንግል

ባለፈው እትማችን የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን ጸሎት በመተንተን ሳይሆን አንዱን ሐረግ መዝዘን ወንጌልን መማራችን ይታወሳል። ዛሬ የምናገኘው የመጥምቀ መለኮት ዮሐንስን ዜና ልደት ነው። በእግዚአብሔር ተአምራታዊ ፈቃድ ይሁን ከተባለ ሊሆን የማይችል አንድ ስንኳ እንደሌለ ቅዱስ መጽሐፍ በተደጋጋሚ ያስተምረናል። «አልቦ ነገር ዘይስአኖ ለእግዚአብሔር፥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።» እንዳለ። ዘፍ. 18፥14። ሉቃ.1፥37።

የዚህ የመጥምቁ ዮሐንስ ልደትም የሚያስተምረው ይህንኑ የእግዚአብሔርን ሁሉን ነገር ለማድረግ መቻል ነው። አስቀድሞ እንደተማርነው በቤተ መቅደስ ለካህኑ ዘካርያስ የተገለጠለት የእግዚአብሔር መልአክ እንደነገረው እንደበቱ ተዘግቶ የተባለውን ሕፃን መወለድ በሚጠብቅበት ጊዜ የሚስቱ የኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰና ወለደች። በአይሁድ ልማድ ልጅ ሳይኖራት በመቅረቱ እንደ ኃጢአተኛ ተቆጥራ ጣት መጠቋቆሚያ የሆነችው ኤልሳቤጥ ዛሬ እፍረቷ ተወግዶላት እግዚአብሔር ያደረገላት ቸርነት በሰዎች ዘንድ ተደነቀ። እግዚአብሔር ተአምራቱን በተለይም ለተናቁትና በሰው ዘንድ ለተጠሉት ሲገለጥ የማይደነቅና የማይደሰት ማን አለ?

ስምንት ቀን በሞላው ጊዜ በሥርዓታቸው መሠረት ሊገርዙትና ስምም ሊያወጡለት ወደዱ። እነርሱ እንደ መረጡትም በአባቱ ስም ሊጠሩት አሰቡ ነገር ግን እናቱ ኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ ገልጦላት ለዘካርያስ የተነገረውን የልጁን ስም ዮሐንስ እንዲሆን አለች። ዘካርያስም ቢጠየቅ ስሙ ዮሐንስ ነው አለ፥ በዚህ ከሚስቱ ኤልሳቤጥ ጋር ተስማማ። ይህም በሥፍራው የነበሩትን አስደነቀ። የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸው ባልና ሚስት በመሆናቸው ነገራቸው ሁሉ የተስማማ የተጣጠመ ሆነ።

እግዚአብሔር የመሠረተው ቤተሰብ የተስማማና የሚጣጣም ነው። በልብም በቃልም ተስማምተው የተገኙ ባልና ሚስት የሚኖሩት ኑሮ እግዚአብሔርን የሚያስመሰግን የሚደነቅ ነው።

የልጁ ስም ዮሐንስ እንዲባል በተናገረ ጊዜ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል የታሸገው አንደበቱ ተፈታ። የመልአኩን ቃል ከአረጋገጠ በኋላም ፈጣሪውን እግዚአብሔርን አመሰገነ። እግዚአብሔር በቸርነት ላይ ቸርነትን የሚያደርግለት ቤተሰብ ምንኛ የታደለ ነው? ምንኛ ግሩም ቤተሰብ ነው። የፈጣሪ ተአምራት የሚደረጉበት ትዳር ምንኛ ድንቅ ትዳር ነው? በአካባቢውና በጐረቤት የሚኖሩትን ሁሉ የሚያስደንቅና የሚያስፈራ የእግዚአብሔር ቸርነት በአካባቢው ላሉት ሀገሮች ሁሉ ሊነገር የሚገባው የመልካም ትዳር የጸና ሃይማኖትና የቀና ሥነ ምግባር ውጤት የሆነ መልካም ዜና የተገኘበት ቤት ከቶ እንዴት ያለ ቤት ይሆን? የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ቤት! ግሩም የካህን ቤት።

ይህን በመሰለ ገቢረ ተአምራት የተወለደው የዚህ ሕፃን ነገር እጅግ አስገረመ። መጨረሻው ምን ይሆን? የሚል አንክሮ የተሞላው ጥያቄ አስከተለ። በእርግጥ እግዚአብሔር በእርሱ ቸርነቱንና ተአምራቱን ገልጧልና በድንቅ ነገር ሁሉ አብሮት አለና ከመፀነሱ ጀምሮ እስከስም አወጣጡ ድረስ ያልተለየው እግዚአብሔር የገለጠው ተአምራት በእውነትም ይህ ሕፃን ምን ይሆን? ማሰኘቱ የማይቀር ነው። እንኳን ትንቢት የተነገረለትን መሲሕ የሚጠብቀው ሕዝበ እሥራኤልና እኛም በጎረቤታችን ተደጋጋሚ ተአምራትን እግዚአብሔር ሲሠራ ብናይ ማድነቃችንና «ምን ይሆን» ማለታችን የማይቀር ነው።

የዮሐንስ ልደት ምን ያስተምረናል? እስከ መጨረሻው ዘመናችን በመታገስ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ እንድንጠብቅ ያስተምረናል። እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ተስፋ ሳይቆርጡ በመታመን ጠበቁ። ቃሉን የማያጥፈው ቸር አምላክም የለመኑትን ልጅ ሰጣቸው በአይሁድ ዘንድ የነበረ እፍረታቸውን አስወገደ። እግዚአብሔርን የታመነ በተስፋም ተአምራቱን የጠበቀ እርሱ በፍጻሜው የሚሻውን ያገኛል። ኤልሳቤጥና ዘካርያስ የወለዱት የጽኑ እምነታቸው ፍሬ የሆነ ልጃቸው ዮሐንስ መወለዱ የሚያስተምረን ይህን ነው። ወደታማኞቹ ፈጣን መልእክተኞቹን ቅዱሳን መላእክትን የሚልክ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ለወዳጆቹ የገባውን ቃል አያጥፍምና የባሕርዩ የሆነውን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ተአምራት እንደገና በዘካርያስ ቤት አደረገው።

ለምርጦቹና በተአምራት ለለያቸው የራሱ ለሆኑ ወዳጆቹ የራሱ አጠራር ያለው እግዚአብሔር በብሥራቱ ጊዜ ለዘካርያስ የነገረውን የልጁን ስም ዮሐንስ (ሰላምና ተድላ) ብሎ ጠራው። የመጪው ሰላም የወንጌልን የምሥራች መንገድ ጠራጊ ነውና የጎበጠውን የሚያቀና የጠመመውን የሚያርቅ የተጣላውን የሚያስታርቅ የትውልዱን ልብ ወደ አባቶቹ የሚመልስ ነውና ስሙ በግብሩ ደስታና ተድላ ተባለ። ይህም በሰዎች ምርጫ ያይደለ በእግዚአብሔር ጸና። እንኳን ኑሮውና አገልግሎቱ ሕይወቱ ይቅርና የሚጠራበት ስም እንኳ በእግዚአብሔር የሚመረጥለት ሰው ምንኛ የታደለ ነው? እንዲህ ዓይነቱን ሰው ያስገኘችው ማኅፀን ይህን ያፈራስ ቤተሰብ እንደምን ይደነቅ፥ ግሩም የአምላክ ሥራ። ልጃቸው ከስሙ አንሥቶ በሕይወቱ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር በረከት እንዲያድግ የወለዱትን ሕፃን ለፈጣሪአቸው ቡራኬ አሳልፈው የሚሰጡ ወላጆች የተመሰገኑ ናቸው። ዘካርያስና ኤልሳቤጥ የመረጡት ስም እግዚአብሔር ለልጃቸው የሰየመውን ነው። የታዘዙት እግዚአብሔር ለፈቀደው እርሱ ለመረጠው ነው። ዛሬም በዓለማችን ያሉ ወላጆች በስዕለት የወለዱ ባልናሚስት ልጃቸውንና ኑሮውን መላ ሕይወቱንም እግዚአብሔር ለመረጠው እንዲሰጡ ወንጌል ያስተምራል። እገዚአብሔር የመረጠው ከሁሉ የተሻለ ከሁሉ የበለጠ የሚወዳደረውም የለምና። ስለዚህ እኛም የወለድነውን ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ እንማራለን።

ከፅንሱ ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተሰጠውና በማኅፀን እያለ ለድንግል ማርያም መስገድን ያስተማረ ወንጌልን የሰበከልን ዮሐንስ ከእናቱ ማኅፀን በወጣ በስምንተኛው ቀን የመልአኩን ቃል አላከብርም በማለቱ አንደበቱ በተግሣጽ የታሸገውን የአባቱን የዘካርያስን አፍ ከፍቷል። ብዙ የተዘጉ አፎችንና ድዳ የሆኑ አንደበቶችን የሚከፍትና የሚያናግር ሌላ ሳይሆን የእግዚአብሔርን የምስጋና ቃል የሚያናግር የታሰረውን አንደበት የሚፈታ ለምስጋና ምክንያት የሚሆን ልጅ ለመውለድ አስቀድሞ ፅንሱን ለፈጣሪው ማስረከብ ያስፈልጋል። የዮሐንስ ልደትና የወላጆቹ የካህኑ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ሕይወት የሚያስተምረን ይህንን ነው።

እግዚአብሔር የባረከው ልጅ የተወለደ እንደሆነ፤ ድንቅ የሆነ ሥራውን እግዚአብሔር በእርሱ የገለጠ እንደሆነ እግዚአበሔር ይመሰገንበታል፤ የፈጣሪን ቸርነት ዓይቶ የማያምነው ሕዝብ እንኳ ያምንበታል። ከፈጣሪው ይታረቅበታል። በእርሱ ሰበብ የእግዚአብሔር ቸርነት ይነገርበታል። የዚህ ብጤ ሕፃን ወላጅ መሆን ታላቅ መታደልና መመረጥ ነው። የዘመናችን ወላጆች የሚመኙት በዘመናዊና ዓለማዊ ጥበብ የበለጸገ ከዘመኑ ቴክኖሎጂና ከውጤቱ ጋር በቅርብ የተዋወቀ የፊልምና የሲኒማ ዓይነቶችን የሚያውቅ የፋሽን ዓይነቶችን የሚያደንቅ እንጂ ኀሊናው በቃለ እግዚአብሔር ተሰብሮ ዓለምንና የሚጠፋውን ነገር ንቆ ለማይጠፋው ዘለዓለማዊ ሕይወት የተዘጋጀ ወይም የሚዘጋጅ ልጅ ለመውለድ አይደለም ስለዚህ ትውልዱ ሁሉ ገና ከፅንሱ ያልተባረከ ስለሚሆን ቢወለድም ለራሱና ለቤተሰቡ ብሎም ለሀገሩ የማይጠቅም የሕዝብ ሸክም ሆኖ ይቀራል ምድራዊ ወይም ሰማያዊ ዓላማ የለውምና።

ለእግዚአብሔር የተሰጠ ፅንስ ልደቱም በእግዚአብሔር ተባርኮ ስለሆነ የሕይወቱም ፍፃሜ በረከት ነው። አስቀድሞ ሊባርከው የተቀበለው እግዚአብሔር ኋላም አብሮት ይሆናልና። እንዲህ ዓይነቱ ቤተሰብና ልጅ ያየውንና ያወቀውን ሁሉ የሚያስደንቅ የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚያሳውቅ አፍን ለምስጋና ልብን ለአንክሮ የሚከፍት ይሆናል። እንግዲህ ቤታችን የተባረኩ ልጆች የሚወለዱበት ኑሮአችን የእግዚአብሔር ቸርነት የሚታይበት አንደበታችን ስብሐተ እግዚአብሔር የሚነገርበት እንዲሆን እግዚአብሔር በቸርነቱ ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ አትለየን አሜን። ✣

ይቆየን።

ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም። እናንተም ትጠሩኛላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተም ትሹኛላችሁ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ ከእናንተም ዘንድ እገኛለሁ።

ኤር.29፥11–14።

ልጄ ሆይ፤ ልብህ ጠቢብ ቢሆን ልቤ ደግሞ ደስ ይለዋል፤ ከንፈሮችህም በቅን ቢናገሩ ኩላሊቶቼ ደስ ይላቸዋል። ልብህ በኃጢአተኞች አይቅና ነገር ግን ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑር፤ በእውነት ፍጻሜ አለህና ተስፋህም አይጠፋምና።

ምሳሌ 23፥15–18።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# "ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ" መዝ 117 ፥ 26።

ዋናው የምርቃት ትርጉም በእግዚአብሔር ስም የሚደረግ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተከትቦ የምናገኘው
ዊ ነገር ነው ። ዛሬ ግን ስመ እግዚአብሔር ሳይጠራ ምርቃት ሲካሄድ ይታያል ። በዘመናችን መጽሐፍ
በሚለው ዓይነት ምርቃት ሳይሆን ለየት ባለ ሁኔታ በየዓለማቱ ይከናወናል ።

በጥቅምት የተካሄደው የምረቃ በዓል ግን ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት እንደተናገረው ምርቃት በእግዚአ
ር ቤት ተካሂዷል ።

ዘወትር እሁድ እሁድ በተምሮ ማስተማርና በዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት ሥር መርሐ ግብር ተዘርግቶ
ው ስለ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናቸው እምነትና ሥርዓት ከሚማሩት በርካታ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሪዎች መካከል 258 የሚያህሉት በጥቅምት 1986 ዓ.ም. በጠቅላይ ቤተ ክህነት አዳራሽ ብፁዕ ወቅዱስ
ን ጳውሎስና ብፁዕን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት የእንኳን ደስ ያላችሁ መርሃ ግብር በቅንጅት ተካሂዷል ።

በዕለቱ ከቀረቡት ዝግጅቶች የብዙዎችን ትኩረት የሳበው ተመራቂዎች የምረቃ ልብሳቸውን እንደለበሱ
ረቡት ወረብ (ያሬዳዊ ዜማ) ነው ።

የጀርባ ፎቶግራፍ መግለጫ


የመጽሔታችን ማኅበርተኛ መሆን ለምትፈልጉ ሁሉ።

ለከ/ሀገር የዓመቱን ብር 38.40 ለአዲስ አበባ ብር 37.80 ወይም

ለከ/ሀገር የመንፈቁን ብር 19.20 ለአዲስ አበባ ብር 18.90 በአድራሻችን በአቶ ዮሐንስ አፈወርቅ ስም ብት ልኩ እያንዳንዱን እትም በአድራሻችሁ የምታገኙ መሆኑን ስንገልጽ በመንፈሳዊ አክብሮት ነው።

አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ
ሐመር መጽሔት ዝግጅት
የመ.ሣ.ቁ. 80078
አዲስ አበባ





የ1986 ተመራቂዎች
ከቅዱስ ፓትርያኩና
ከብፁዓን ሊቃነ
ጳጳሳት ጋር



ተመራቂዎች ያሬዳዊ
መዝሙር በበዓሉ ላይ
ባቀረቡበት ወቅት

ዋጋ 3.00 ብር

©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፤እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡